## ኢትዮጵያ እጆቿዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታለች፤



ጌታን ልትቀበል ሲመጣ ከሰማይ፣
እጇን ዘርግታለች ኢትዮጵያ ወደ ላይ።
ደስ ይበልሽ በጣም ኢትዮጵያ እማማ፣
በክርስቶስ መንበር ጭሆትሽ ተሰማ።
እጆቿን ዘርግታ ቁማ ስታለቅስ፤
ወደ ታች ወረደ እንባዋን ሊያብስ፤
የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ።
እራሱ ሊጎበኝ የኢትዮጵያን ምድር፣
ወደ መሬት መጣ በወርቅ መንኰራኵር።
በወርቅ መንኰራኵር ወረደ ክርስቶስ፣
በቃሉ መሰረት አንችን ለመፈውስ።
የኃያላን ኃያል የንጉሦች ንጉሥ
ለአንች ተገለጠ እንባሽን ለማበስ፣
የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ።
ከሰማይ ወረደ የፈጠረሽ ጌታ፣
ወጥተሽ ተቀበይው በእልልታ በሆታ፣
እንባሽን አቁመሽ በሳቅ በፈገግታ፣
ኀዘንሽን አቁመሽ ተሞልተሽ በደስታ፣
አንችን ሊያድን ወርዶአል ከረሃብ ከበሽታ፤
የዓለም መድኃኒት የሰማዩ ጌታ!!!

<u>***የሥዕሉን፤ ትርጉም ፤ ገጽ 33 ፤ ታገኙታላችሁ፤***</u>

## <u>መቅድም፤</u>

“እግዚአብሔር፤ በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውለውም፤ በሕልም በሌሊት ራዕይ አፍላ እንቅልፍ በሰዎች ሲወድቅ በአልጋ ተኝተው ሣሉ በዚያን ጊዜ የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል”። (ኢዮብ፡ 33፥14-17)
ራዕይ ወይም ሕልም እንበለው በሌሊት በምኝታ ሰዓት የሚታይ ነገር ነው። የሚታየውም ስለ ራስ ስለ ሀገርና ስለ ሰው ልጆች መጥፊያና መዳኛ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር በሰዎችና በእርሱ መካከል የሚሆነውን ነገር አስቀድሞ ይገልጻል። እንደ ምሳሌ አድርጌ የማቀርበው፣ እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋትና መዳን፣ እንዲሁም ስለ ራሱ ወደዚህ ዓለም መምጣት፣የተነበየውን ነው። በመጨረሻም ጌታችን መዳኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን አድኖ ሥራውን ጨርሶ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፤ ሐዋርያትን በአንድነት ሰብስቦ ዳግም ወደዚች ዓለም ተመልሶ መምጣቱን ሲያበሥራቸው“ኢየሱስ፡ከመቅደስ፡ወጥቶ፣ሄደ፥ደቀ መዛሙርቱ፡የመቅደሱን ፡ግንቦች ፡ሊያሳዩት፡ቀረቡ። እርሱ ፡ግን ፡መልሶ፡- ይህን፡ሁሉ፡ ታያላችሁ? እውነት፡ እላችኋለሁ፥ ድንጋይ ፡በድንጋይ፡ላይ ፡ሳይፈርስ ፡በዚህ ፡አይቀርም፡ አላቸው። እርሱም፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ተቀምጦ፡ ሳለ፥ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ለብቻቸው፡ ወደ፡ እርሱ፡ ቀርበው፡- ንገረን፥ ይህ፡ መቼ፡ ይሆናል ? የመምጣትህና፡የዓለም፡ መጨረሻ፡ ምልክቱስ፡ ምንድር ፡ነው ? አሉት። ኢየሱስም፡ መልሶ፡ እንዲህ፡ አላቸው፡- ማንም፡ እንዳያስታችሁ፡ ተጠንቀቁ። ብዝዎች፡- እኔ፡ ክርስቶስ፡ ነኝ፡ እያሉ፡ በስሜ፡ ይመጣሉና፣ ብዝዎችንም፡ ያስታሉ። ጦርንም ፡የጦርንም ፡ወሬ ፡ትሰሙ ፡ዘንድ ፡አላችሁ ፣ይህ ፡ሊሆን፡ ግድ፡ ነውና ፡ተጠበቁ ፥አትደንግጡ፣ዳሩ ፡ግን ፡መጨረሻው፡ ገና፡ ነው ። ሕዝብ፡ በሕዝብ ፡ላይ ፡ መንግሥትም፡በመንግሥት ፡ላይ፡ይነሣልና ፥ራብም ፡ቸነፈርም ፡የምድርም ፡መናወጥ ፡በልዩ ፡ልዩ ፡ስፍራ ፡ይሆናል፣እነዚህም ፡ሁሉ፡የምጥ፡ጣር፡መጀመሪያ ፡ናቸው።በዚያን፡ጊዜ፡ለመከራ፡አሳልፈው፡ይሰጡአችኋል፡ይገድሉአችሁማል፥ስለ፡ስሜም፡በአሕዛብ፡ሁሉ ፡የተጠላችሁ፡ትሆናላችሁ።

በዚያን፡ጊዜም፡ብዝዎች፡ይሰናከላሉ፡እርስ፡በርሳቸውም፡አሳልፈው፡ይሰጣጣሉ፡እርስ፡በርሳቸውም፡ይጣላሉ፤ብዙ፡ሐሰተኞች፡ነቢያትም፡ይነሣሉ፡ብዝዎችንም፡ያስታሉ፤ከዓመፃም፡ብዛት፡የተነሣ፡የብዙ፡ሰዎች፡ፍቅር፡ትቀዘቅዛለች።እስከ፡መጨረሻ፡የሚጸና፡ግን፡እርሱ፡ይድናል።ለአሕዛብም፡ሁሉ፡ምስክር፡እንዲሆን፡ይህ፤የመንግሥት፡ወንጌል፡በዓለም፡ሁሉ፡ይሰበካል፥በዚያን፡ጊዜም፡መጨረሻው፡ይመጣል"።
(የማቴዎስ፡ወንጌል፡ ምዕራፍ፤፳፬፡ቁ፡፩-፲፬፤ (24፤ከ1-14)

ስለ ጌታችን መድታኒታችን ኢየሱስ ክርቶስ፣ ከድንግል ማርያም መወለድ ፣ እኛን የሰው ልጆች ከመከራ ቀንበር ለማላቀቅና ለማዳን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማውጣት፣ የሰው ልጅ ያጣውን ክብር ለማስመለስ እንደሚመጣ፣ እርሱን በሚወዱት በሚያውቁትና በሚፈሩት ሰዎች አድሮ፣ በራዕይ ወይም በሕልም እንደ ገለጸላቸውና እንደነገራቸው ይህውም መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። እግዚአብሔር ይላል፣ "በመጨርሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ፥ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ህልምን ያልማሉ፣ ደግሞም በዚያ ወራት በዎንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፣ ትንቢትም ይናገራሉ"። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል አስፍሬዋለሁ። (ትንቢተ፡ ኢዩኤል፡ምዕራፍ፡፪፡ ቁጥር፡፳፰-፳፱፤(2፡ቁ 28-29) የሐዋ ርያት ሥራ ምዕራፍ፡፪ ከቁጥር ፲፯-፲፰ (2፡ቁ 17-18) ማየት ትችላላችሁ። ጌታችን መዳኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋው በረከቱ ሁልጊዜ ለሰው ልጆች የበዛ ከመሆኑ የተነሳ፣በአንድ በማልረባ ኢምንት በሁንኩት ሰው፣ በእኔ ላይ መንፈሱን አሳድሮ ፣ስለ ሀገራችን ስለ ቤተክርስቲያን፣ እንዲሁም እርሱን እንዲያገለግሉ ቤተክርስቲያንን እንዲያአስተዳድሩና ሕዝቡን እንዲመሩ በመረጣቸውና ባስቀመጣቸው ላይ ምን እንደሚፈርድ፣ የገለጸልኝን ከሞላ ጎደል በመጠኑ በመጽሐፉ ውስጥ አስፍሬውለሁ። ከአየኋቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ደርሰዋል ብዙዎቹ ገና ናቸው።

## <u>መግቢያ፤</u>

እንግዲህ ስለ ሀገራችንና ስለ ሕዝቦቿ የሚደርሰውን ግፍና በደል መከራና ሥቃይ፣ ከአየሁት ራዕይ በመነሳት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ መጥፋትና እንደ ጨርቅ መበጣጠቅ ፣ሕዝቦቿ በዕርስ በርስ ጦርነት መተላለቅ በበሽታ መሰቃየት፣ በረሃብ መጎዳት፣ በሦስት ነገሮች ሕዝቡ እንደ ቅጠል የሚረግፍበትን የሚያሳይ በተለያየ ዓመተ ምህረትና ወራቶች እግዚአብሔር የገለጸልኝን ከሞላ ጎደል አስፍሬዋለሁ። መልሶም ቤተ-ክርስቲያን ስትረገጥ ስትደፈርና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላደረባቸው ካህናት በጭቅጭቅና በጥላቻ ልባቸው ተሞልቶ በረከሰ አንድበታቸውና እጃቸው፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደሙን እንደሚያዘጋጁ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሐሳዊ መሲህ ይመጣል እንዳለው፣ እኔም በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሐሣውያን ካህናት እንደበዙባት ከነፍሳቸው ይልቅ ለሥጋቸው ያደሩ በመሆናቸው በዚህ የተነሳ እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸው ያየሁት። በሰሩት መጥፎ ሥራቸው ምን እንደሚደርስባቸው የብዙ ጳጳሳትና ካህናት እንዲሁም ዲያቆናት ስም ዝርዝር በዚህ ጽሑፍ ሳልገልጸው አልፌዋለሁ። ምክንያቱም ጥፋታቸውን አውቀው ንስሐ ገብተው እንደማይመለሱ ስለ ማውቅ ነው። እንዲያውም ያስቆጣቸውና ያበሳጫቸዋል እንጂ እግዚአብሔር አውቆብናል ብለው፣ ከጥፋታቸው አይመለሱም።
(ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ፡፶፫:ቁጥር ፩፤ (53 ፡ቁ 1) "የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል?"ይላል። እኔም የአየሁትንና የሰማሁትን ብናገር ማን ያምነኛል ብዬ ነው፣ የተውኩት። እንዲሁም ለኢትዮጵያ ጎረቤት ለሆኑት አገሮች ለኤርትራና ለሱዳን ምን እንደሚደርስባቸው የገለጸልኝን ግዜና ሰዓቱ ሲደርስ እራሱ ባለቤቱ ይግለጸው ብዬ በዝግ አልፌው አለሁ።
ኢትዮጵያ ሀገራችን ከደረሰባት አሳፋሪ ውርደትና ሽንፈት በራሱ ሰራዊት ጠላቶቿን እንደ ጭቃ እረግጦ ማእረግና ክብሯን መልሶ እንደሚያጎናጽፋት ከቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሐሳዊ ካህናት በእሷ ውስጥ ተኮልኩለው የገቡትን ተኩላዎች በራሱ ጅራፍ ገርፎ እንደሚያወጣቸው ቤቴ የጸሎት "ቤት እንጂ የወንበዴዎች ቤት አይደለችም " ብሎ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እንዳደረገው ሁሉ፤ አሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እንደሚያደርገው ግልጽ ነው። ከደረሰብን መከራና

ስቃይ ከአለብን ጥላቻና ተንኮል ምቀኝነትና ቂም በቀል አላቆ ስላምና ፍቅርን እንደሚሰጠን ስለ ሰዎች በቸርነቱና በምህረቱ እንደሚጎበኘን ካየሁት ነገር በመነሳት ነው፤ ይህን ልጽፍ የቻልኩት።

__“መጀመሪያይቱ፡የሐዋርያው፡የጳውሎስ፡ መልእክት፡ ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች። (ም፤ 14፡ቁ፡1-5)__

ፍቅርን፡ተከታተሉ፥መንፈሳዊ፡ስጦታንም፡ይልቁንም፡ትንቢት፡መናገርን፡በብርቱ፡ፈልጉ።በልሳን፡ የሚናገርስ፡ለእግዚአብሔር፡እንጂ፡ለሰው፡አይናገርም፤የሚያስተውለው፡የለምና፥በመንፈስ፡ግን፡ምሥጢርን፡ይናገራል፤ትንቢትን፡የሚናገር፡ግን፡ ለማነጽና፡ ለመምከር፡ ለማጽናናትም፡ለሰው፡ ይናገራል። በልሳን፡ የሚናገር፡ራሱን፡ያነጻል፤ ትንቢትን፡ የሚናገር፡ ግን፡ ማኅበሩን፡ ያንጻል። ሁላችሁ፡ በልሳኖች፡ ልትናገሩ፡ እወድ፤ነበር፥ትንቢትን፡ልትናገሩ፡ግን፡ከዚህ፡ይልቅ፡እወዳለሁ፤ማህበሩ፡ይታነጽ፡ዘንድ፡ንግግሩን፡ባይተረጐም፡በልሳኖች፡ከሚናገር፡ትንቢትን፡የሚናገር፡ይበልጣል”።

__ሁለተኛይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት። (ም፤1 ቁ፡20-21)__

እንዲህ ይላል፤ “ይህን፡ በመጀመሪያ፡ እወቁ፡ በመጽሐፍ፡ ያለውን፡ ትንቢት፡ ሁሉ፡ ማንም፡ ለገዛ፡ ራሱ፡ሊተረጉም፡አልተፈቀደም፤ትንቢት፡ከቶ፡በሰው፡ ፈቃድ፡ አልመጣምና፥ ዳሩ፡ ግን፡ በእግዚአብሔር፡ ተልከው፡ ቅዱሳን፡ሰዎች፡በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተነድተው፡ ተናገሩ።”

እንግዲህ ቅዱሳን ሐዋርያ በዚህም በሌላም ስለ ፍቅር በአጽንኦት ተናግረዋል። ይህን መጽሐፍ ለማንበብ እድሉ ያጋጠማችሁ ወገኖቼ በሙሉ፤ በጥሞና አንብባችሁ እንድትረዱት እግዚአብሔር ልቦናችሁን ይክፈትላሁ፤ ምክንያቱም ፤የእሱ የኃያሉ፤ ጌታ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ፤ቃል ነውና። ጽሑፉን በሁለት ምዕራፍ ከፍየዋለሁ፤ በሃይማኖትና በሀገር፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

## __ማሳሰቢያ፤__

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ አንድ የማሳስባችሁና የማስገነዝባችሁ ጉዳይ አለ። እሱም በሀገራችን የነገሰውና በስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች እንዳይመስሏችሁ፤ በእነሱ ጫንቃ ተቀምጦ የሚጋልባቸው ሰይጣን ነው። ሁለቱን ፈረሶቹን እግዚአብሔር ድንገት ቀምቶ ስለ ወሰደበት ዲያብሎስ ተበሳጭቶ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ለመበታተን አሁን በተለያየ ቦታ ብዙ ፈረሶች አሰማርቶአል። ይህውም በሃይማኖት ስም፤በፖለቲካ ወይም በድርጅት ስም፤ በመንግሥት ውስጥና ከመንግሥት ውጭ የሚቀሳቀሱ በአፋቸው ኢትዮጵያውያን በልባቸው ግን ከኢትዮጵያ የራቁ የእሷን መጥፋት የሚጠባበቁና እሷን ለማጥፋት ውስጥ ለውስጥ የሚሠሩና የሚታገሉ ብዙ ናቸው። እግዚአብሔር የአወቃቸው ሰው ያልነቃባቸው ወይም ያላወቃቸው እንደተኩላ እያደቡ ጊዜ የሚጠባበቁ ሃይማኖተኛነን የሚሉ እንደገና የፖለቲካ ሰዎች ነን የሚሉ በዬ ጊዜው ቃላቸውንና ዓላማቸውን እየቀያየሩ ሕዝብን የሚያደናግሩ ዲያብሎስ ያዘጋጃቸው የሕዝብን ፍላጎት የሚያሟሉ እየመሰሉ ሰውን ወደ እነሱ እየመለመሉ ለሰይጣን፤ እየጋበዙ ናቸውና ንቁባቸው። ይህ ሲሆን ግን የምትቋቋሟቸው ሁልጊዜ በጸሎትና በእግዚአብሔር ኃይል ነው። የሰዎቹን ስም ከዚህ ላይ መጥቀስ አልፈልግም ሁሉም ልባቸው ያውቃል ሃሳባቸውን ሕዝብ ባያውቅም እግዚአብሔር ግን ያውቃል፤ የሁሉም ስም በእግዚአብሔር ባሕር መዝገብ ተመዝግቦ ተቀምጦአል። ተሎ ንስሐ ገብተው እግዚአብሔርና ሕዝብን ይቅርታ ካልጠየቁ እነሱም እንደ አባ ጳውሎስና እንደ አቶ መለስ ሳያስቡት ድንገት ይጠራሉ። ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ሀገርና እምነት የነበራት መሆኗን ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ነው። ይህም የሆነበት ጀግኖች፤ጠንካራና እምነት የነበራቸው በቤተ ክህነትና በቤተ መንግሥት መሪዎች ስለነበሯት ነው። አሁን ያሉት ግን ከሀገርና ከእምነት የራቁ ልባቸው በእግዚአብሔር የሸፈተ በየቀኑ ኃጢአትን ሲሰሩ የሚውሉ ናቸው። ይህን ስል ግን በፊት የነበሩት ፍጹም ነበሩ ማለቴ አይደለም፤ሆኖ

ግን የነዚህ የተለየ ነው። የዚህን ጽሑፍ የሚገልጽ ወደ ፊት ስታነቡ ታገኙታላችሁ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ምድር ሰይጣንን ለማጥፋት እጆቹን ዘርግቶአል።

**ይህ ሰው ማነው? እንዳትሉ የኔን ምንነት ከዚህ ላይ መግለጽ አልፈልግም ፤ምንነቴን ማወቅ ከፈለጋችሁ የጻፍኳቸው መጽሐፎቶቼ ታትመው ለንባብ ሲበቁ የኔን ምንነትና ሙሉ ታሪኬን ታውቃላችሁ ይችን ጽሑፍ ከመጽሐፉ ቀንጨብ አድርጌ ነው ያቀረብኳት፤**

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር (August 2001)መጀመሪያ ሥንነሳ በህጋዊ መንገድ ልክ ከቦሌ አየር ማረፊያ ወደ አሜሪካ እንደ ሚጓዝ ሰው ሁነን ስንሸኝ ፤በጥሩ ሁኔታ ነበር። ከቀኑ አራት ሰዓት ማለትም ከሰዓት በኋላ፣ ከሊቢያ ዋና ከተማ ከትሪፖሊ ተነስተን ፣ወደ ስርጥ በሁለት ምኒ ባስ ሞልተን ከፖሊስ ጣቢያው ጎን ተሳፍረን። ማክሰኞ ምሽት ለሽርሽር የምንሄድ መስለን ስርጥ ወደብ ደረስን። እንደ ደረስን ቢዝነስ ማኑ(ደላላዩ) በግ አረደ ሕዝቡም በልቶ ያን ሌሊት ልንጓዝ ነበር። ሆኖ ግን በአጋጣሚ ሰው ተጠቃሎ አልመጣም ነበረና ለአራት ቀን ያህል ቆየን። ሰውም ተደናግጦ ተስፋ በመቁረጥ ላይ ነበር። ሆኖ ግን አራት መርከቦች ወደቡን እየተቆጣጠሩ ሽፋን ሲሰጡ ሰነበቱ። **ነሐሴ፡፫ቀን፡ ፲፱ ፻፺፫፤ዓ/ም የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ዕለት፤** እንዲህ የሚል ራዕይ አየሁ። “ተዘጋጅ ፈተና አለብህ ተግተህ ጸልይ” አለና አንድ ሰው ተናግሮኝ ከፊቴ ተሰወረ። እኔም ሰውየውን በአካል የአየሁት መስሎኝ ብድግ ስል ራእይ ሆኖ አገኘሁት። ሰይፈ ሥላሴን፣ ሰይፈ መለኮትን፣ ድርሳነ ሚካኤልን፣ ድርሳነ ገብርኤልን፣ ድርሳነ ሩፋኤልን፣ መልክአ ማርያምንና፣ መልክአ ኢየሱስን፣ እንዲሁም የዘወትር ጸሎት ውዳሴ ማርያም ሌሎች የጸሎት መጽሐፍቶቼን አዘጋጅቼ ይዤ ነበር። ወዲያውን ዓርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ ከንጋቱ አራት ሰዓት ላይ ተነሱ ተባልን። መመሪያ ሲሰጠን “እያንዳንዱ ሰው ጓዝ የሚባል ነገር እንዳትይዙ ተባልን፤ ሌላ ቀርቶ ምግብና ውሃ ሳይቀር። መቶ ሜትር እርቀት ላይ ትንሽ ጀልባ ቀረበች፤ እስከዛች ድረስ እያንዳንዱ ሰው እስከ ብብቱ ከውሃው ውስጥ ገብቶ በእግሩ ተጓዘ። ያች ጀልባ በተራ በተራ እያመላለሰች ወደ ትልቁ ጀልባ አደረሰችና ሁሉም ሰው ተሳፍሮ ከአበቃ በኋላ ትልቁ ጀልባ ተንቀሳቀሰ። የሊቢያ ዋናተኞችም ከአሳፈሩን በኋላ “አላህ መአኩም” (እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን)ብለው በዚያች ትንሽ ጀልባ ተሳፍረው ወደ ቦታቸው ተመለሱ። ካፒቴኑና አንድ እረዳቱ እስከ እንተርናሽናል ባሕር አድርሰው የያዝነውን ገንዘብ ሰጥተናቸው ተመለሱ። ሁለት መርከቦችም አሣ የሚያጠምዱ መስለው በቀኝና በግራ ሽፋን እየሰጡ በደህና ሸኙን። ዓርብ እለት ጀልባዋ ገና ሳትንቀሳቀስ ፣ለሁሉም ሰው የተጣላችሁ ታረቁ፥ የሰው ገንዘብ የወሰዳችሁ መልሱ፣ ቂም የያዛችሁ ከአላችሁ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባባሉ፣ ክርስቲያንም፤ እስላምም ሁሉም በሚያምነው ሃይማኖት ይጸልይ። ክርስቲያን የሆናችሁ ብትጾሙ መልካም ነው፤ ወቅቱ የጾም ጊዜ ነውና። አሁን የምንጓዘው ጉዞ የመከራና የፈተና መንገድ ነው፣ የምንሄደው ብዬ ተናግሬ ጸሎቴን ጀመርኩ። ጀልባዋ ከአቅሟ በላይ አንድ መቶ አምሳ (150) ሰዎችን ጭናለች፣ ሃያው ህጻናቶች ሲሆኑ የቀረው ትላልቅ ነው። አብዛኛዎቹ ወንዶች ናቸው፣ አምስት ሱዳናውያን፣ሰባት ባንግላዴሽ ፣አራት ኮንጎውያን፣ አምስት ሱማሌውያን ፣አስር ኢትዮጵያውያን፣ ከዚያ የተረፉት አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ(119) ኤርትራውያን ናቸው።

ቅዳሜ ሙሉ ቀን ስንጓዝ ውለን አድረን እሁድ ከንጋቱ ላይ፥ ነሐሴ 7ቀን፡የሥላሴ እለት ከባድ ማዕበል ተነሳ። ጀልባዋን ከውስጥ አስገብቶ መልሶ ያወጣታል ሕዝቡም ይንጫጫል። እኔ ቁሜ የምጸልይባትን ሥፍራ ከጭንቀት የተነሳ ከማእበሉ ያመለጡ መስሏቸው እየዘለሉ ገቡ። እኔም መጽሐፍቶቼን እንዳይበላሹብኝ በፕላስቲክ ሸፍኜ ጠቅልዬ ከሻንጣየ አስገባዋቸው። ከጀልባዋ ጠረፍ ተቀምጬ ውሃው በበላዬ እየሄደ ወርውሮ እንዳይጥለኝ በሁለት እጆቼ አጥብቄ ይዤ ተቀመጥኩ። ሰውም አለቅነ እያለ እሪ ይላል፣ ግማሹም ኧረ ቄሴ ጸልይ ስንሞት እያየህ ዝም አትበል ሲል። እኔም ተናግሬ ነበር፣ የሚሰማኝ አጣሁ ምንም ማድረግ አልችልም እንደናተ ሰው ነኝ ብዬ ዝም አልኩ። ማዕበሉ ቅዳሜ ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ ጀምሮ እስከ ሰኞ ቀጠለ። ሰኞ ቀትር አስራ ሁለት ሰዓት ላይ፥ ከባድ እንቅልፍ ተጫነኝ። አገር ቤት እያለሁ አንድ የማውቃቸው ሃጅ ከሪም የሚባሉ ትልቅ ሰው ነበሩ፣ እሳቸውን ተመስሎ አንድ ቀይ ትልቅ ሰው ቅቤ አምጥቶ ከአናቴ ላይ አስቀመጠልኝ። ኧረ ጌታዬ በጾሙ እንዴት ይሆናል ስለው። “ዝም በል ህልም የምታይበት ነው” አለኝ። ታዲያ ይቀልጥብኛል ስለው “በል የራሴን ነው የምሰጥህ ብሎ አንድ ጥላ ከትልቅ ሱቅ ውስጥ አውጥቶ ገትሮ ” ሰጠኝ። ወዲያው ትልቅ ጥቁር

ዘንዶ መጣ። እንዳለ ሰውን ሁሉ ሊውጥ አፉን ሲከፍተው፣ አንገቱን አንቄ ይገፔ ስታገለው አልወድቅልኝ ብሎ ለረጅም ሰዓት ቆየሁ። ክንዴ እየዛለ ሲሄድ ያለ የለለ ኃይል አንድ ጊዜ ተጠቅሜ ገነደስኩት። ገንድሼ ስጥለው ማእበሉ ተው እንደተባለ ሁሉ በአንድ ጊዜ ቆመ። ከእንቅልፌ ባትቼ ስነሳ ባሕሩ ጸጥ ብሏል፣ ህዝቡም እልል እያለ ደስታውን አቀለጠው።እኔም ፈጣሪየን እያመሰገንኩ የአየሁትን ህልም ነገርኳቸው። አሁንም መከራውና ፈተናው በዚህው አላበቃም ወዲያው የሚጠጣ ንጹህ ውሃ አለቀ ተባለ። እናትና ልጅ፣ አባትና ልጅ፣ የተካካዱበት ሰዓት ነበር። ጥቂት ውሃ ለሞተር መጠባበቂያ ተብላ የተቀመጠች ኑራ ፣ያችን ለህጻናቶች ለምላሳቸው ማራሻ ለጎሮሮአቸው ማርጠቢያ ቢባልም ቅሉ ሰሚ ጠፋ። ወላጆችም ለራሳቸው ነው እንጂ ለልጆቻቸው ያሰበ አልነበረም። እንዲያውም ሰዎች በውሃው የተነሳ ተጣልተው ተያይዘው ባሕር ውስጥ ገብተው ነበር። እኔም ተነስቼ እባካችሁ ተው ያን ማእበል ያቆመ አምላክ፣ ውሃ ይፈጥርልናል፣ ጸልዩ ተስፋ አትቁረጡ፤መልሶስ ይህን የጨው ባሕር ውሃ ወደ ንጹህ መቀየር የሚሳነው አምላክ መሰላችሁ፤ ብዬ ብናገር ሁሉም ተስፋ ቆርጦ ማን ይስማኝ። እግዚአብሔር ሆይ ለኛ ለኃጢአተኞቹ ሳይሆን ክፉና ደጉን ለይተው ለማያውቁት ህጻናቶች ስትል ምህረትህን አውርድልን፤ አምላኬ የአንድም ሰው ሕይወት ሳይጠፋ በሰላም ከዚህ ባሕር አውጥተህ ከየብስ ከአደረስከን፣ ያለ ውሃና ምግብ ሦስት ቀን እጾማለሁ አልኩና ጉዞአችን ቀጠልን።

ሰኞና ማክሰኞን ስንጓዝ ውለን ማክሰኞ ማታ ላይ የችችልያን ከተማ መብራት በሩቅ አየን። ወዲያውን እንደተቃረብን አወቀና ካፒቴኑ እንዳይታይ መብራት አጥፍቶ ተራራውን ተገን አድርጎ በጨለማ መጓዝ ጀመርን። ***<u>ቅዱስ ጳውሎስ ከአረፈባት ስራኩሳ ከተማ ደረስን።</u>*** ረቡእ ከንጋቱ አራት ሰዓት ላይ በዋናው ወደብ ሳይሆን፣ በሌላ ቦታ ከተራራው እግር ወስዶ አቆማት። ሁሉም ሰው እየዘለለ እንዲወጣ ተናገረ። ጉልበት ያለው የተራራውን አለት በእጁና በእግሩ እየሟጠጠ ሲወጣ፣ ጉልበት የሌላቸው ሴቶችና ህጻናቶችን ጨምሮ ከዚያው ከጀልባዋ ላይ ቀሩ። የተወሰን ሰዎች ጥርጊያ ላይ ወጥተን ውሃ ልመና ስንሄድ አንዲት መኪና ስትመጣ አይተን መንገዱን ዘጋነባት። ወዲያው ሹፌሩ ሲያቆም ጣሊያንኛ የሚችሉ ሁለት ኤርትራውያን ነበሩና "አኩዋ አኩሃ" (ውሃ ውሃ)ሲሉ። ፖሊስ ሊጠራ መኪናውን አዞሮ ወደ ከተማ ሄደ። ወዲያው ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ውሃ ይዘው ደረሱ። ሴቶችና ህጻናቶች በውሃ ጥም አለቁ ስንላቸው "የታሉ" ሲሉን ። ጀልባዋ ከቆመችበት ሥፍራ የተወሰኑ ሰዎች ሊያሳዩ አብረዋቸው ሄዱ። ከተራራው ራስ ሁነው ወደ ታች ፖሊሶቹ ባውዛ አብርተው ሲያዩ፣ ለካስ ጀልባዋ በታች የቆመ አለት ድንጋይ ገጭቷት ተሰብራ ውሃ ገብቶባት ወደታች እየሰጠመች ኑራለች። ወዲያውኑ ድንገተኛ ፈጥኖ ደራሽ ጀልባ ሕይወት የሚያድን (Life boat) ተጠርቶ አንቡላንስ(Ambulance) ጭምር ደረሱ። ሰውን እየዋኙ ወደ እነሱ ጀልባ ከአሸጋገሩ በኋላ ጀልባዋ አንድያዋን ወደታች ሰጠመች። የአንድ ሰው ሕይወት ሳይጠፋ ሁሉም በሰላም ወጣ። ሦስቱ ሥላሴ ተአምራቸውን አሳዩ፤ የኔንም ጸሎት ሰሙኝ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን አሜን።

ከዚህ በኋላ ከትልቅ አዳራሽ ውስጥ አስገብተው ውሃም ምግብም ተሰጥቶን ፣ሰው ትንሽ ከአረፈ በኋላ ቤተሰብ የሆነውንና ሴቶችን አስቀርተው ወንድ ወንዱን በአንድ ትልቅ አውቶቢስ ሞልተው ወደሌላ አካባቢ ወሰዱን። ከተባለው ቦታ ስንደርስ ከሌባውና ድራግ (drug) ከሚወስደው ጋር እስር ቤት አስገብተውን ለሳምንት የሚሃል ከቆየን በኋላ፤ አቤቱታ አቅርበን ጉዳያችን እየታየ ከእስር ቤት ተለቀን አንዳንድ ቅያር ልብስ ተሰጥተን ከዋናው ከተማ ወደ ሮም እንድንሄድ፣ጉዳያችንም ከዚያው እንደሚታይልን ተነገረን። ወደ ሮም ለመሄድ መሳፈሪያ ገንዘብ ስለ ሌለን ያለምንም ትኬት በባቡር ተሳፈርን ትኬት ተቆጣጣሪ ሲመጣ ጉዞው ሌሊት ስለነበር፣ ግማሹ ሽንት ቤት እየገባ ሲያመልጥ ግማሹ ደግሞ እንደተኛ ተያዘ። ወዲያው ትኬት ተቆጣጣሪው መጣና "ብሌቶ ብሌቶ"(ትኬት ትኬት)ሲል በዚያን ሰዓት ብሌቶ ምን እንደሆነ አናውቅም ቋንቋው አይገባነም መረዳዳት የለም፣ በዚህ የተነሳ እያወረደ ጣለን። ተሰብስበን ፖሊስ ጣቢያ ሄድን። የተሰጠን የፍቃድ ወረቀት አሳየን፣ ያን አይቶ በነጻ ተሳፍረን እንድንሄድ ለተቆጣጣሪው ተናግሮ በሌላ ባቡር አሳፍሮ ወደ ሮማ ላከን። ሮማ ተርምኒ (ባቡር ጣቢያው )ደርሰን ወረድን። ከዚያ የምንሄድበት ግራ ገባን፣ በእንዲህ እንዳለን ሱማሌውያን ተሰባስበን ሮማ ካለው ከሱማሌ ኮምኒቲ ለአንድ ቀን እናድራለን ብለው ሲያጽናኑን። ኤርትራውያን ግን እንዳይጥ ልጅ ሹልክ ሹልክ እያሉ ከኛ ተሰወሩ። ከጥርጊያ ላይ ቁጭ ብለን በጭንቀት ላይ ሳለን። ከክፍለ ሀገር ከብሃሪ ለረፍት የመጡ ሁለት ሴቶች ያገኙናል። መብራት የምትባል አንደኛዋ መጥታ ለኔ "አወይ ወንድሜን ትመስላለህ" ብላ ሳመችኝ።

ከዚያም ወንድሟ አለመሆኔን ከአወቀች በኋላ፣ የአዲስ አበባ ልጅ ነህ ወይ ብላ ጠየቀችኝ። እኔም አይደለሁም የጎንደር ልጅ ነኝ አልኳት። እርግጥ እሷም የአዲስ አበባ ልጅ አይደለችም የትግራይ ልጅ ነች። ከዚያ በኋላ የመጣነበትን አገርና በመንገድ የደረሰብን መከራና ችግር፤ አሁንም ከዚህ ከደረስን በኋላ የሚተባበረን ዘመድና ለጊዜው የምናርፍበት ቦታ እንደሌለን ገልጬ ስነግራቸው፣ በጣም አዝነው አለቀሱ። በኋላ ምሳ ሊያበሉኝ "ወደ ምግብ ቤት እንሂድ" ሲሉኝ፤ ኤርትራውያንን ጨምሬ ብዙዎች ነን ስላቸው። ወደ ሠላሳ ለሚጠጋ ሰው ምግብና ውሃ ለስላሳ መጠጥ ጨምረው ገዙ። እኔ ጾመኛ ነኝ ይህን የገደፈ ምግብ አልበላም ስል፣ ለብቻ የጾም ምግብ አሰሩልኝ። ኤርትራውያን ቢፈለጉ ጠፉ። ለካስ የእነሱ ሰዎች መጥተው እኛ እንዳናያቸው ተደብቀው እየጠቀሱ ይዘዋቸው ሂደዋል። እኒያ የጋበዙን ሴቶችም "እኛ እንዳናሳድራችሁ ሆቴል ነው ያለነው" ብለው፣ በእኛ እየተጨነቁ ሳለ። ድሮ ከሊቢያ የማውቀው ልጅ አጋጣሚ በዚያ አልፎ ሊሄድ ሲል አየሁት። ስጠራው ዞር ብሎ ሲያይ እኔ ነኝ። "ቄሴ ብሎ መጥቶ ተገናኘኝ"። ከተሳሳምን በኋላ ሁኔታውን ገልጬ ማደሪያ እንደሌለን ነገርኩት። "በሉ እንግዳ የሚቀበሉ ሁለት መነኮሳት ሴቶች አሉና ወደዚያ እወስዳችዋለሁ"አለን። እሱም እንደ ኤርትራውያን እኛን ደብቆ ለመውሰድ አስቦ ሲጠቅሰን፣ ሱማሌውያን ማደሪያ ቦታ አላቸው ሱዳኖቹ ግን እንደኛ ናቸው ቦታ የላቸውም አልኩና እነሱንም የእኛን እግር እያዩ እንዲከተሉን በዓይን ጥቅሻ ነገርኳቸው። ሁላችንም ልጁን ተከትለን ከአንድ አውቶቢስ ተሯሩጠን ተሳፈርን። ከወረድን በኋላ ልጁ እሱ ይዟቸው መጣ እንዳይባል ከገባ በኋላ ትንሽ ቆይተን እንድንገባ ቦታውን አሳይቶን ሄደ። እኛም በተነገረን መሰረት ቆይተን ከግቢው ገባን፣ ስንገባ ቤቱ በእንግዳ ሞልቷል። ከኛ ተደብቀው የሄዱት ኤርትራውያንም ከዚያ ቤት ሂደው ገብተዋል። አልጋ የሚባል የለም የዛሬን ከዚህ ከወለሉና ከሶፋው ላይ እደሩ ተባልን። ከዚያም እራት ሲሰጠን እኔ አሁንም ጾመኛ ነኝ የገደፈ ምግብ አልበላም አልኩ። ወዲያው አዘጋጁ ሂዶ ለመነኮሳቱ ነገራቸው፣ ተጠርቼ ሄድኩ። ሃይማኖቴን ተጠየቅሁ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንደሆንኩ ተናገርኩ። የጾም ምግብ እንዲዘጋጅልኝ ለአስተናጋጁ ተነገረው። እንዲሁም የምተኛበት አልጋ ፈልጎ እንዲሰጠኝ ተነገረው። እራቴንም በላሁ፣ ከጥሩ ምኝታም ተኟቼ አደርኩ። ጧት ተነስቼ ከግቢው ሁኜ የዘወትር ጸሎት ሳደርስ ወደ ቤተ-ክርስቲያን ሊሄዱ ሲወጡ አዩኝ። ሁለቱ መነኮሳት መጥተው እጅ ነሱና "ለእኛም ጸልይልን" ብለው ወደ ቤተ-ክርስቲያን ሄዱ።

*ያ ሊቢያ ወደብ ላይ ሳለሁ የተገለጸልኝ ራእይ እውነት ሆኖ ደረሰ። ከላይ እንደገለጽኩት **<u>ነሐሴ ፫፡ቀን፡የአቡነ ገ/ መንፈስ ቅዱስ ዕለት</u>** ከላይ ካየሁት ራዕይ ጋር ተጨማሪ ሁለት ትላልቅ ሴቶች ነጭ ልብስ ለብሰው ከፊቴ መጥተው ሲሰግዱልኝ አየሁ። እኔም በአካል ያየኋቸው መስሎኝ ብድግ ስል አሁንም ራዕይ ነበር። በኋላ ግን ሮም ስገባ ያ ከሁለት ሳምንት በፊት ያየሁት ራእይ እውነት ሆነ በሁለቱ ደናግል ሴቶች ተገለጸ። ጉዳያችንም ተከታትለው ከመንግሥት በኩል አስፈጸሙልን። ከዚህ ላይ ለአንባቢያን የማስገነዝበውና ግልጽ ማድረግ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር። የእግዚአብሔርን ተአምር፣ ለመግለጽ ፈልጌ ነው እንጂ የራሴን የሕይወት ታሪክ ከዚህ ላይ ለመጻፍ እንዳልፈለክኹ እድትገነዘቡልኝ እውዳለሁ።*

*ያን ሁሉ መከራና ፈተና አልፈን ሮም ገብተን ወደ ተመደብነው ቦታ ሄድን። አንድ አካባቢ ከተመደብነው ሦስት ሱዳናውያን ሶስት ኢትዮጵያውያን ሰባት ኤርትራውያን ነበርን። ወቅቱ የባድሜ ጦርነት በነበረበት ጊዜ ስለ ሆነ የተረከበን ድርጅት ለየብቻ መደበን። ኤርትራውያንን ለብቻ ኢትዮጵያውያንና ሱዳኖችን በአንድ ላይ፣ በአጠቃላይ ሁሉም ሲጋራ አጢያሾች ነበሩ። ግን እግዚአብሔር ይስጣቸው የምጸልይባትን ክፍል አያጤሱባትም ነበር። እኔም ሥላሴን ያችን ቀን እያሰብኩ በየ ወሩ እዘክር ነበርና፤ አንዳንዴ ከእኔ ይልቅ ሱዳኖቹ ቀኑን ያስተውሱኛል"ያ ገሲስ አልዮም አምስታ ሽር" (ቄሴ ዛሬ ቀኑ አስራ አምስት) ነው ይሉኛል። ኤርትራውያን ክርስቲያኖቹና እስላሞቹ አልስማማ አሉ። ምክንያቱም እሮመዳን የእስላሞቹ ጾም ገብቶ ስለ ነበር፣ ክርስቲያኖቹ መጠጥ እየጠጡ እረበሿቸው ለእስላሞቹ። የውስጡን ችግር ገልጠው ሳይነግሩኝ በጾሙ ምክንያት አድርገው ለኔ ቦታ ቀይረን አሉ። እኔም በቅንነት እሽ ብዬ ቀየርኳቸው። አሁንም ለኔ እየሰከሩ መበጥበጥ ጀመሩ የምጸልይበትን ቦታ እየጠጡ እያጤሱ አበላሹት። ብናገራቸውም "አሁንስ ነጻነታችን ልትገፍ ነው መሰል አንዱን ጋዳፊ አውጥተን አንደኛውን ጋዳፊ አስገባን" ብለው፣ በሊቢያው መሪ መስለው ተናገሩኝ። ለድርጅቱ ተናገርኩ "ለብቻህ የምትጸልይበት ቦታ ለአንተ ለማግኘት ከባድነው እስከ ዚያው*

ፈልገን እስከምናገኝልህ ድረስ አንድ ኢጎዝላቢያዊ ክርስቲያን አለ ከእሱ ጋር ተቀመጥ" አሉኝ። አንድ ቀን የሥላሴ እለት ነበር፣ ኮካ ኮላና ኬክ አድርጌ ስለ ሥላሴ ስል፤ አንደኛው መንፈስ ርኩስ የተጠጋው "ሁል ጊዜ በዚህ ትሸኘናለህ ለምን ቢራ አትገዛልነም" አለኝ። እኔም እንዳንተ አልደላኝም ፈጣሪየ ከዚያ ሁሉ መከራ ስለ አወጣኝ እሱን ለማስታወስ ነው እንጂ ሌላ እንዳይመስልህ ብዬ በዚያ የተነሳ ተነጋገርን። አንደኛው እግዜር ይስጠው አንዳንድ ጊዜ ሌሊት እየተነሳ ያጸዳልኛል። ከዚያ የተረፈውን ግን እኔው ራሴ እነሱ ከተኙ በኋላ አጽድቼ ጸሎት አደርጋለሁ። እነሱ ከመነሳታቸው በፊት ወደ ምኝታ ክፍል ሂጄ እተኛለሁ። ከእለታት አንድ ቀን በሰውየው የተነሳ ተበሳጭቼ ጸሎት ሳላደርግ እግዚአብሔር ይፍረድብህ ብዬ ተኛሁ። ወዲያውን የሰውየው ዓይን በሽረሪት ዝሐ ሲዘጋና ሲሸፈን በራዕይ አየሁ። ከአንድ ወር በኋላ ሰውየው ዓይኑ እንደፈጠጠ ሸፈነው፣ አላይ አለ። ከዚያ ሆስፒታል ሂዶ ሲመረመር "ኦፕሬሽን መሆን አለብህ" ተባለ። ሦስት ቀን ተኝቶ ከሆስፒታል ወጣ። አሁንም አልተሻለውም ተመልሶ ሆስፒታል ገባ። አሁንም ደግሞ ሲመረመር "ጭንቅላትህ ኦፕሬሽን መሆን አለበት" ተባለ። በዚህ የተነሳ በአጠቃላይ ሰውነቱ በሙሉ በበሽታ ተበከለ ፤ዓይኑም እየባሰ እየጋረደው ሄደ። እኔም ከዚያ በኋላ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር ተዛወርኩ። አንድ ቀን ጉዳይ ኑሮኝ ተመልሼ ከዚያ ቦታ ሂጄ የመድኃኔዓለምን ስእል አስቀምጦ አገኘሁት። አንድ ሱማሌ ያን ነገር የሚያውቅ "ቄሴ ሌላው ቀርቶ መስገዱን እንኳ በቅጡ አያውቅበትም" አለኝ። ሦስቱ ሥላሴ የሰሩት ሌላም ብዙ ተአምር ነበር፣ ሆኖ ግን የራሴ ታሪክ እንዳይመስልብኝ ብዬ ትቸዋለሁ።

## ሥላሴ፤

ሎጥን እንዳዳኑት ነፐለው ከሰዎች
የአብርሃም አምላክ ሦስቱ ታዳጊዎች።
　　አዳኑ እስራኤልን ቀይ ባሕርን ከፍለው
　　እኔንም አዳኑኝ ከማዕበል አውጥተው
　　መቶ አምሳ ነፍሳትን ከዘንዶ አፍ መንጥቀው።
የሁሉ ፈጣሪ ሥሉስ ቅዱስ ናቸው
ዓለምን ጨብጠው የያዙ በእጃቸው
ክብርና ምስጋና ለእነርሱ ይግባቸው።
　ከሰማያት ወርደው የሰውን ልጅ ቋንቋ በመበተናቸው
　　ሲደነቅ ይኖራል በዓለም ሥራቸው።
አጋዕዝተ ዓለም ከአብረሃም ቤት ገብተው
ምግብ ተመገቡ በሰው ተመስለው።
　　ሰውን እንፍጠረው በአምሳላችን ብለው
　　አዳምን ፈጠሩ ከጭቃ ለውሰው
　　ወደ ምድር መጡ ይሄነን አስበው
　አብርሃምን ጎበኙት ደግነቱን አይተው።
እንደ ባሕር አሸዋ ዘር ይበዛልሃል፤
ሣራም ትወልዳለች ስሙን ይሠሐቅ በለው
የዓለም ገዢ ይሆናል ከአንተ የሚወለደው።
　　ቃል ኪዳን አድርገው ሄዱ ተሰናብተው
　　በእርሱ ብቻ ነው ዓለም የሚድነው።

## መስከረም፡፳፩፡ቀን፡፲፱ ፻፺፯ (21/1997፤ዓ/ም፣)

ኢጣሊያ በነበርኩበት ጊዜ አንድ በጣም የምወደው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፤የሰንበት ተማሪ ልጅ ነበር፤ ከሥራ ውሎ ሁልጊዜ ቤተ-ክርስቲያን ሳይደርስና ሳይሳለም ወደ ቤቱ አሄድም ነበር። ለኔ ሁል ጊዜ ከቤተ-ክርስቲያን ስንገናኝ ጸልይልኝ ጸልይልኝ ይለኝ ነበር። እኔም ከዚያ እስካለሁ ድረስ ዳዊት ስደግም ስሙን እየጠራሁ ሁልጊዜ እጸልይለት ነበር። ከዚያ በኋላ በንጹህ ሁነህ ጸልይ ጾም ጹም ስገድ

ሁልጊዜ ቤተ-ክርስቲያን አትለይ ችኩል አትሁን ብዬ ምክሬን ለግሸለት **ሐምሌ ፲፰፡ቀን፡፲፱ ፻፺፮ (18/1996ዓ/ም)** እሱ የሐምሌ ቅዱስ ገብረኤልን ልያነግስ ወደ ሚላኖ እንደሚሄድ ገለጾልኝ እኔም ወደ ብርታኒያ እንደምሄድ ነግሬው በዚህ ተለያየን። እንግላንድ ከመጣሁ በኋላ አልፎ አልፎ ወደ ኢጣሊያ ለአባ ስደውል ወልደ ገብርኤል ደህና ነው ስላቸው፣ እሳቸውም በዓለም ስሙ ነው፣ ብዙውን ጊዜ የሚጠሩት ማነው ሲሉኝ። ልጁ ከሚሰራቸው አንዳንድ ነገሮችን ስጠቅስላቸው "እህ ተሼ ተሾመ አዎ ስላቸው ደህናነው" ይሉኛል። ከእለታት አንድቀን ሮማ ካለችው ቤተ-ክርስቲያን ሲያገለግል የነበረ አንድ ልጅ ከዚህ መጥቶ ሊድስ መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን አግኝቸው፣ ስለ ልጁ ስጠይቀው "ተሼ እማ የመስከረም ማርያም እለት ልክ የዛሬ ዓመት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ" ሲለኝ ከአለሁበት ክው አልኹ። ትንሽ ቆይቼ ስለ አማሟቱ ስጠይቀው "ጓደኛው ጥላ ገትሮ እሱ ሙዳዬ ምጽዋት ይዞ ከአንድ ሰው ጋር ሆኖ መባእ ሊሰበስቡ ሲዘጋጁ ጎኔን ወጋኝ ብሎ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ስእል ሂዶ በርከከ" አለ። "ከዚያ ጓደኞቹ አንስተው ቅዳሴው እስከ ሚያልቅ ድረስ ከቤተ-ክርስቲያኗ ከአንድ ክፍል ውስጥ አስቀመጡት ቅዳሴው ተፈጽሞ ሂደው ሲያዩት ሕይወቱ አልፎ አገኙት። እሱ ቁሞ ከሚያስቀድስበት ቦታ ላይ ጃኬቱ ተሰቅላለች አጋጣሚ ኪሱን ስንፈትሽ አንዲት ጽሁፍ አግኚተን ስናነባት እመቤቴ ወደ እኔ ና ትለኛለች የምትል ነበረች" ብሎ ሲነግረኝ ማመን አቃተኝ። እንዴት ሊሆን ቻለ ብዬ በእግዚአብሔር ሥራ ልመራመር ገባሁ። በሮማ ደብረ ጽዮን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ይህ የተከሰተ አሳዛኝና አስደንጋጭ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ነገር ነው። ከዚያ በኋላ መቅሰፍት ወይስ ጽድቅ እንዲህ ያለ አማሟት ከቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እያልኩ ራሴን መጠየቅና ማስጨነቅ ጀመርኩ። ከቤተ-ክርስቲያን ተመልሼ እህል ውሃ ሳልቀምስ አመሸሁ፣ ድንጋጤውም እንደ ማበሳጨት አድርጎኝ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቼ የዘወትር ጸሎት ሳላደርግ ከምኝታየ ሂጄ ተኛሁ።

ከሌሊቱ አራት ሰዓት ላይ ብዙ ሕዝብ ቦርጩ የተንጠለጠለ ሱሪ ሳይታጠቅ እንዲሁ ከወገቡ በታች ልብስ አገልድሞ መስቀለኛ መንገድ ላይ ቁሞአል። አንድ ትልቅ ሰው ይመጣና ሕዝቡን በግራ በኩል እኔን በቀኝ በኩል አቁሞ ሲያበቃ "ሂዱ ወደ ፊት" ይለናል። ጥቂት መንገድ እንደ ተጓዝን ያን መስቀለኛ መንገድ ስንጨርስ ሕዝቡን እንደከብት ወደ ሜዳ ገፍቶ ሰደደው። እኔን በቀጭን መንገድ አስገብቶ እሱ በቀኝ በኩል ከመንገዱ ዳር ሆኖ ጎን ለጎን እየሄደ፣ ወደ ትልቅ ተራራ ይዞኝ ወጣ። ተራራው በጣም ቀጥ ያለነው፣ ደከመኝና በግራ እግሬ ተምበርክኬ በቅኝ እግሬ እየሄድኩ ተራራውን በጭንቅ ወጣሁት። ከተራራው ከወጣሁ በኋላ በባሕር መሃከል በድቃቃ ድንጋይ የተካበ በጣም ጠባብ የሆነች የአንድ እግር ጫማ የማታስቆም እንደ ገመድ ተዘርግታ በሩቅ አየሁ። ሰውየው "በል በዚያች አድርገህ ሂድ" ይለኛል። ሂጄ ቀረብ ስል ያነ ባሕር ተቀይሮ እሳት ሆኖ አንዳንዴ እንደ እሳተ ገሞራ ወደ ላይ ይፈነዳል፣ ወዲያው ተቀይሮ የእሳት እረግረግ ይሆንና ፤ዶቅ ፤ ዶቅ ሲል ሰማይ ደርሶ ይመለሳል። ይህን እያየሁ እየተንቀጠቀጥኩ እግሮቼን ፊትና ኋላ እያደረክኹ በዚያች ቀጭን ካብ መንገድ ለረጅም ሰዓት ተጓዝኩ። **ከዚያው ላይ እንዳለሁ ዙሪያው ሰማይ ብቻ ሆነ፣ ወዲህ ብዞር ወዲያ ብዞር መሬት የሚባል የለም፣ ከዚያ ሰማይ ውስጥ የአንድ ሰው ድምጽ እንደ ነጎድጓድ ሲያገመግም ሰማሁ። ወዲያውኑ አብሮኝ ለአለው ሰውየ መልሰህ ውሰደው የሚል ትእዛዝ ሲሰጠው ሰማሁ። ዞር ብዬ ሳይ መሬት ላይ ነው ያለሁት፣ አብሮኝ የነበረው ሰውየም ከእኔ ተሰወረ።**

**ከዚያን እለት ጀምሮ ለሦስት ቀናት ያህል ታምሜ ሰነበትኩ። በአራተኛው ቀን በ፳፬፡ቀን፡ ፲፱ ፻፺፯ (24/1997 ዓ/ም) በአቡነ ተክለሃይማኖት እለት ረቡዕ ቀን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ አንድ ጢሙ እረጅም የሆነ ሰው ከምኝታየ አስነስቶ ወደ በረሃ ወሰደኝ። ከበረሃው እንደ ደረስን አንድ ትልቅ ዛፍ ቆርጦ ጣለና ቃዛውን ቀፍቅፎ ሲያበቃ ሁለት መንታ ያለው እረጅም ምሰሶ አድርጎ "ና ተሸከም" ይለኛል። ኧረ ጌታዬ አልችለውም ብለው "በግድ ትሸከማለህ" አለና አንስቶ በባላው በኩል ያሸከመኛል። እንዲቀለኝ በቂጡ በኩል ልሸከም ብለው "አይሆንም" አለኝ። ያን ምሰሶ እየተጨነቅኹ ተሸክሜ ወደ ትልቅ ተራራ ይዞኝ ሄደ። ያን ተራራ እየወደቅኹ እየተንሳሁ በግድ ወጣሁ፣ ከዚያ በኋላ ሸክሙን ጣልኩት። ሰውየውም ከኔ ተሰወረ። እኔም በሽታው ለቀቀኝ ጤነኛ ሆንኩ፤ ከዚያ ወዲህ ነው ምስጢራዊ የሆኑትን ብዙ ራዕይ የገለጸልኝ።**

## ክፍል አንድ፤
## ራዕይ በኢጣሊያ፤ስለ ቤተክርስቲያን፤
## ሚያዝያ፡፳ ፬፡ቀን፡፲፱ ፻፺፮ (በ1996ዓ/ም፣)

ጣሊያን በነበርኩበት ጊዜ የአየሁት ራዕይ፤ ሮም ባለችው ቤተክርስቲያን ነበር። በአንድ ሌሊት አንድ ካባ የለበሰና በራሱ ላይ ዘውድ የሚመስል የጫነ ጢሙ በጣም ረጅም የሆነ ትልቅ ሰው፤ መጥቶ በዛች ቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚያገለግሉ አንድ ደግ መነኩሴ እንዲህ ብለህ ንገራቸው የሚል ቃል ነገረኝ። እኔ የነበርኩበት ቦታ ከሮም ወጣ ያለ ክፍለ ሀገር ነበር። ያየሁበት ቀኑ **የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕለት (ሚያዝያ ፳ ፬፡ቀን፣፲፱ ፻ ፺፮** (በ24/ 1996) **ነው።** ያ ትልቅ ሰው የነገረኝ ቃል እንዲህ የሚል ነበር። "ሂድና ለዚያ መነኩሴ በርህን ዝጋ አትክፈት ተጠንቀቅ ጽኑዕ ሁን ብለህ ንገረው" አለኝ። ከዚያ ለዚያ መነኩሴ አፍነው ሊወስዱት የተሸፋፈኑ ፊታቸው የማይታይ ግን የሰው ቅርጽ ያላቸው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ቤት፣ አውጥተው ሊወስዱት ሲሉ፣ ያ ትልቅ ሰው ዘንጉን ልኮ ሲከላከልለት አየሁ። እነዚያም ሰዎች መነኩሴውን ሳይወስዱት ቀሩ። ያ ትልቅ ሰውም ከፊቴ ተሠወረ። እኔም ከእንቅልፌ ነቃሁ በገሀድ ያየሁት መስሎኝ ነበር፣ ስነሳ የለም ራዕይ ሆኖ አገኘሁት። ከዚያም ሳልዘገይ በማግስቱ ተነስቼ ለኒያ መነኩሴ ያየሁትን ልነግራቸው የባቡር ተኬት ቆርጬ ጉዞየን ቀጠልኩ። ጉዞውም አምስት ሰዓት ያህል ጨረሰብኝ። ደግነቱ ማልጄ ስለተነሳሁ አባን ቤተክርስቲያን ከፍተው ኪዳን ሲያደርሱ አገኘኋቸው። እኔም ገብቼ ተሳልሜ የራሴን ጸሎት አደርስኩ። ከዚያ አባ ኪዳን አድርሰው ከጨረሱ በኋላ መስቀል ተሳለምኩና ሰላምታ ተለዋውጠን ቁጭ አልን።እርሳቸውም የምኖርበት ሀገር ሩቅ መሆኑን ስለሚያውቁ "በደህና ነው ምነው ዛሬ መጣህ"? አሉና መጠየቅ ጀመሩ። እኔም መለስኩና፣ አባ አመጣጤ ከእርስዎ ነው ስላቸው "ምነው በደህና"? አሉኝ።እኔም ነገሩን ጀመርኩላቸው ምቀኛ ተነስቶብዎታል በዚህ ላይ ይጠንቀቁ አልኳቸውና፣ አንድ ትልቅ ሰው በሩቅ ሆኖ በዘንግ ሲከላከልሎዎት አየሁ እርሱም በራፉን ዝጋ በለው ብሎ አለኝ፣ እና ያየሁትን ልነግርዎት ነው የመጣሁት አልኳቸው። ነገር ግን ይህን ሲል ቤተክርስቲያን ለቀው እንዳይወጡ ለማለት ነው።አባም እንደመበሳጨት አሉና "ለነገሩ ተነስተውብኛል ሊያኖሩኝ አልቻሉም" በማለት ስሜታቸውን እየተቆጣጠሩ ቆይተው አሁንም እንደመበሳጨት አሉ።

"አይ እንዲያው አንቺ ቤተ ክርስቲያን ለሚሆንሽ አትሆኚ እስከመቼ ተገፍተን እንኖራለን" አሉ። ለነገሩ መነኩሴው በጣም ተሰምቷቸው ነበር፤ ቆዩና እንደማሰብ ብለው ለነገርኳቸው ነገር መልስ ሲሰጡኝ። "አይ እኔ በሕልም አላምንም ጠባቂዬ እርሱ አንድዬ  መድኃኔ ዓለም ነው" አሉና ነገሩን በዚህ ዘጉት። እኔም መልሼ ይመኑ አይመኑ ይህ የእርስዎ ፋንታ ነው፣ እኔ ንገር የተባልኩትን ነግሬዎትአለሁ አልኳቸውና፤ መልሼ አባቴ ሆይ እግዚአብሔር እኮ ለሰዎች ሲናገር ወይም ሊገልጽ ሲፈልግ በሰው እየተመሰለ ነው።  ድሮ በነቢያቶች አማካይነት ለሰዎች የሚድኑበትንና የሚጠፉበትን ነገር ሲነግራቸው የነበረ፣ አሁንም እርስዎ ካላመኑ ሲደርስዎት ያውቁታል አልኩና ነገሩን በዚህ አቆምነው። ከቤተ-ርስቲያን ወጥተን ሻሂ ቤት ሄድን ሻሂ ጠጥተን በዚህ ተለያየን። እኔም በመጣሁበት ባቡር ወደ ቦታዬ ተመለስኩ።  ከዚህ በኋላ ልክ በአየሁት በሳምንት ግንቦት አንድ ቀን የእመቤታችን ማርያም ልደት ዕለት እሁድ ሲውል ቅዳሜ ማታ ክንፍ ያለው ቀይ ዶሮ የሚመስል ከትክሻዬ ላይ ተቀምጦ ተነሳ ሂድ ሂድ ይለኛል፣ክብደቱ አላንቀሳቅሰኝ አለ። ከዚያ ተነስቼ ለጓደኞቼ ሮም መሄድ አለብኝ አልኳቸው። "እንዴት አሁን ትሄዳለህ ማልዳ የማትሄድ" አሉኝ። እኔም አይ ሂጄ ቤተከርስቲያን ቁሜ ማስቀደስ አለብኝ ቀኗ ግንቦት ልደታ ናት አልኳቸውና ለመሄድ ተነሳሁ።

እነርሱም እስከ ባቡር ጣቢያው ድረስ ሸኙኝ። ከዚያም ስጓዝ አድሬ ሲነጋ ደረስኩ። ያ ነገር ከትክሻዬ እንደተቀመጠ  አልለቀቀኝም እንደከበደኝ ነው።  ቤተክርስቲያን ገባሁና ተሳለምኩ ካህናቱም መቅደስ ውስጥ ገብተዋል ቅዳሴም ተጀምሯል ሕዝቡም ቁሞ በማስቀደስ ላይ ነው። ከዚያ መሃል አንድ መነኩሴ ጥቁር ቀሚስ እንደለበሰ ከውጭ ቁመዋል ማለትም ቅዳሴ አልገባም። ከሕዝቡ ጋር ቁሞ ያስቀድሳል። ያለወትሯቸው ጳጳሱ በእርሱ ፋንታ ገብተው ይቀድሳሉ ማለትም በዚያ መነኩሴ ምትክ። የዚያን ቀን ገብተው ሲቀድሱ ጳጳሱም ያልተለመደ ነበር። ምክንያቱም ይቅርና መቅደስ ውስጥ ገብተው ሊቀድሱ በዕለተ ሰንበት እና በታላላቅ በዓላቶች ቀን እንኳ መጥተው ኪዳን አያደርሱም ነበር። ከሰዎች

አንደሰማሁት ከሆነ፤ ብዙ ሰዎችም አይወዷቸውም ለጵጵስናቸውም ብዙ ክብር አይሰጧቸውም ይሉ ነበር። የቅዳሴው ሥርዓት ተጠናቆ ቁርባን አቁርበው ሕዝቡም ተቀብሎ ካበቃ በኋላ ቦታ ቦታውን ያዘ። እኔም የራሴን ጸሎት አድርሼ እንደ ሕዝቡ አብሬ ቁሜአለሁ፣ ነገሩ እንደ ከበደኝ ነው አለቀቀኝም። ልክ ካህናት ተመልሰው ወደቅድስተ ቅዱሳኑ ሲገቡ ያ ውጭ ቁሞ የነበረው መነኩሴ ብድግ አለና፣ ለሕዝቡ ሲናገር “አቡነ ዮሐንስ በስልጣናቸው ተመክተው እኔ መቅደስ ውስጥ ገብቼ እንዳልቀድስና መስቀል እንዳላሳልም ከለከሉኝ ካገልግሎትም አገዱኝ” በማለት ተናገረ። ሕዝቡም በነገሩ ግራ ተጋብቶ እንዳለ፣ አቡኑ ትልቁን መስቀል ይዘው ብቅ አሉ። ለሕዝቡም ሲያሳልሙ በቅርቡ የነበሩ ትላልቅ ሰዎች ቀርበው ሲሳለሙ መነኩሴውም ለመሳለም ቀረብ ሲል ጳጳሱ መስቀሉን ከፊቱ ዞር አደርገው ለሚቀጥለው ሰው አሳለሙ። ይህን ያየ ምእመናን ጋማሹ ያለቅሳል፣ ግማሹ አንገቱን ደፍቶ ያዝናል፣ ግማሹ አጋጩን በእጁ መዳፍ አስደግፎ በመገረም ያያል። ሁኔታው በጣም የሚያስገርምና የሚያስደነግጥ ስለነበር፤ እኔም ያን ነገር በዓይኔ ሳይ እንደ ሕዝቡ አብሬ አዘንኩ። ሁሉም ነገር ተጠናቀቀና ምእመናኑ ወደ ጸበል ጠዲቅ ቦታ ሂደው ተቀመጡ። እኔም ሸክሜን ገና አላራገፍኩም እንደተጫንኩ ነኝ። ሄድኩና ከሁለቱ መነኮሳት ፊት ተንበርክኬ ፍቀዱልኝ ትንሽ የማደርሳት መልእክት አለችኝ፣ ነገር ግን ለእናንተ ላስተምር ወይም ላስረዳ ስልጣን የለኝም፣ ሁኖም ግን የታዘዝኩትን ለማድረስ ወይም ግዳጀን ለመፈጸም ነው አልኳቸውና፤ በዚች ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የሚያሳየው ተአምር አለ ስለዚህ ፈጥናችሁ ሰላም ፍጠሩ። ከእኔ ላይ ክንፍ ያለው ቀይ ደሮ የሚመስል ከትከሻዬ ላይ ተቀምጦ እያበረረ ያመጣኝ ያየሁትን እንድናገርና ይህነንም በዓኔ ሊያሳየኝ ነው። አሁንም ፍቀዱሉኝ በተለይ ካህናት ለብቻ ሁኑና ልናገር አልኳቸው። እነርሱም መለሰው “መጀመሪያ ለጳጳሱ ንገር” አሉኝ ። የት አሉ ብዬ ስጠይቅ አንዱ ዲያቆን “ከቤተልሔም ውስጥ ነው ያሉ በነገሩ ሽምግልና ይዘዋቸው ከሰበካ ጉባኤው ጋርና ከታላላቅ ሰዎች ጋር” ቁመዋል አለ። እኔም ሸክሙ ስለከበደኝ አልቻልኩም እየፈራሁና እየተነቀጠቀጥኩ ሰውነቴም እየራደ ሄድኩና ይን ጉዳይ ስግልጽላቸው፣ እርሳቸውም ንቀትን አሳዩና “አሁን ሥራ አለኝ እቆያለሁ”አሉ። እኔም እጠብቅዎት አለሁ አልኩና ከውጭ ወጥቼ ተቀመጥኩ።  መከፈልትም አልቀመስኩም ዕዳዬን ሳልላቀቅ ብዬ ከውጭ ተቀምጬ ከካህናቱ ጋር ብዙ ሰዓት ጠበቅሁ፣ ሊወጡ አልቻሉም። ተነሳሁና ውስጥ ገብቼ አንዱን ዲያቆን የታሉ ጳጳሱ? ብዬ ስጠይቅ “እንዴ እርሳቸውማ ከወጡ ቆይተዋል በአንደኛው በራፍ ነው ወጥተው የሄዱ “ሲለኝ። ወደ መቅደሱ ፊቴን ዞር አድርጌ አንቺ እመቤቴ ፍረጂ ድካሜንም ተመልከች  ስል፣ ከትከሻዬ የነበረው ሲወርድ ታወቀኝ፣ ወዲያዉኑ ጤነኛ ሆንኩ። ከዚህ በኋላ ሁለቱን መነኮሳት ሦስት ዲያቆናት፤ ሌሎችም ሳሄዱ የቀሩ የሰንበት ተማሪዎችን እና አንዳድ ምእመናን ነበሩ። ለእነርሱ በዚች ቤተክርስቲያን ውስጥ የምታዩት ተአምር አለ ተጠንቀቁ ስለ ራሳችሁ እንጂ ስለ እሷ አታስቡ እሷ እናንተን ትጠብቃለች እንጂ እናንተ እሷን አትጠበቋትም ብዬ ነገሩን በዚህ ዘጋሁት።

ከዚያ እኒያ ባለፈው ያየሁትን ሕልም የነገርኳቸው መነኩሴ ብድግ አሉና “እኒህ ሰውዬ ባህታዊ ናቸው የሚሉትን ስሟቸው” አሉና ቁመው በመድረክ ተናገሩ። አንዳድ ሰዎችም እየመጡ ስለ ቤተክርስቲያንና ስለራሳቸው ችግር እንድጸልይላቸው ጠየቁኝ።  እኔም መልሼ ዘመዶቼ እኔ ከሰው ያነስኩኝ በኃጢአት የተዘፈቅሁኝ ጌታዬን የበደልኩና የአስቀየምኩ ሰውነኝ። ለእኔ ከምትነግሩኝ ይልቅ ለካህናት እየተናገራችሁ ንስሐ ግቡ ምን አልባት እኔ የምመክራችሁ ነገር ቢኖር ወደ ቤተክርስቲያን ስትመጡ ከቂምና ከበቀል ከጥላቻ እርቃችሁ፣ ፍቅርንና ሰላምን ይዛችሁ ነው መምጣት ያለባችሁ፤ቤተ-ክርስቲያንንም በንጽህና ያዟት ለእናንተ ምህረት ታሰጣለች አልኳቸው። **ነገር ግን እርሱ በእኔ ላይ አድሮ ክብሩን መግለጽ ስለፈለገ አልናቀኝም። ሐዋርያው ጳውሎስ ባለማወቅ ቢከደውና ቢበድለው፣ እርሱ ግን መልሶ የእርሱ አገልጋይ አድርጎታል።  እኔንም ስለወደደኝ አመሰግነዋለሁ፣ አልኳቸውና ነገሩ በዚህ ተፈጸመ።** በሳምንቱ በሚቀጥለው እሁድ ጳጳሱ ተሸምግለው ለመነኩሴው መስቀል እንዲያሳልሙት ተደርጎ አሁንም የቅዳሴው ሥርዓት ተጠናቅቆ ለመእመናኑ አቡኑ መስቀል ሲያሳልሙ ለመነኩሴውም ሂደው ሊያሳልሙት ሲሉ፤ እርሱም በፈንታው መስቀሉን ገፈተረው፤ እንደገና ሕዝቡ ተንጫጫ፣ መተረማመሱም ቀጠለ፤ ችግሩ በቀላሉ ሊፈታ አልቻለም። ካህናቱም ከሁለት ጎራ ተከፈሉና አድማው ቀጠለ፤ መነኩሴውም ሕዝቡ ሰልፍ እንዲወጣ ቅሰቀሳ ጀመረ ነገሩም ሃይማኖት ሳይሆን ፖለቲካ ሆኖ ተገኘ። ካህናቱ አቡኑን ሲደግፉ አብሮ ገንዘቡን የበላ ደግሞ መነኩሴውን ደገፈ። መነኩሴውም ቢጠየቅ አላውቅም ሂዱና ክሰሱኝ አለ። እርሱም በሚመካው ተመክቶአል የአባ ጳውሎስ

ዘመድ ነው። የቤተክርስቲያን ገንዘብ ተዘርፎ ተወስዶአል። ሕዝቡም ተጨንቆ የሚያደርገው ግራ ተጋብቶአል። ሰበካ ጉባኤው በበኩሉ ከመነኩሴው ጋር ስለወነ ሕዝቡ ችግሩን በቀላሉ መፍታት ስላልቻለ በአስቸኳይ ወደ ቅ/ሲኖዶስ አመለከተ። ከአዲስ አበባ በአስቸኳይ ዶክተር ገሪማ ተልከው መጡ። እርሳቸውም ሲመጡ ያልተደረገ ነገር የለም። ሁሉም ፈርተዋል በክፍለ ሀገር ያሉ ካህናት ሳይቀር በንጉሡ ዘመን ለባለ ስልጣን ሲደረግ እንደነበረው እጅ መንሻ ይዘው መጥተዋል። መነኩሴውም የሰጠው ጉቦ ይህ ነው አይባልም። እራሴ ተሸክሜ ስለወሰድኩና በዓይኔም ስላየሁ ነው። አንድ ቀን ጸሎት ላደርስ ቤተ ክርስቲያን ሂጄ፣ ውስጥ አንዳልገባ በራፉ ዝግ ነው። ቤተ-ክርስቲያኗን የሚከፍቱት መነኩሴ ታመው ሐኪም ቤት ሂደዋል። ያ መነኩሴም መዝረፍ እንጂ ከፍቶ አያገለግልም። ከዚያም ውጭ ሁኜ ጸሎት ካደረስኩ በኋላ ደክሞኝ ከበራፉ ቁጭ እንዳልኩ እንቅልፍ ወሰደኝ።

ያ መነኩሴ መጣና በያዘው በትር ጎኔን ነካ ነካ ሲያደርገኝ ፈክሬ ተነሳሁ “እንዴ እስከ አሁን ተኝተዋል? ተኝተው አላደሩም እንዴ”? አለኝ። እኔም አይ ትንሽ ጸሎት ቁሜ ስላደርስኩ ደክሞኝ ነው ስለው። “አይ ይህ እኮ ለእናንተ አልተፈቀደም አለና ቀጠል አድርጎ በእኔ ሲመስልብኝ አንድ ወታደር ሲሰለጥን ጥይት እንዴት እንደሚተኩስና ጠላትን እንዴት እንደሚማርክ ነው መማር ያለበት እንጂ ይህ ዓይነቱ ግን ለናንተ አይደለም የተሰጣችሁ” አለና በድፍረት ተናገረ። እንግዲህ ወገኖቼ ይቅርታ አደርጉልኝና እንዲህ ያለው ሰው በእውነት የቤተክርስቲያን አገልጋይ መነኩሴ ነው፤ ተብሎ ሊታመን ይቻላልን? እንዲህማ ያለ ሰው ቢሆን ኑሮ እንዲህ ያለ ቃል ባልተናገረ ነበር። ቤተክርስቲያን ያገለግላል ሕዝቡን ያስተመራል ከነጣቂ ተኩላ ይጠብቃል ተብሎ ታምኖበት ተልኮ እንዲህ ያለ ሥራ ሲሠራ አያስገርምም? ይህ ሰው ስለ ውትድርና ትምህርት እንዴት ሊናገር ቻለ? ለማስመሰል ነው ቆብ የጫነው ማለት ነው ወይስ ለምን? በሌላም በኩል መልሶ ሕዝቡን ለሰልፍ እንዲወጣ ያካሂዳል እንደ ዘመኑ የሀገራችን ፖለቲካ ሆኔታ ሕዝቡን ለመከፋፈል መነኩሴው ሊጠቀመበት የቀየሰው ዘዴ ነበር። በዚሁም ላይ ሰውዬው የበተክርስቲያን አገልጋይ ሳይሆን የፖለቲካ ሰባኪና ተወካይ መሆኑን የሚያመለክት ነበር። እኔም ነገሩን ሳስበው የሌላ መሆኑን ስለአወቅሁና ስለተረዳሁ እሷ እመቤቴ ድንግል ማርያም ትፍረድብህ ብዬ ዝም አልኩ። ከላይ የጠቀስኩላችሁን አባባል (ስለውትድርና) ከነገረኝ በኋላ “ወደ ሱቅ እንሂድ አለኝና አንሶላውን ፒጃማውን ሌላውንም የልብስ ዓይነት ሁሉ ከዚያው በገዛው ትልቅ ሻንጣ” አስገባው። በተጨማሪም የወይራ ዘይት በካርቶን ተገዛ። እኔም ይህ ሁሉ ለምንድርነው? አልኩት። ወደ ሀገር ቤት ልሰደው ነው አለኝ። ነገር ግን ለጉቦ ነበር፣ያ ሁሉ የተገዛው። ምክንያቱም ና ተገናኛቸው ብሎ ወስዶኝ ለዶክተር ገሪማ ሲያበረክት ስላየሁ ነው። ዶክቶሩም ከሰውነታቸው ውፍረት የተነሳ ሊንቀሳቀሱ ስለአልቻሉ ከዚያው እንደተቀመጡ ዘይቱን ከፍተው ሲያዩት በጠርሙስ ነበር።

በጣም ተቆጡ “እንዴት ይሄማ ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርስ ይሰበር የለም ወይ? መልስና የቆረቆሮውን ገዝተህ አምጣ” አሉና፤ የአንዱን ከክፍለ ሀገር የመጣ ካህን ስም ጠርተው እርሱም እንደዚህ ያለ ነው ያመጣ” ብለው አስመለሱት። ከዚያ በኋላ ነው ጉቦ መሆኑን ያወቅሁት። ዶክተር አቡነ ገሪማም የእግዚአብሔር ጸጋ እንደተለያቸውና ለነፍሳቸው የአደሩ ሳይሆንስ ለሥጋቸው ያደሩ መሆኑን ተረዳሁ። እርሳቸውም እንኳን ሊያስታርቁ ይቅርና “እያንዳንድህ ቤተ-ክርስቲያን ሳትልክህ ከዚህ መጥተህ ትረብሻለህ” ብለው ዲያቆናቱን መአት አወረዱባቸው። ነገሩን አባብሰውት ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው ሄዱ። ብጥብጡ ቀጥሏል ሕዝቡም ተደናግጧል በዚች ቤተ-ክርስቲያን ምን ሊፈጠር ይሆን በማለት እጅግ ተጨንቋል። እኔም በዚች ቤተ-ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሥራ ታያላችሁ አትደናገጡ። እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አትፍሩ፣ እያልኩ ምእመናኑን ሳበረታታና በንጹሕ ልቦና እንዲጸልዩ ሳሳስባቸው ቆየሁ። ከዚያውም ሁኜ ጧትና ማታ እየሄድኩ ጸሎት ሳደርስ፣ አንድ ቀን እሁድ ጳጳሱ በሌሉበት ሰዓት መነኩሴው ይመጣና መቅደስ ውስጥ ገብቶ በጠበጠው። የዕለቱን ምስባክ ዲያቁኑ ቆሞ ሲሰብክ “ይህ አይደለም የሚሰበክ”አለና፤ ዲያቆኑ ያለተዘጋጀበትን ይህን ስበክ አለው። ዲያቆኑም ለጊዜው በመጽሐፍ እየተመራ ሰበከ። ግን መነኩሴው እንዲህ በማድረጉ ዲያቆኑ ተናደደ። መነኩሴውም በጉቦው ተማምኗል፤ከዚያ ቦታ እንደማይነቀል ዶክቶሩ ገሪማ በፊርማ አረጋግጠውለታል።

ከዚህም የተነሳ ካህናቱንም ሆነ ሕዝቡን በንቀት ነበር፣ የሚመለከተው። እግዚአብሔር የሚፈርድበት አልመሰለውም ነበር። አቡነ ዮሐንስ ለናካቴው ፈጽሞ መቅደስ ውስጥ እንዳይገባ አግደውት ነበር። በዚያን ቀን ግን የእርሳቸውን አለመኖር አይቶ ነው እንደዛ ሊበጠብጥ የቻለው። በዚህ ሁኔታ ቅዳሴው ከተጠናቀቀ በኋላ፤ እኒያ የሰው መውደድ ያላቸው ደግ መነኩሴ (ሕልም ያየሁላቸው) በመንፈስ ተምርተው እርግማኑን አወረዱት ለሕዝቡም እንዲህ በማለት ቁመው ተናገሩ። "የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ወገኖቼ በሙሉ፣ በእግዚአብሔር አንድ እንደ ሆን ሁሉ፥ አሁንም አንድ ነን፣ ይህን ሊለያየን የፈለገውን እግዚአብሔር ይለየው ፤ ይህን ሊያነጣጥለን የፈለገውን መድኃኔ ዓለም ይነጥለው፤ እኛ በሰላምና በፍቅር የምንኖርባትን ቤተክርስቲያን ሊያፈርሷት ስለተነሱ እርሱ ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍርዱን ይስጣቸው" አሉና በጸሎት ዘጉት። ከዚያም በኋላ ያ በጥባጭ በተራው አስተምራለሁ ብሎ ሲነሳ ሕዝቡ እንዳለ ግልብጥ ብሎ ወጣ። እርሱም "ኧረ ቆዩ አድምጡኝ" ቢል ሰሚ አጣና ውረደቱን ተከናነበ። እግዚአብሔር ሲያጋልጥ እንደዚህ ነው። በሳምንቱ ጳጳሱ የሆነውን ሰምተው ሲመጡ የሰኔ ሚካኤል ዕለት አሁንም ሊጣሉ ነው ብሎ፤ ሕዝቡ ሲጨነቅ ሳለ፤ ያ መነኩሴ ያቡነ ዮሐንስን መምጣት ሲሰማ የሚካኤልን ጸበል እባርካለሁ ብሎ ወደ ክፍለ ሀገር ሄደ። ከሄደም በኋላ መጀመሪያ ለሕዝቡ በጸሎት ባርኮ ሳይሰጥ ሰው በልቶ ከጠገበ፤ ጠጥቶ ከሰከረ በኋላ ትምርት ላስተምር ብሎ ሲነሳ። ያ ጎረምሳ ሁሉ ሕይወቱን በዳንስ እያዝናና ሳለ ወነጌልን ሊሰብክ አቁሙ ቢላቸው። አንዱ በመጠጥ የተመረዘ ጎረምሳ "ዝም በል አንተ ሌባ አሁን ከኛ ጋር አብረህ በልተህ ከጠገብክና ጠጥተህ ከሰከርክ በኋላ ላስተምር ትላለህ ቅድም የት ነበርክ" ብሎ አሳፈረው ተብሎ ተነገረ። የሰማውም ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ አደቀ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ሲጣላ ነው፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተአምር ስሠራና እርሷንም በዓልሽ በጥሩ ሁኔታ ይከበር ሲላት፣ እኒህን የቤተክርስቲያን ነቀርሳዎች በአስቸኳይ ከቦታው እንዲነሱ አደረገች። ቅ/ሲኖዶስ ከአዲስ አበባ ለአቡነ ዮሐንስና ለዚያ መነኩሴ ለአባ ገ/እግዚአብሔር ለሁለቱም የአየር ትኬት ቆርጦ ላከና ወዳገር እንዲመለሱ አደረገ። አቡነ ዮሐንስም በዕለተ ሰንበት ለካህናቱም፤ለምእመናኑም ቁመው ከግዲህ በዓይነ ሥጋ አንገናኝም ብለው ተሰናበቱ፤ መነኩሴው ግን አፍሮና ደንግጦ የሰራው ሥራ አሳፍሮት፤ሳይታይ በዚያው አድርጎ ተሸኘ። ጳጳሱም ታይቶአቸው ኑሮ ነው መሰል እንዳሉት አገር ቤት እንደሄዱ ብዙም ሳይቆዩ ከዚች ዓለም በሞት ተለዩ። ቤተ-ክርስቲያኒቱም ከነበረባት ችግር ጸዳች፣ ተአምሯንም አሳየች። ሕዝቡም ችግር ፈጣሪዎቹ ከቦታው ሲነሱለት ደስታ ተሰማው። የሰኔ ማርያም ዕለትም በዓሉ በጥሩ ሁኔታ ተከብሮ አለፈ። ለሕዝቡም መልሶ ሰላም ሰፈነለት ከቦታው ርቀውና ሸሽተው የነበሩ ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፤ ድንግልንም በሥራዋ እያደነቁ፤ ወደ ቤተ-ክርስቲያናቸው ተመለሱ። የሮማ ቤተ-ክርስቲያን ልጆቿን መልሳ በማሰባሰቧና ምሕረትም በመውረዱ እርሷንም ከበታኝ ተኩላዎች፤ ከአፍራሽ ወንበዴዎች፤ ካሉባልታ ነዚዎች በመጠበቅዋ፤ ትልቅ አድናቆትና ክብርን አግኝታለች። በቤተ- ክርስያንኒቱ ውስጥ ብዙ የተሠራ ስህተት ነበር፤ ያን ግን የቤተ-ክርስቲያናችንና የንጹሓን ካህናትን ስም በአናዳንድ ሕገ ውጥ ሰዎች ምክንያት እንዲነቀፍብኝ አልፈለግምና ስለዚህ አልፌውአለሁ። ባጠቃላይ እግዚአብሔር ፍርዱን ሰጥቷል ለእርሱ ምስጋና ይግባው።በሮማ ቤተ-ክርስቲያን ያሳየውን ኃይሉንና ተአምሩን በውጭም ሆነ በሀገር ቤት ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ቢያሳይ ወይም ቢሠራ፣ የቤተ-ክርስቲያን ተኩላዎች ተመንጥረው ወይም በነው በጠፉ። ቤተ-ክርስቲያንም ትከበር እንጂ ባልተደፈረችም ነበር። ሕዝቡም ካለበት መከራና ችግር ይላቀቅና ምሕረትን፤ ፍቅርን ጤናን፤ ብልጽግናንና ሀብትን ያገኛል፤ ሀግርም ሰላምን ታገኛለች እንደ ድሮውም ትሆን ነበር።ለሁሉም ነገር እግዚአብሔር ለሀገራችን ደህንነትን ለህዝባችን ስላምን ይስጥልን። ሁሉም በእርሱ እጅ ነውና የሚሳነው ነገር የለም።

## <u>ራዕይ በእንግላንድ፤</u>
## የአቡነ አረጋዊ ዕለትታህሳስ፡<u>፲፬</u>፡ቀን፡<u>፲፱</u> <u>፻፺፯</u> (14/1997ዓ/ም)

በዚያን ሌሊት ከበረሃ ወጥቶ ብዙ ሕዝብ ከትልቅ ተራራ ተሰብስቦ አየሁት። መጀመሪያ ከበረሃው ወደ ተራራው ሲወጣ ጅብ ሕዝቡን ሊበላው መንገዱን ዘግቶ አላሳልፍ ብሎት፤ እኔ እረጅም ዘንግ ይዤ

በግራ ጎን ጅቡን እየተከላከልኩ ሕዝቡ በቀኝ ጎን ተበታትኖ መንገድ እየፈለገ በጭንቅ ወደ ተራራው ወጥቶ በአንድ ላይ ተሰበሰበ። ከዚያም ትልቅ ድግስ ተደግሶ ሕዝቡ ባርኮ የሚሰጠው ይፈልጋል፤ ሁለት ከሙታን የተነሱ ሰዎች በድንገት መጥተው ስለ ሀገርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ቁመው ደብዳቤ ያነባሉ። የአንደኛውን ስም "ዘለቀ የሁለተኛው ስም ሲሳይ ይባላል ብሎ እራሱ ዘለቀ የሚባለው ሰውዬ የኋደኛውን ስም ጨምሮ አስተዋወቀ። የመጀመሪያውን ደብዳቤ ያነበበው ዘለቀ የሚባለው ሲሆን ሁለተኛውን ደብዳቤ የሚያነበው ደግሞ ሲሳይ የሚባለው ነው እርሱ ያነብላችኋል" ብሎ ተናገረ። ነገር ግን ሁለተኛው ሰውዬ ደብዳቤውን አላነበበውም፣ በእጁ እንደያዘው ነው የቀረ። ዘለቀ የሚባለው መልኩ በጣም ቀይ ነው፣ የራሱም ጸጉር በጣም ነጭ ነው፣ መልሶም የጠመጠመው እሻሽ ትልቅ ነው። ሲሳይ የሚባለው ግን መልኩ በጣም ጥቁር ነው፣ የራሱ ጸጉር ግን በጣም ነጭ ነው፣ እሻሽ ግን አልጠመጠመም ቁመቱ አጭር ነው። የመጀመሪያው ዘለቀ የሚባለው "ለአሁኑ እኛ እናሰማችሁአለን" ብሎ ለሚቀጥለው ሌላ እንዳለ ጠቁሞ ነገሩን ሳይገልጸው ዘጋው፣ ከዚያም ተሠወሩ። ነገሩ በእንዲህ እንዳለ ድግሱን ለሕዝቡ ባርኮ የሚሰጠው አጥቶ በመጨነቅ ላይ ሳለ፣ በድንገት አንድ የማውቀው የቤተ ክርስቲያን መምሕር እርሱን ተመስሎ ከሕዝቡ መካከል ብቅ አለ። የለበሰው ካባና ከራሱ ላይ የጠመጠመው ጥምጥም የተለየ ነው። ያን የለበሰውን ካባና ከራሱ ላይ ያስቀመጠውን ከጳጳስም ሆነ ከነጉሥ ከዚያ ቀደም ያደረገ ማንም የለም ፤በጣም የተለየ እንደወርቅ የሚያንጸባርቅ ሲሆን ርዝመቱ እስከ እግሩ ጣት የሚጎተት ንጣቱም በጣም ነጭ ነው።

*ከዚያ ለሕዝቡ በትልቅ ሼንኬሎ ውሃ ሞልቶ ሲያበቃ "አጠምቀከ በአብ፣ አጠምቀከ በወልድ፣ አጠምቀከ በመንፈስቅዱስ" እያለ ውሃውን ከደገመበት በኋላ ሕዝቡን በሙሉ እየዘረ እረጨው። የተረፈውን ውሃ አንስቶ እስከነ ሼንኬሎው ከለበሰው ልብስ በላይ በራሱ ላይ ደፋው። <u>ከዚያም በመቀጠል"ኵኑ፤ፍቱሐነ ፤ወንጹሐነ፤ይረስየነ ፤ድልዋነ ፤ለመንግሥተ ሰማያት" እያለ ሕዝቡን፤በመስቀል ፤ባረከው</u>። ደግሞም እንጀራውንና ጠላውን ባርኮ ቆርሶ ለሕዝቡ ተከፋፍሎ እንዲበላው ሰጠው። እርሱ ግን አብሮ ከሕዝቡ ጋር አልተቀመጠም ያን ካደረገ በኋላ ተሠወረ። ድግሱን ግን ኤርትራውያንም ባንድ ላይ አብረው ነው ያዘጋጁት ወጣቶችም አብረው ከኢትዮጵውያን ወጣቶች ጋር በማሳለፍና በማስተናገድ ያገለግሉ ነበር። ሕዝቡም በደረጃ በደረጃው እንዲቀመጥ ተደረገና በመስሪያ እየሆነ ምግቡን ተመግቦ በሰላም ተለያየ።*

## <u>ራዕይ በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤</u>
## የኪዳነ ምህረት ዕለት፤ጥር፡፲፮፡ቀን፡፲፱ ፻፺፯ (16/1997ዓ/ም)

በዚያች ሌሊት አንድ ቁመቱ ረጅም ሰው መልኩ ጠይም ውበቱ በጣም የሚያምር ጸጉሩ ሙሉ ዓይኑ በጣም የሚፍለቀለቅ እንደ በግ ዓይን የፈጠጠ ፤አፍንጫው ሰልካካ የለበሰውም ልብስ በጣም ነጭ ቅጥል የሌለበት፤ አንድ ወጥ የሆነ ቀሚስ እስከ እግር ጣቱ የሚጎት፤ በለንደን ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ቁሞ በቁጣ ከመቅደስ የነበሩትን ካህናትና ዲያቆናት፤ እንዲሁም በዚያ በኩል የቆሙትን በሙሉ በቁጣ ቃል ተናግሮ ሲያስወጣቸው አየሁ። ሲናገርም ከቁጣው የተነሳ ሌላ ድምጽ አብሮ ያስተጋባል። ሁሉንም ወደ ውጭ ካስወጣቸው በኋላ ይጠይቃቸው ጀመር። አንድ ግን ሊመልስለት የቻለ ሰው አልተገኘም (የለም)። ከዚያም በመቀጠል አንድ የቤተ-ክርስቲያን መምሕር ስም ጠርቶ የት አለ? ብሎ ጠየቀ "ጠብቅ ያልኩትን እረሳ" ብሎ አስፈለገው። እርሱ ግን አልተገኘም፣ ከዚያ አንድ ዲያቆን ተነስቶ "የታክሲውን ማን ይከፍልለታል ሲል" መለሰለት። ሰውዬውም በጣም በመበሳጨት አዘነ። እኔ በሩቅ ሁኜ ነው የምመለከተው። ስሙ ማን ይሆን የሚባል እያልኩ ሳለ? አንድ ከጎኔ ሆኖ "ስሙ ታምራት ነው የሚባል" አለኝ። እኔ ግን ከጎኔ ያለውን ሰውዬ አላየሁትም፤ ዘወር ብዬ ሳይ የለም ድምጽ ብቻ ነው የሰማሁት አይታይም። ሰውዬው ግን ከወንዶችም ከሴቶችም የትላልቅ ሰዎችን ስም እየጠራ እኒህን ሁሉ ጠብቅ እያልኩ ጠፋ እያለ ያዝናል። መምሕሩም ተፈልጎ ሊገኝ አልቻለም። በመጨረሻ ግን ሰውዬው በቁጣ እየተናገረ ተሠወረ ። የቤተ -ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ካህናት በሙሉ እንደ ቆሙ ቀሩ ተመለሰው ወደውስጥ አልገቡም።

## ራዕይ በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤
## የቅዱስ አማኑኤል ዕለት፤ጥር፡፳፰፡ቀን፡፲፱፻፺፯ (28/1997፤ዓ/ም)

በዚያን ሌሊት ያየሁት ሁለት ሰዎች በፈረስ ሁነው ጦር በእጃቸው ጨብጠው ከሀገር ተነስተው ሲመጡ አየኋቸው። ይችን ቤተ-ክርስቲያን ሊያጠፏት ነው፤ ቁጣው እንደ እሳት ነደደ እያሉ ይናገራሉ። ከዚያም በተጨማሪ ሁለት ደበሎ የለበሱ ሰዎች በድንገት ይመጡና ከሰዎቹ ጋር ሲቀላቀሉ አየሁ፤ ማለትም ከባለ ፈረሶቹ ጋር። ሁሉም ግን ከኢትዮጵያ ነው የመጡት። ከዚያ አንደኛው ባለፈረስ ጦሩን እንደያዘ "ከዚህ ሕልም የሚያይ የለም?" ብሎ ለእነዚያ ለሁለቱ ደበሎ ለለበሱት ሰዎች ይጠይቃቸዋል። አንደኛው ብድግ አድርጎ ወደ እኔ ጣቱን ቀስሮ እያሳየ "ይህ ሰው ያያል" ሲል መለሰለት። እኔም ብድግ ብዬ ኧረ ጌታዬ ከአሁን በፊት ያየሁትንም አልተናገርኩ ይቅርታ ይደረግልኝ አልኩት። እንደዚህም ስል ከፊቴ ሁሉም ሰዎች ተሰወሩ፤ ላያቸው አልቻልኩም።

## አሁንም ራዕይ በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤
## የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት፤የካቲት፡፳፫፡ቀን፡፲፱ ፻፺፯ (23/1997፡ዓ/ም)

በዚሁ ሌሊት ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ማለትም ከለንደን ቅድስት ማርያም ውጭ ቁሜ ለሚመጣው ሕዝብ ሁሉ ይችን ቤተ -ክርስቲያን ረገጣችኋት አረከሳችኋት እርሷም ታረክሳችሁአለች እያልኩ በኃይል ቃል እናገራለሁ። ከዚያ አንድ ወጣት ዲያቆን ይመጣና ወደ ቤተ- ክርስቲያን ሊገባ ሲል አንተ ቆሻሻ ታቆሽሻታለህ? አሁን ይፈርድብሀል ብዬ በኃይል ቃል እናገረዋለሁ። እርሱም መልሶ "እኔ ምን አደረግሁ እነርሱ ናቸው ሚስቴን እንድትባልግ ያደረጓት" እያለ በካህናቱ ላይ እጁን ቀስሮ ያመለክታል። ከዚያም እኔ ይህነን እያዩ የቤተ ክርስቲያኗ (ስም አልጠራም) አላፊ ዝም አሉ? ስል፣ እርሳቸውም ማለትም ካህኑ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኑረው ምንም መስኮት በሌለው በግድግዳ በደቡብ በኩል አድረገው ሾልከው ሲሄዱ አየኋቸው። ሕዝቡም ወደ ውስጥ አልገባም ቅዳሴም አልተቀደሰም ቤተ- ክርስቲያኗም ጭር ብላለች፤ ሁሉም ሰው በመደናገጥና በመገረም እያዘነ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

## ራዕይ፤ በእንግላንድ፤
## የቅድስት ኪዳነ ምህረት ዕለት፤ጥር፡፲፮፡ቀን፡፲፱፻፺፰ (16/1998፡ዓ/ም)

በዚች ሌሊት ያየሁት፤ ከትልቅ ወንዝ ወርጄ ፏፏቴው በጣም የሚጮህ ከመካከሉ ላይ ትልቅ ድንጋይ አለ ፣ከዚያ ላይ እኔ ከባሕሩ ገብቼ ከድንጋዩ ተቀምቼ ከባሕሩ ውሃ እየጨለፍኩ ሰውነቴን በሳሙና ታጥቤ ወጣሁ። ከዚያም ወጥቼ ረጅም መንገድ ከሄድኩ በኋላ በሰውነቴ ላይ የሳሙናው አረፋ አለ ቆሻሻው ከሰውነቴ በሙሉ አልጸዳም ብየ ተመለስኩ። ተመልሼ ስመጣ በባሕሩ ዳር ብዙ ሰው ወንዱም ሴቱም ተቀምጦ አገኘሁ፤ ባሕሩም በተራራ መካከል አድርጎ ነው የሚሄደው። ከትልቁ ተራራ ላይ እረጅም ጥቁር የውሃ ቱቦ የእሳት አደጋ ማጥፊያ የመሰለ ዙሪያውን ተጠምጥሞ ጫፉን አንድ ጥቁር ሰው ይዞት ከባሕሩ ዳር ተቀምጧል። ከዚያ መካከል እኔ ከባሕሩ ዳር ልታጠብ ደረስኩ፣ ሁሉ ሰው ግን አይታጠብም ዝም ብሎ ተቀምጦ ነው ያለው። ከዚያም ለዚያ ጥቁር ሰው አንተ ነህ ይሄነን ይዘህ የመጣህ? ብዬ በቁጣ ቃል ተናግሬ አልፌ ከባሕሩ ገብቼ ልታጠብ ስል፤ በድንገት ያ ቱቦ ወደ እባብነት ይቀየርና እኔን ሊውጠኝ አፉን ከፍቶ ወደ ላይ ተነሳ። ከዚያ መካከል አንድ የማውቀው የቤተ-ክርስቲያን መምሕር እርሱን በጫንቃዬ አዝዬ ወደላይ መጠቅኹ ግን ክንፍ የለኝም እባቡም ሊደርስብኝ አልቻለም መምሕሩ ግን ከዚያ ቦታ አልነበረም በጫንቃዬ ታዝሎ ሲሄድ ብቻ ነው የሚታወቀኝ። መምሕሩን እንዳዘልኩ በዚያ ተራራ ዱር ለዱር ስዞር ሰውዬውን ውረድ አሁን በዚህ ውስጥ ከእኔ ጋር መሄድ አትችልም እንጨት ይዞ ያስቀራሃል ስለው "አልወረድም ከአንተ ጋር ነው የምሄደው"ይላል። እኔም እርሱን አዝዬ በዚያ ውስጥ መብረር አልቻልኩም ወደ መሬት እወርድና የእርሱን እጅ ይዤ በዚያ ተራራ እየዞርኩ ሳለሁ ባቡር የመሰለ በበረሃ አድረጎ ሲመጣ አየን። እኛም ቁመን በመገረም ያለ መንገድ በተራራ ላይ ይወጣል ብለን ስንነጋገር፣ እርሱ የሚመጣው ያን ቱቦ ለመጠቅለል ነበር፣ ትቦውም ከተራራው ላይ ጫፉ ተጋድሟል። ልክ ባቡሩ እኛ ከቆምነበት ሲደርስ

አሁንም ያ ትቦ ወደ እባብነት ይቀየርና አፉን ከፍቶ እኔን ሊውጠኝ ተነሳ፣ እንደ ኮብራ ራሱን እያሽከረከረ በዚያ ተራራ ላይ ያሮጠኝ ጀመር። ከሰውዬው ነጥሎ ልክ ደርሶ ሊይዘኝ ሲል፤ **<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣ እያልኩ እደግማለሁ እጸልያለሁ።</u>** ደርሶ እግሬን ጠልፎ ሊጥለኝ ሲል ወደላይ አሁንም ተነጠቅሁ። እባቡም እጅግ በጣም ራሱን ወደ ላይ አቆመ ሊይዘኝ ግን አልቻለም ። ከዚያም ወደ ቤተ- ክርስቲያን ሄድኩ፣ ወጣት የነበርኩት በአንዴ ሽመገልኩና ወገቤ ጎብጦ ምርኩዝ ይዤ ገባሁ። ስገባ ከቤተ- ክርስቲያን ውስጥ ማኅሌት ተቁሟል ካህናቱም የሰንበት ተማሪዎችም እኔም ከዚያ መካከል መቋሚያ ይዤ ችሎታዬ ከሁሉ ያነሰ ስለሆነ ከበስተኋላ ቁሜለሁ። ከዚያም መዘምራኑ እየገፉ ወደ ውስጥ ያስገቡኛል። ሁለት ካህናት ፊት ለፊት እየተያዩ ሰዓታት አይሉት፤ ማኅሌት ወረብ አይሉት፤ ዘፈን ወይም ቅዳሴ አይሉት ብቻ ምኑም አይታወቅ መቋሚያ ይዘው ይጨፍራሉ። እኔም *ሥራ*ቸውን እምለከትና ኧረ ተው አቁሙ ጥሩ *ሥራ* አይደለም እያልኩ እነገራለሁ። ብዙ ሻማ ከምድር ተቀምጦ ይበራል፤ ከዚያ አንድ መነኩሴ በያዙት መቋሚያ ሰውን ሁሉ ጎን ጎኑን እየጎሰሙ "ሻማውን አጥፉ እያሉ ይናገራሉ" ሁሉም ዝም ይላል። በመጨረሻ አንድ ካህን በግድ ተጎንብሶ አጠፋው። እርሳቸው ግን አሁንም በያዙት መቋሚያ መጎሰማቸውን አልተውም፤ ከእኔ ደርሰው ጎኔን ሲወጉኝ ዞር ብዬ ሳያቸው "አንተ ነህ እንዴ እ . እ .ም . ም"ብለው ተደምመው ሹልክ ብለው ጠፉ። እኔም በዓይኔ ተከታተልኳቸው ላያቸው ግን አልቻልኩም። ይህ የሚያሳየው በቤተ-ክርስቲያናችን ታላቅ ችግር እንዳለ ነው። መነኩሴውም ቄሱም ዲያቆኑም ሁሉም ጠፍተዋል። አገልጋይም የለም በሰንበትና በታላላቅ በዓለት ማኅሌቱን የሚቆሙት ጽናጽልና መቋሚያ ይዘው ከበሮውን የሚጎስሙት መርጌ ሊቃውንት የሉም። በንጹህ ልቦና ሆኖ የሚቆም የለም ሁሉም ከቦታው ጠፍተዋል፣ በንጹህ ህሊና በቅን ልቡና ሁነው የጌታች የመድኃኒታችን የኢሱስ ክርስቶስን ቅዱስ *ሥጋ*ውንና ከቡር ደሙን የሚፈትት ወይም የሚያዘጋጅ የለም (አልተገኘም)።

እውቀት ላላቸውና ለተማሩ ሰዎች ቦታው ተዘግቶባቸዋል። እውቀት የሌላቸው ሰዎች ቦታውን ይዘው ይኮፈሱበታል። ሰዎች በጌታችን በመድኃኒታችን ቤት ክብርና መአረግ የሚሰጣቸው መስሎአቸው መድረክ ላይ ቁመው ይጎራደዳሉ እውቀትንና መአረግን ግን የሚሰጥ እሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ፤ ማንም በእሱ ቤት የሚሰጥ የለም። እግዚአብሔርም በተለያየ ነገር ተናገረ ግን ሰሚ ጠፋ፤ ከእርሱ ቁጣ ያድነን ሁሉም በኃጢአት ልቡ ተሸፍኖ ደንድኗል፤ በትዕቢት ተወጥሯል ጥቅም አሳዳጅ ሁኗል ፍቅር የለም ጠላቻ ነግሷል ቤተ-ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ምሕረት መለመኛ የሰላማም ማውረጃ መሆን ሲገባት የፖለቲካ ማራመጃና መፋጠጫ ሁናለች ፣ካህናቱም ምእመናኑም በእርስዋ ውስጥ የቃላት ጦርነት ሲያካሂዱ ይውላሉ። ማስታረቅ ሳይሆን ማጣላት፤ መሰብሰብ ሳይሆን መበተን እንደ ዕለት ተግባር ተይዟል፤ በመፋቀር ፋንታ የጎሪጥ መተያየት ሁኗል። ታዲያ እግዚአብሔር ከላይ ሆኖ እንዴት ይመለከተን ይሆን። ከሁሉም በላይ እጅግ የሚያሳዝነው እንዴት አንዲት ቤተ-ክርሰቲያን ከሁለት እንደ ጭራ ትስነጠቃለች ይህ ሁሉ መከራ የመጣብን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ስትከፈል ነው ሰውም ሁሉ ያላወቀው ነገር ቢኖር ይህንኑ ነው። የጥንት አባቶቻችን መንገድ ብንከተል ኖሮ ይህ ሁሉ መከራ ባልበዛብን ነበር፤ እነርሱ በፍቅር ሁነው ቤተ ክርስቲያንን ሠሩ እግዚአብሔርንም አገለገሉ። ሌትና ቀን ቁመው ለሀገራቸው ሰላመንና ደህንነትን ለወገናቸው ሀብትን በረከትን እንዲሰጥላቸው ሁልጊዜ ካህናቱም መነኮሳቱም ይጸልዩ ነበር። የአሁኖቹ ግን ለራሳቸው ብቻ እንጂ ለሀገራቸውና ለወገናቸው አያስቡም፣ የዓለሙን መንገድ ተከትለዋል፤ የሚያልፈውን እንጂ የማያልፈውን አልፈለጉም፣በዚሁም ሁኔታ ቢጸልዩ ጸሎታቸው ተሰሚነት ይኖረዋል ተብሎ አይታመንበትም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን አሳዝነዋል እመቤታችን አስቀይመዋል፣ጻድቃን ሰማዕታት መላእክትም እንዳይታደጉን በመጥፎ *ሥራ*ችን አርቀናቸዋል። እርሱ እግዚአብሔር ብቻ የድሮዎቹን ጸሎት ሰምቶ አስታውሶ ለእኛ ምሕረትን ያውርድልን ፍቅረ ሰላሙን ይስጠን በቀኝ እጁ ከወደቅነበት ያነሳን ዘንድ በምሕረቱ የጎበኘን በዚህ መጥፎ በሻታ የተለከፉትን ምሕረትን ይስጥልን አሜን።

## <u>ራዕየ ሄኖክ፤በኢትዮጵያ፤</u>

*የያሬድ ልጅ ሄኖክ ያየውን ለማቱሳላና ለልጅ ልጆቹ ለላሜህ እስከ ኖህ ድረስ የሰው ልጅ በምን እንደሚጠፋና እንደሚድን አይቶ የጻፈውን ለልጁ ለማቱሳላ የሰጠውን ወይም መጽሐፈ ሄኖክን*

*አንብቤ ከተረዳሁትና ካየሁት ለክፉዎች የሚያስጨንቅ ለደጋጎች የሚያስደስት ሆኖ አገኘሁት። በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ኃይል ቃላት ላለፈው ዘመንና አሁን ለአለነበት ዘመን ቁልጭ አድርጎ እንደመስታውት የሚያሳይ ሲሆን፤ አሁንም ለሰው ልጆች የሚደርሰውን ግፍና መከራ ፣እረገጣና ጭቆና ፣ድብደባና ግርፋት፣ እሥራትና እንግለቲት፣ ግድያና ሞት፣ ረሀብና ጥማት ፣ችግርና እርዛት፣ ተሰዶ መንከራተቱን አጉልቶ ስለሚያሳይ፤ እኔ ያን ሳይ ልቤ በኃዘን ተነካ። መጽሐፉንም አንብቤ እንደጨረስኩት ተነሳሁና የዘወትር ጸሎቴን አድርሼ ጌታዬን አመስግኘ ወደ ምኝታ ክፍል ገባሁና ተኛሁ።*

ከአልጋ እንደተጋደምኩ በቤተ -ክርስቲያን በግፍ የተጨፈጨፉትና የተገደሉት በግራኝ አህመድ በድርቡሽና በፋሽስት ጣሊያን ያለቁትን ካህንትና ምእመናን መነኮሳትና ደናግሉን ባጠቃላይ በቤተ-ክርስቲያን በደረሰው ግፍ በህሊናዬ መጥቶ ታዬኝ። በዚያን ሰዓት አምላኪዬን ፈጣሪዬን፤ ምን ነው ይህ ሁሉ በደል በእኛ ላይ ደረሰ ፣እለት በዕለት መስቀሉን ተሸክመን እየተጓዝን፣አንተ ግን ይህን ሁሉ መከራ ጫንከብን፣አባቶቻችን ያገኛቸውን መከራና በደል በእኛ ላይ አትድገመው አድነን፣ በመላእክታንም አስጠብቀን ብዬ ጸሎቴን ጨርሼ ተኛሁ። ወዲያው እንቅልፍ እንደ ወሰደኝ ሦስት ሽማግሌዎች አንድ ሕፃን ልጅ ሁነው ጠርተውኝ ሄድኩ። እነርሱ ቁመው ያሉት ከአንድ አትክልት ካለው ግቢ ውስጥ ነው፣ ወረቀትና ብዕር ይዣለሁ ከሽማግሌዎች ጋር የእጅ ሰላምታ ተለዋወጥን ሕፃኑ ልጅ ግን እኔ ስደርስ ተሠወረ። ከዚያ እነዛ ሽማግሌዎች ጻፍ ሲሉኝ ከመጀመሪያው አንሰቼ ማለትም ከግራኝ አህመድ አንስቶ አሁን እስከ ተጨፈጨፉት አንድ በአንድ ጽፌአለሁ አልኳቸው። ከዚያ አንድ ቀይ ሽማግሌ ሰው "አዎ ጠላታቸው አንድ ነው" አለኝ። እንደዛ እንዳሉኝ መልኩ ነጭና ጥቁር የሆነ ትልቅ እባብ በሩቅ ታየኝ። ከቦታው ብዙ ከብትና ብዙ ጥጃ ያለበት ቦታ ነው፣ ሁላችንም ወደዚያ ስፍራ ስንሄድ ያን ሕፃን ልጅ ከዚያ ቁሞ አየሁት። እንደ ደረስን እኔ ከብቱ ወዳለበት ሂጄ ገባሁ ሦስት ሽማግሌዎች እና ሕፃኑ ልጅ እባቡ ወደ ተደበቀበት ስፍራ ሄዱና ያ ቀይ ሽማግሌ እጁን ሰዶ አፈር ለብሶ ከተኛበት እባቡን ያዘው። እባቡ ሲያዝ ያ ሁሉ ከብት በረገገ እኔም ከእንቅልፌ ነቃሁ። ይሄን ያየሁት በዕለተ ሰንበትና የቅዱስ ገበርኤል ዕለት በዋለበት ፤ጥቅምት፡19፡ቀን፡፲፱ ፻፺፱ (19/1999፡ ዓ/ም)

## <u>በጅማና በሌሎች አካባቢ ስለ እምነታቸው ለተሠውት ሰማዕታት መታሰቢያ፤</u>

**በአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በአል በዕለተ ሰንበት፤ የሰማይ መላእክት፤ ጥቅምት፡ ፭፡ቀን፡፲፱ ፻፺፱ (5/1999፡ዓ/ም)**

በቤተ -ክርስቲያን የፈሰሰውን ደም
የሰማይ መላእክት አዩ በመገረም
ያችን ነፍስ ወሰዱ እያሉ ትለምልም።
ለሰው ልጅ በሙሉ ለአዋቂ ለልጅም
በቤተ-ክርስቲያን በፈሰሰው ደም
እንዳይጫናቸው የመከራ ሸክም
መላእክት መጡና ቆሙ ለሰላም
ደሙንም ጠረጉት እንዳይፈስ ዳግም።
የሰማይ መላእክት መጥተው ተረከብዋት
ትልቁ ጻድቅም ፊት፤ፊት እየመሯት
ከፈጣሪዋ ዘንድ ወስደው አደረስዋት።
በእርሱ ቤት መውደቅዋ ክብርን አስገኘላት
መርቆ አመስግኖ ሽልማቱን ሰጣት
የብርሃን አክሊል ጽድቁን አለበሳት
ፈቃድን አግንታ ሄደች ወደገነት
አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ካሉበት
ሂዳ ተገናኘች ከጻድቃን ሰማዕታት።
የታደለች ነፍስ አምላክ የወደዳት
በተመረጠች ቀን እርሱ በሚያርፍባት

እረፍትን አገኘች በእለተ ሰንበት
እያሉ ዘመሩ በሰማይ መላእከት።
እያሸበሸቡ ጻድቃን ሰማዕታት
እንኳን ደስ አለሽ ብለው ተቀበልዋት
ምስጋና አቀረቡ ለሰማዩ አባት
ለሦስቱ ሥላሴ ያችን ነፍስን ለአዳኗት።

## ራዕይ፤በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤ መጋቢት፡፳፯፡ቀን፡፲፱ ፻፺፱ (27/1999፡ዓ/ም)

የመድኃኔዓለም ቀን በዕለተ ጸሎተ ሐሙስ ነበር። ያየሁት ራዕይ ይህውም ለንደን በምትገኘው በደብረ ጽዮን ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሲሆን፣ ያየሁት ራእይ እንደሚከተለው ይሆናል። በቤተ-ክርስቲያኗ ውስጥ የሚያገለግሉት ዲያቆናትና መዘምራን በሙሉ ባንድ ሚኒ ባስ ሞልተው ትልቅ የእጅ ማይክራፎን ይዘው ለቤተ-ክርስቲያኗ መግዣ የሚሆን ገንዘብ አዋጡ እያሉ ማይክራፎኑን በመኪናው መስኮት ብቅ አድርገው በከፍተኛ ድምጽ እየጮሁ ይናገራሉ። ሕዝቡ ግን ቁሞ በመገረም ዝም ብሎ ያ ያቸዋል። ምክንያቱም እነርሱ የሚናገሩት ለሕዝቡ ምን እንደሚሉ አይገባውም ነበርና። ከተማውን ሲዞሩ ከቆዩ በኋላ በደቡብ በኩል አድርገው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ጥርጊያውን ይዘው ወደ ቤተ-ክርስቲያኗ መጡ። ከዚያም ከዋናው በር መግቢያ ላይ ሲደርሱ ሁሉም እንዳለ ከመኪናው ወረዱ፣ የቤተ-ክርስቲያኗ በራፍ ግን እንደተዘጋ ነበር። እነርሱ ግን ይዘው የመጡት ገንዘብ ሳይሆን ከበሮ ጽናጽል እና መቋሚያ ነው። ያን እንዳለ ከበራፉ ውጭ አስቀምጠው በመጡበት መኪና ተሳፍረው ሁሉም ተመልሰው ወደ ሄዱ። መሪያቸው አንድ ዲያቆን ነው እሱ ቤተ-ክርስቲያኗ ስትመሰረት ጀምሮ አብሮ የነበረ ነው። እንዲያውም በአስተዳደር ውስጥ ይሰራል ስሙን ግን መግለጽ አልፈልግም። በእንዲህ እንዳለ አንዲት ቀይ ወጣት ሴት እንደ ጸሐይ የምታበራ በራፉን ከፍታ ወጣች ፣የለበሰችው ልብስ እስከ ተረከዟ የደረሰ መልኩም ሰማያዊ ሆኖ፣ እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቅ ነው። በኋላዋም አንድ ጠይም ጎበዝ ነጭ ልብስ የለበሰ አብሯት ቆሟል። እሷ ከበራፉ ላይ ቁማ ለአንዱ መዘምራን እንዲህ ትለዋለች “አንተ ግን ብትመለስ ይሻልሃል የሚጋብዝህ የለምና ተመለስ” እያለች ብትጠራውና ብትነገረው እሱ ግን ሊመልስላት አልቻለም፣ ዞር ብሎም አላያትም።
ሁሉም በመኪናው ሞልተው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተጓዙ። እኔም እንደነሱ ለቤተ-ክርስቲያኗ መግዣ የሚሆን ገንዘብ አሰባስቤ ይዤ መጥቼ የተማሪ ደበሎ የመሰለ ልብስ ለብሼ በምሥራቅ በመቅደሱ በኩል ራቅ ብየ ተቀምጫለሁ። ለዛች ቀይ ሴት ያመጣሁትን ገንዘብ ተቀበይኝ እና አሰናብችኝ አገሬ እሩቅ ነው፣ ልሂድ እላታለሁ። እሷም “አንተማ ከእኔ ጋር ሳትጋበዝ አትሄድም “ትልና ከጠባቂዋ ጋር ሁና እሷ በፊት እየመራች እኔ በኋላዋ እየተከተልኩ ወደ ጸሐይ መውጫ መኖሪያ ቤቷ ይዛኝ ሄደች። አብሯት ያለው ጠይም ጎበዝ ግን ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻው አንድም ቃል ሳይተነፍስ፣ እሷ ስትንቀሳቀስ አብሮ ይንቀሳቀሳል እንጂ ሌላ ምንም አያደርግም ነበር። በጉዞ ላይ እንዳለን በድንገት አንድ ትልቅ ቤት ከፊታችን ቁሞ አየን። የዚያ ቤት ግቢም በራፉ ተከፍቶ ቆየን፣ እንደ ሄድንም ከዚያ ቤት ገባን። ያ ቤትም እራሱ ቤተ-ክርስቲያኑ ነው፣ ሙብራት ወይም ሻማ አልበራበትም እንዲሁ ደብዘዝ ያለ የቀን ብርሃን የመሰለ የታይበታል እንጂ ሌላ ነገር የለውም። እሷ እና አብሯት ያለው ሌሎችም ሰዎች ሁነው ከመቅደሱ ውስጥ የሆነ ስራ ይሰራሉ፣ የሚሰሩትን ግን አላውቅም። እኔ ያለሁበት ቦታም ከነእርሱ በጣም ይርቃል የቆምኩበት ስፍራም በምሥራቅ በኩል ነው። በዚያ በኩል በራፍ የለውም ፣ዋናው የመግቢያው በራፍ ተዘግቷል አልተከፈተም። እኔ ከግድግዳው ላይ ተደግፌ ቁሜ ሳለሁ በተአምር በጣም ትልቅ የሆነ የብረት መዝጊያ ይቆማል። ያ የብረት መዝጊያ በሁለት በኩል የሚከፈትና በመወርውሪያ የሚዘጋ ነው። ያ መዝጊያ እንደ ቆመ በምዕራብ በኩል የመጣ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ እንደ ሰው ገልብጦ ሊገባ ይታገላል። እኔም በመወርወሪያው ዘግቼ በሁለት እጆቼ ይዤ እገፋለሁ ገልብጦ እንዳይገባ። ነፋሱ ግን ኃይል ስላለው እስከ ጣራው ድረስ አነቃነቀው፤ ሊከፍተው ግን አልቻለም።
ከዚያ መሃል ሌላ አውሎ ነፋስ ከውስጥ ይነሳል ሰው የሚመስል። ነገር ግን እንደ ነፋስ ነው የሚውለበለበው ፣ከመሬት ተነስቶ ጣራውን ገልብጦ ሊወጣ ሲል፣ ያች ቀይ ሴት ትመጣና የሆነ ቃላት ስትናገር ያነ ነፋስ ከዚያው ከቤተ-ክርስቲያኗ ውስጥ መሬት ተከፍቶ ጉድጓድ ውስጥ ገባ። ለእኔ

ትመጣና "እንዲህ አይነቱ፤ **በአዶናይ ፤በአልሻዳይ፤ በእንዲህ አይነት ድግምት ነው የሚሸነፍ" አለችኝ።** እኔም በነፋሱ አስፈሪነት የተነሳ ደንግጬ ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ ሳለ፤ ከዚያ ቤተ-ክርስቲያን አውጥታ ብዙ በጎች ወደ አሉበት ቦታ ወሰደችኝ። ጫማ አላደረኩም በባዶ እግሬ ነው የሚሄደው። ነገር ግን መሬቱ በጣም ለስላሳ ስለነበረ፣ እግሬን አልተሰማኝም። በጎቹን በርቀት ሳያቸው የሰውነታቸው ማማርና የተለያየ መልክ በመሆናቸው እያደነኩና እየተገረምኩ፣ እንዲሁም ከሰውነታቸው በሚወጣው ጠረን (ሽታ) ተመስጬ ሳለሁ፣ ያ የያዘኝ ፍርኃት እና እንቅጥቅጥ የት እንደገባ ሳላውቀው ጠፋና ድንገት ከበጎቹ ጋር ሂጄ ተቀላቀልኩ። በጎቹ የህዳርን ቀርም ሣር ይለቅማሉ እረኛው ግን አይታይም በበጎቹ ውበትና በሽታቸው መዐዛ እንደተመሰጥኩ ከምኝታየ ነቃሁ።
ደስ ብሎኛል ደስ፤ ደስ ብሎኛል ደስ፤

በእመቤቴ ማርያም አግኝቻለሁ ፈውስ፤
ምን አስሄደኝ ከዚያ እንጦጦ ድረስ፤
ከዚህው ድኛለሁ ሳልንቀሳቀስ።
ምን አስሄደኝ ከዛ መንበሯ ካለበት፤
ከቤቴ ድኛለሁ ከዚህ ካለሁበት።
ምን አስሄደኝ ከዛ ተነስቼ በወርጭ፤
ከዚህው ተፈወስኩ የእርሷን ጸበል ስረጭ።
ስሟን እጣራለሁ ሁልጊዜ ሳልታክት፤
የድንግል ማርያምን የጌታዬን እናት፤
የእኔ ተስፋ አለኝታ አጽናኜ እርሷ ናት።

## ራዕይ በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም፤
## ጥር፡፳፩፡ቀን፡፪፻፪ (21/2002፤ዓ/ም)

የእመቤታችን በአል የአስተርእዮ ማርያም ዕለት በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ-ክርስቲያን በአሉን ለማክበር ከዚህ ከእግላንድ ውስጥና ከውጭ አገር የመጣ ሕዝብ ቤተ-ክርስቲያኗን ሞልቷታል። አንድ የቤተ-ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ መምህር ከጥንቱ ማህሌት አቋቋም በተለየ በአዲስ አያያዝ መቋሚያና ጽናጽል አሲዞ ካህናቱን ሰብስቦ ያስረግደዋል። እኔንም መቋሚያና ጽናጽል አሲዞ አብሮ ያስተምረኛል ዜማውና አቋቋሙ ልብን ይመስጣል (ይማርካል)እንኳን ካህናቱ ባላገሩ ሳይቀር በመምህሩ ማህሌትና አቋቋም ጽናጽል አያያዝ የተለየ በመሆኑ ሕዝቡ በደስታ ተውጦ በአየር ላይ የሚሳፈፍ ይመስላል። እኔም መቋሚያና ጽናጽል ይዤ እንደ ካህናቱ ስለ ማልችል ለምነው ያለ ቦታየና ያለ ችሎታየ ከዚህ ውስጥ ያስገባሃኝ የኔ ሥራየ ዳዊት እየደገምኩ መጸለይ ነው እንደ ሰዎቹ ብዬ ዞሬ ወደ ኋላ ሳይ ከኢትዮጵያ በየ ገዳማቱ ፤በየ አድባራቱ ያሉት ትላልቅ አባቶች፤ ልብሳቸው ያለቀ በየ ዛፉ እግር፤ በየ ቅጥሩ ተቀምጠው ዳዊታቸውን ዘርግተው ይደግማሉ፤ ረሃብ አጎሳቁሏቸዋል፤ ደክመዋል ውስጣቸው ግን በጣም ደስተኛ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ደህና ልብስ የለበሱ ሰውነታቸው ያልተጎሳቆለ በልተው የጠገቡ፤ ግን ውስጣቸው በሃዘን የተጎዱ ቁመው አየሁ። በዚህ እየተገረምኩ ቁሜ ሳለ አንድ ሊቀ ጳጳስ ከሴት ጓደኛው ጋር ሲጫወት አየሁት፤ ወዲያው ተነስቼ ሂጄ ከነ ሴት ጓደኛው አውጥቼ አባረርኩት የእሱን አልጋ እኔ ተቀመጥኩበት። ያን ከአደረኩ በኋላ እስከ መቼ ሰዎችን እጠብቃለሁ እኔ ራሴ ሂጄ ጦርነት መግጠም አለብኝ ብዬ ጦርና ጋሻ ፤ ጎራዴ ይዤ ተንሳሁ፤ ወደ ጦር ሜዳ ከመሄዴ በፊት ተንበርክኬ ጸሎት አድርጌ ጌታዬ አብሮ ሂዶ እንዲረዳኝ ለምኜ ወደ በረሃው ሄድኩ። ከዚያ ስደርስ ጦሩ በሁለት ወገን ተከፍሎ በሰሜንና በምዕራብ በኩል ሊዋጋ ተሰልፏል። ወታደሩ ከባድ መሳሪያና ቀላል መሳሪያ ታጥቆ በተጠንቀቅ ላይ ቁሞአል። ከዚያ ደርሼ ከሁለቱ ጦር መሃል ስገባ ሁሉም ወደ እኔ ሊተኩስ አፈሙዝ አዙሮ ምላጭ ሊስብ ሲዘጋጅ የያስኩትን ሰይፍ ከፍ አድርጌ ሳሳያቸው ሁሉም መሳሪያውን እየጣለ መጥቶ ከበበኝ። እየተሳሳቁ እርስ በርሳቸው አንገት ለአንገት ተያይዘው ተሳሳሙ የኤርትራ ወታደርም ወደ ቦታው ሳይመለስ እንደ ተቀላቀለ አብሮ በዚያው ቀረ።

## የካቲት ፲፱ ቀን ፡ ፪ሺ፭ ዓ/ም (19/06/ 2005)

**የቅዱስ ገብርኤል ዕለት፤** በለደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያየሁት ራዕይ። ህንጻው ፈርሶ ጣራውና ግድግዳው ቆርቆሮ ለብሶ በበራፉ የገባው ኃይለኛ ነፋስ በምሥራቅና በምዕራብ በኩል ያለውን የቆርቆሮ ግድግዳ ሲነቃቅለውና ጣራውን ሳይቀር ሲያነቃንቀው ሰው ከዚያ ውስጥ የነበረውን ንብረት ማንም ሰው ሳይሰጠው በየፊናው እያነሳ ወደ እየ ቤቱ ይዞት ሄደ። እኔ የቤተ ክርስቲያኗ መፍረስና የንብረቱ መዘረፍን ሳይ ከቦታው እራቅ ብዬ ቁጭ ብዬ ሳለቅስ ሁለት ሰዎች እረጃጅም ሽመል በትራቸውን ከትከሻቸው ላይ አድርገው ወደ እኔ መጡና፤ ከዚህ ብቻህን ሁነህ ምን ያሳዝንሃል ምንስ ያስለቅስሃል፤ ተነስና እኛን ተከተል ብለው ወደ ምሥራቅ ይዘውኝ ሄዱ። ሰዎቹ ካሁን ቀደም በራዕይ ተገልጸው ያ የኳቸው ሲሆን፤ መልካቸውም አንደኛው ጥቁር ሁለተኛው ደግሞ ቀይ ነው። ጥቁሩ ሰውዬ በፊት ዘለቀ ከሚባለው ሰውዬ ጋር መጥቶ ዘለቀ የሚባለው ሰውዬ ዛሬ እኔ እነግራችኋለሁ ፤ በሚቀጥለው ደግሞ ሲሳይ ይነግራችኋላ ብሎ ሁለቱም ከአንድላይ ተሰወሩ። ግን ሲሳይ የሚባለው በአንደበቱ ምንም አልተናገረም ነበር፤ ዝም ብሎ ነው የሄደ። አሁንም ተመልሶ ሲመጣ አልተናገረም፤ ቀዩ ደግሞ በፊት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ-ክርስቲያኗ በራፍ ቆሞ ጠብቅ ያልኩትን ትቶ ጠፋ ብሎ ያስፈለገው መምህር ነበር። ከዚያ በኋላ እሱን አስፈልጎ ሲያጣው ካህናቱን በሙሉ በጅራሽ ግርፎ ከመቅደስ ያስወጣቸው። አሁንም ያ መምህር ከጥቁሩ ሰውዬ ጋር ሆኖ እረጅም ሽመል ከትከሻው አድርጎ እሱ ነበር፤ ብቻህን ምን ያስለቅስሃል ምን ያሳዝንሃል ያለኝ። እኔም በቤተክርስቲያኒቱ መፍረስ እያዘንኩ ጓዜን ተሸክሜ እነሱን ተከትዬ ሄድኩ። ከተባለው ቦታ ስንደርስ ከአንድ ትልቅ አዳራሽ ቤት ገባን። ከዚያ ቤት አንዷት ጠይም ወጣት ሴት እስከ እግር ጣቷ ቀሚሷን እየጎተተች አንድ አይነት ዕድሜ ያለቸው ፊታቸው የመላእክታን ፊት የመሰለ ሕጻናቶች ሰብስባ ምግብ ስትመግብ ደረስን። እኒህን ሕጻናቶች በአንድ ግዜ እንዴት ወለደቻቸው እያልኩ ስገረም ሳለ። እንዲሁም ሌላ ተጨማሪ እነዚያን የሚመስሉ ሕጻናት አንድ አይነት እድሜ አንድ አይነት መልክ ያለቸው ሕጻናት ከጎረቤት መጥተው አብራ መአድ አቅርባ ስታበላቸው አየሁ። እኒያ ሰዎችም እኔን አስገብተው ተሰወሩ፤ ሴቲቱም ለእኔም ምግብ አቀረበችልኝ እኔም ተቀብየ በላሁ ከዚያ ቤት ሳልወጣ ከንቅልፌ ባነንኩ።

## ክፍል ሁለት፣ስለ ሀገር፤
## እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ፤1998፤

**በኤርትራ ላይ የታየ አስደንጋጭ ራዕይ** ፤ ወቅቱ የኢትዮና የኤርትራ ግጭት ዳግም ሊቀሰቀስ የጦርነት ነጋሪት እየተጎሰመ በአለበት ሰዓት ይህውም የኤርትራ መንግሥት የመጀመሪያ ዒላማ ያደረገው በመቀሌ ሕጻናት በትምህርት ቤት እንዳሉ በአውሮፕላን ድብደባ ያደረው እለት ነበር። የነዚያን ህጻናት አማሟት በትቪ ሳይ ልቤ በሃዘን ተነካ ምክንያቱም ወደፊት ከዚያ የባሰ እንደሚመጣ በግልጽ ታየኝ። የኢትዮጵያ መጻኢ እድል ምን ያጋጥማት ይሆን የሚለውም ትልቁ ጉዳይ ሆኖ አስጨነቀኝ፤በዚህ የተነሳ ፈጣሪየን ተብርክኬ ለመንኩት። አንድ ቀን በጸሎት ላይ ሳለሁ ማለትም ስለ ሀገራችን ችግር እግዚአብሔር ሰላም እንዲሰጠን ስለምነው ቆይቼ ወደምኝታዬ ክፍል ሄጀ ተኛሁ። በሕልሜ የባህታዊ ብጫ ልብስ የለበሰ ቀይ ሰው መጥቶ ከመኝታየ አስነስቶ ወደ ትልቅ ተራራ አወጣኝና ለሁሉም ጊዜ አለው፤(መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ፡3) የሚለውን አንብብ አለኝ። መልሶም “ያችን ከተማ ታውቃታለህ ወይ?” አለኝ። እኔም ኸረ ጌታዬ አላውቃትም አልኩት። እሱም መልሶ “ያች ከተማ አሥመራ ናት” አለኝ ፤ ከዚያ መሃከል ፒያሳ ላይ ወይም ጥርጊያ ላይ ሰውን ከሦስት ከፈለውና ሽማግሌዎችን በተራ ለብቻ አቆማቸው፤ ከዚያም ወጣቱን ክፍል እንደዚሁ አቆማቸው፤ ደግሞም ሕፃናትን ለብቻቸው በተራ አቆማቸው፤ መልሶም መሪውን ማለትም ፕሬዝደንት ኢሳይያስን የጦር ሰራዊት ልብስ እንደለበሰ ለብቻው ቁሞ አየሁት። በኋላቸው ትላልቅ ከርሠ ምድር (አንደር ግራውንድ) የሚመስል ጋራጅ በሁሉም በኩል ጨለማ ለብሶ በራፉ ተከፍቶ ይታያል። አንዷት ትልቅ አዛውንት የሆኑ ሴት ተነስተው በማናውቀው ነገር አለቅነ፤ በማናውቀው ነገር አለቅነ እያሉ፤ ወዪያና ወዪህ ይዘላሉ። በኋላ በየአሉበት ሁሉም በተዘጋጀላቸው ቦታ ጨለማ ውስጥ ገብተው በሩ ተዘጋባቸው፤ መሪው ፕሬስደንት ኢሳይያስ

አፈወርቂ ብቻውን ሲቀር አየሁት። ኤርትራንም ከጫጉላ እንዳለች ሙሽራ፤ በተዳረች በሰባት ቀኗ ሙሽርነቷን ሳትጨርስ የራስ ጠጉሯን አስላጭቶ ነጠላዋን አስወልቆ በወጣት ሴት መስሎ ከኤርትራ አውጥቶ ከመሃል ኢትዮጵያ ሸዋ ክፍለ ሀገር ጫካ ውስጥ አስገብቶ አንጋሎ አስተኝቶ በበላዩዋ እሳር ሲበቅልባት አሳየኝ። ይህን ከአሳየኝ በኋላ ከኔ ጋር የነበረው ሰውዬ ከፊቴ ተሠወረ።

በዚያን ሰዓት ፕሬዝደንት ኢሳይያስና ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ለድርድር ወደ ቦርኪና ፋሶ ሄደው ነበር፤ እኔ ጧት ከምኝታየ ተነስቼ እንደ እኔ በስደት ለሚኖሩ ኤርትራውያን ለብዙ ሰዎች ነገርኳቸው ማለትም እኒህ ሰዎች አይስማሙም ነገሩ ከእግዚአብሔር ነው ሁላችሁም ተሰብስባችሁ እግዚኦ በሉ ለወገኖቻችሁም ንገሯቸው ይጸልዩ አልኳቸው። እነሱ ግን የእኔን ንግግር ከምንም አልቆጠሩትም በመቀሌ ትምህርት ቤት በአውሮፕላን በተጨፈጨፉት ህጻናት ሞት ተደስተው ይጨፍሩ ነበር። የእግዚአብሔር ቃልም ደረሰና ኤርትራ በምን ደረጃ እንዳለች እያየን ነው።

## <u>ስለ ኢትዮጵያ የታየ፤</u>

የላይኛውን ራእይ ካየሁ ከሁለት ወር በኋላ እንዲሁም በኢትዮጵያ በአንድ ሌሊት ሁለት ራእይ አየሁ። እሱም የመጀመሪያው በምሥራቅ እና በደቡብ በኩል ሁለት ሕዝብ በጦር ሊዋጋ ከዚያና ከዚህ እየተሯሯጠ መጥቶ ሊገጥም ሲል በፀሐይ መውጫ በአህያ ተቀምጦ ካባ እና ዘውድ የጫነ ሰው እኔ በኋላ በኋላው እየተከተልኩ ያ ሁለት ሕዝብ ሊገጥም ሲል አህያዋ ከመሃል ገብታ በኋላ እግሯ ቁማ የፊት ሁለት እግሮቿን እንደ ሞተር ስታሽከረክራቸው፤ ከዚያ ሁሉም ሰው ተደናግጦ ወደኋላ ተመለሰ። ያ ሰውም ማለትም በአህያይቱ ላይ የነበረው ከፊቴ ተሠወረ፤ የት እንደ ሄደ አላየሁትም። ሁለተኛው ራዕይ ያየሁት በኢትዮጵያ ሕዝቡ ተሰብስቦ በተራ ቁሞ የምርጫ ካርድ ይመስለኛል ሰው ሁሉ ይዞ ሱቅ በደረቴ የምትመስል ናት፣ከዚያ አንድ ሰው ተቀምጦ ወረቀታቸውን ይቀበላል እኔም እንደሰው ተሰልፌ ቁሜአለሁ፤ ነገሩ ለምን እንደሆነ አላወኩም ነበር። በኋላ ተራዬ ሲደርሰኝ ለሰውየው የምርጫ ካርድ ነው ሰው ሁሉ የሚሰጠው፤ እኔ ምንም የያዝኩት ነገር የለኝም ከዚያ ማሃከል ያ በፊት አስመራን ያሳየኝ ሰው መጥቶ “አንተ ከዚህ አይደለም ምድብህ” ብሎ ከሰው ነጥሎ ወደ በረሃ ወሰደኝ። ከዚያ በኋላ ሦስት መጽሐፎች በፖስታ አሽጎ ሰጠኝና እሱ ከኔ ተሠወረ፤ እኔም ብቻየን ከበረሃው ቀረሁ። እነኛ ሦስት መጽሐፎች በኢትዮጵያ ሦስት ነገሮች አሉ እነሱም እያንዳንዳቸው ትርጉማቸውን ያስረዱናል በሽታ ረሃብ ስደት ወይም ሞት እንበለው፤ ትርጉሙን ያነ አንድ ሰው ከወንበር ቁጭ ብሎ የምርጫ ካርድ የሚቀበለው በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ነው። ሰይጣን በሰው ተመስሎ ሕዝቡን በተለያየ ነገር እንደ ቅጠል በየቀኑ የሚያስረግፈው፤ እንደገና ሕዝቡም በየተራ ያ የምርጫ ካርድ የሚሰጥ እጣ ፈንታው ለሞት የደረሰው ነው። የእነዛ ሦስት መጽሐፎች ትርጉም ይህ ይመስላል። እነኛን ሦስት መጽሐፎች ያ መላእኩ ከፍቶ ሰጥቶኝ ቢሆን ኑሮ ኢትዮጵያ የሰላሙ ጊዜ ቀርቦላት ነበር፤ ሁኖ ግን የኛ ተንኮላችን እና ኃጢአታችን ስለበዛ እግዚአብሔርም ፊቱን ከኛ አዙሮብናል። ግማሹም ሀገር እየተወ በሰው ሀገር ተንከራታች ሁኗል። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው የሰው ልጅ ያልተወለደበትን ሀገር እንደተወለደበት ሀገር ይናፍቃል። ይኸውም ደርሶ እያየን ነው፤ ሕዝቡ ሀገሩን እየጣለ እየተሰደደ እየወጣ ነው። አሁንም የእግዚአብሔር ቃል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ይሰደዳሉ ይላል ፤ ከዚያም በመጨረሻ ከሞት የተረፉት ሽዋል ለብሰው ይመለሳሉ። ይህም በኛ ላይ እንዳይደርስ ወገኖቼ በንጹህ ህሊና በቅን ልቦና ሁነን ፈጣሪያችን እንለምነው። መዓቱን ከኛ እንዲያርቅልን አገራችን ሰላም እንዲሰጥልን። ከዚህ ከምናየው እና ከምንሰማው መጥፎ ነገር እንዲሠውረን ሁላችንም በየአለንበት እግዚአብሔርን እንለምነው። እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር መንገድ በመውጣታቸው የደረሰባቸውን ነገር እንመልከት የባቢሎን ንጉሥ አገራቸውን አቃጥሎ እነሱን ማርኮ በወሰዳቸው ጊዜ እንዴት እንደጸለዩ እንሰማለን ኢየሩሳሌም አትርሽን አንረሳሽም ባሉ ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ መልሶ ወደ ሀርቸው እንዳስገባቸው በቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን። እኛም ያችን የምንወዳትን ሀገር ኢትዮጵያ ማሪን እንበላት አንርሳት እናስታውሳት ከፈጣሪያችን ጸሎታችን ደርሶ ምሕረትን እንድናገኝ ከመለመን አንቆጠብ እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ አምላክ ነው ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች (መዝሙር ፡67 ፤ቁጥር ፡31) የሚለውን ቃል እናስተውል።

# ራዕይ በኢትዮጵያና በኤርትራ፤
# የቅድስት ድንግል ማርያም ዕለት፤ኅዳር፡፳፩፡ቀን፡፲፱ ፻፺፰ (21/1998፡ዓ/ም፣)

በዚሁ ዕለት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ በእሳት ሲቃጠል አየሁ። ከዚያ አንድ አበበ የሚባል ሕፃን ልጅ ኤርትራውያን ካሉበት ቦታ በእነርሱ እጅ ተይዞአል፤ መሬቱ ግን የኢትዮጵያ ነው። ልጁ እናት አባት የለውም እርሱን ከዚያ በረሃ ለማውጣት እኔ ወደዚያው ሄድኩ። ድንገት መሳሪያ የታጠቁ የኤርትራ ወታደሮች ይመጣሉ፣ ሕፃኑን ሲያዩት ኢትዮጵያዊ ነው፣ እነርሱም አውጥተው ሊገድሉት ይጎትቱታል። ከዚያ መሃከል እኔ ደርሼ እንዳትነኩት ስላቸው “አንተም ከዚህ አለህ”? ብለው ሊገድሉኝ እርስ በራሳቸው ሲገላገሉ። ተዋቸው ፍርዳቸው ነው ዘመዶቻቸው እንጂ አልቀውባቸው ነው፤ እባካችሁ ከመግደላችሁ በፊት አንድ ነገር እንድናገር ፍቀዱልኝ አልኳቸው፤ አሁን ማን ያልሞተበት አለና እንደዚህ የምትሆኑት ይህ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ስለሆነ ሁላችን በአንድ ሆነን እንጸልይ ስላቸው። አንዱ በጣም ተሰማውና የያዘውን መሣሪያ ከመሬት ላይ ጥሎ አንገቴን ጠምጠም አድረጎ ያዘና አዘነ አለቀሰ። ከዚህ በኋላ እኔም ልጁም ከመሞት ተረፍንና በአንድ ላይ ተቀምጠን ሳለን፤ ስሙኝ ያየሁትን ልንገራችሁ የኢትዮጵያና የኤርትራ ከብቶች በውሃ ጥም ሲያልቁ አየሁ፣ ውሃውም ከታች አንስቶ ወደላይ እየደረቀ ይመጣል፤ ከዚያ የሌላው አገር ከብት በዳር ቁሞ ይመለከታል አልኳቸው። አብረው የነበሩትን ኤርትራውያን እነርሱንም እዘኑ አልኳቸው። ከዚያም ያ በፊት ጸበሉን የባረከውን መምሕር ተመስሎ “አንተ የተናገርከው እንዲደርስ ገንዘብ ተቀበል” ይለኛል። እኔም መልሼ  እንድፈርድ ፈቀድክልኝ? ስለው። እርሱም መልስ ሳይሰጠኝ ከእኔ ተሰወረ። እኔም ተነስቼ ወደ ትልቅ ተራራ ወጣሁኝ፣ የለበስኩትም ነጭ ረጅም ቀሚስ ነው። ፊቴን ወደ ጸሐይ መውጫ አዞሬ በሀሳቤ አላህ አክብር የምል ይመስለኛል፤ ጨለማ መስሎ የነበረው ቦታ በሰሜን ጎንደር በወገራ አውራጃ በስተ ምሥራቅ በኩል በሚገኘው በሰንበትጌ ቅዱስ ሚካኤል አንስቶ እስከ ሰሜን ተራራ ድረስ የንጋት ብርሃን ይታያል። ጸሐይ በደመና ተሸፍና ብቅ ስትል፣ ከመሬት ተነስተው ትላልቅ ሕንጻዎች አብረው ጣት መስለው ብቅ ብቅ አሉ። ቦታውም ተራራና ገደል የነበረው በአንድ ጊዜ ወደ ሜዳ፤ ጥቁር የነበረው መሬት ወደ ቀይ እና አሸዋማ አፈር ተቀይሮ ለም መሬት ሆነ። ከዚያ ተራራ እየተንደረደርኩ ወርጄ ወደዚያ ቦታ ሄድኩ ፤ ደርሼ ልቀመጥ ስል አንድ ረጅም ጠይም ሰው ከብቶች እየነዳ ወደዚያ ቦታ ይሄዳል፣ በኋላው አንድ ጥቁር ወይፈን ተከትሎት ይመጣና ከከብቶቹ መሃል ገብቶ ያምስበታል። ሰውዬውም ከከብቶቹ ነጥሎ ሲያባረው እኔን ሊወጋኝ ወዳለሁበት ሥፍራ መጣ። እኔም ከነበርኩበት ዘልዬ ከገለባ ካብ ገብቼ አመለጥኩ። ያ ጥቁር ወይፈንም ዓይኑና ፊቱ ያስፈራል፤ የፊቱ ጸጉር እረጅምና የቆመ ነው። ከዚያ በኋላ ወጥቼ ከበጎችና ከፍየሎች ጋር ተቀላቀልኩ። በጎቹ በጣም የከሱና የደከሙ ናቸው፤ፍየሎቹ ግን በጣም የወፈሩና ደስ የሚል ያማረ ሰውነት አላቸው።ሰዎች ፍየሎቹን ይንከባከቧቸዋል በጎቹን ግን የሚረዳቸው ወይም የሚንከባከባቸው የለም።

በጎች ከፍየሎች በአንድ ተሰማርተው
የእነርሱ መዋያ አንድ ሆኖ ሜዳቸው
በፍየል እረኛ ሥቃይ ተቀብለው
ለበጎች እረኛ መለየት ተሳነው።
        ጣጥሎአቸው ሄደ በምኝታ ሰዓት እለያለሁ ብሎ
        ለእነርሱ ማደሪያ ጋጣቸውን ሊሰራ ሊያመቻች ቸኩሎ
        ሲንገላቱ አይቶ በሥምሪት ውሎ።
ሁሉም ተሰብስበው ሄዱ በጎዳና
የሚሄዱበትን አላወቁምና
ልባቸውን ከፈት ቃልህም ሲነገር ይስሙ በጥሞና።
        ጦም ውለው ጦም አድረው የሰው እህል ያልበሉ
        ስጋት የለባቸው ጌታን አመስግነው በሰላም ያድራሉ።

## <u>አቤቱታ ለአምላክ፤</u>

አገራችን በመጥፎ ሁኔታ በመውደቋ አንድ ቀን ፈጣሪዬን አምርሬ ተናገርኩት። ከሀገራችን ጀምሮ እስከ ስደት ዓለም በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን ግፍና መከራ አታይም?ወይንስ አትመለከትም። አንተን ብቻ በማመናችን አሕዛቡ ሁሉ ይስቅብናል፤እኛ ግን የአንተን ስም በደስታም ሳናስቀድም የኖርነበት ጊዜ የለም፤ ጠግበንም ሆነ ተርበን ተገፍተንም ሆነ ተደብድበን ወድቀንም ሆነ ተነስተን፤ እርሱ ያውቃል ጸሎታችን ይሰማናል፤ እርሱ ያለው ይፈጸማል ከማለት አልቦዘንም። አንተ ግን ረሳህን፣ ለሰይጣን አሳልፈህ ሰጠህን፤ በያለነበት ሰቆቃው በዛብን ። እስራኤልን ከተበተኑበት የሰበሰብክ አምላክ ለአብርሃም ለይሥሐቅ ለያእቆብ በገባሃላቸው ቃል ኪዳን መሠረት ቃለህን አላጠፍክም። ምንም እንኳ ያሁኖቹ ቢክዱህ ለእነዚያ ለተመረጡት ስትል የቀደስካትን ሀገር ኢሩሳሌምን እንዲወርሷት አደረግህ። ኢትዮጵያውያንም ምንም እኛ የአሁኑ ተውልዶች ብናስቀይምህም *በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅለህ በጦር በተወጋሃው ጎንህ የፈሰሰውን ደም በብርሃን ጽዋ በቅዱስ ኡራኤል እጅ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ረጭተህ፤* የእህል በረከት ወተትና ማር ይፍሰስብሽ ስትል የባረካትን ሀገር ለእነዚያ ለደጋጎቹ ለተባረኩት ለነአቡነ ተክለሃይማኖት፣ለእነ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣እንዲሁም ለደናግል ለመነኮሳት ሕይወታቸውን ለሃይማኖታቸው ሲሉ ላሳለፉት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ስትል ምሕረት አውርድልን ብዬ ጸሎቴን አድርሼ ተኛሁ። የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ጸሎቴን ሰምቶ በዚች ሌሊት መልሱን ነገረኝ። እንዲህም የሚል ነበር!!

<u>*የመጀመሪያቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት (ምዕራፍ 2፡ቁጥር፡18፣*</u>*)* ጀምሮ ያለውን ቃል ተነሳና አንብብ አለኝ። እኔም ወደያውኑ ተነሳሁና መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመርኩ፤ ቃሉንም አገኘሁት እንዲህም የሚል ነበር ። *ሎሌዎች ሆይ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞችም ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ።* በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገስ ምስጋ ይገባዋልና ኃጢአትን አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሱ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሱ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ዳግም ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም ተንኮልንም በአፉ አልተገኘበትም ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል አስፍሬዋለሁ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ገልጠው ለማያነቡ ሰዎች እንዲረዳቸው ብዬ ነው ከቁጥር፡፲፰ (18) አስከ መጨረሻው ያለውን መመልከት ትችላላችሁ። ግን ከዚያ መካከል ለእኔ በሚናገርበት ሰዓት አንድ እረጅም ወጣት ሰው የዲቁና ማዓርግ ያለው የኸነንማ እናነባለን ብሎ መልስ ሰጥቶት ተሠወረ። ከዚህ በኋላ ነው ሌላውን የገለጻልኝ ደግሞም ኢትዮጵያን ፈጣሪ እንዳልረሳትና እንደቆመላት ያወቅሁ ከዚህ ሰዓት ጀምሬ ነው።

## <u>1ኛ፤ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>

## የአማኑኤል ዕለት፤ኅዳር፡<u>፳፰</u>፡ቀን፡<u>፲፱፻፺፰</u> (28/1998፡ዓ/ም)

የአባቴ ቤት ይመስለኛል ትልቅ ድግስ ተደግሶ ከትልቅ አዳራሽ ብዙ ሕዝብ ተጠርቶ በውስጥም በደጅም ተቀምጧል። ሁሉም ሰው የወፈረና ቦርጩ የተንጠለጠለ ነው፣ ግን ሁሉም ሰው ከዚያ ድግስ አልበላም ግብዣውን የተጋበዘ አንድ መነኩሴ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ ነበርኩ አሳላፊው። ያ የተጋበዘው መነኩሴ በጣም ሰውነቱ በረኀብ የተጎዳና የደከመ ጥቁር ቀሚስ የለበሰ እርሱም ከድካሙ የተነሳ ምግቡን ሊበላ አልቻለም ማውረጃ የወይን ጠጅ የመሰለ ወፍራም መጠጥ (ጭማቂ ነገር) ብሰጠው "አሁን ይሄን አልጠጣም ሌላ ለስላሳ መጠጥ ስጠኝ" አለ። እኔም በረሀብ ተጎድተህ ነው እንዲህ የሆነከው አልኩት። ከዚያም ከትልቅ ወንበር ከፍ ብሎ የተቀመጠ ካባ የለበሰና በእራሱ ላይ ዘውድ የጫነ አንድ ሰው ፊቱ አይታይም መልሶም አስቀድሞ ምግቡ ተበልቶ እስከሚያበቃ ድረስ

አልተናገረም ነበር። በኋላ ግን ምግቡ ተበልቶ ካበቃ በኋላ ተናገረ። ባጠገቡ ማንም ሰው የቀረበው የለም። እርሱ ከላይ ነው ያለው፣ ሰው ግን ከታች ተቀምጧል። ያ ሁሉ ሰው ግን የለበሰው ልብስ ከወገቡ በታች ነው፣ እንጂ ከወገቡ በላይ ሁሉም ደረታቸውን ገልጠው ነው የተቀመጡት። ከዚህ በኋላ ከትልቅ ወንበር የተቀመጠው ሰውዬ ለእኔ "ያን ድግስ እንደሞላ ወደ ላይ አንሳው" አለኝ። እንጀራው ማቶት ከሚመስል ነገር ላይ ተቀምጦ በዚህና በዚያ ተወጥሮ(ተጠልፎ) በአውታር ተይዟል። እኔም ላነሳ ስሞክር አልቻል አለኝና፣ ኧረ ጌታዬ እኔ ደካማ ነኝ፣ ቁመቴም አጭር ነው እረዳት ያስፈልገኛል አልኩት። ከዚያ መካከል አንድ ረጅም ጠይም ዲያቆን መጥቶ ወደላይ ሲያነሳው ምግቡ ወደሰማይ ተወሰደ (ተነጠቀ)። የሚገርመው ግን ሁሉም ሰው ተጠርቶ ምግቡን ሳይበላው በዓይኑ ብቻ እንዳየው ሲቀርና ወደላይ ሲያርግ በጣም ግራ ገባኝ። ከዚያ በኋላ ያ ከትልቅ ወንበር ላይ የተቀመጠውን ሰው ግን ማንም አላየውም ምግቡ ከተነሳ በኋላ እርሱም ዲያቆኑም ተሠወሩ።

## <u>2ኛ፤ ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>

በአንድ ሌሊት ሁለት ነገሮች ነው ያየሁት። አንደኛው ድግሱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሚከተለው ነው። በድንገት ከትልቅ ጫካ ውስጥ እና ከትልቅ በረሃ ተደብቃ የነበረች አንዲት ረጅም ቀይ ሴት እርግዝናዋ በጣም የከበዳት ልትወልድ የተቃረበች ናት፤ አንድ ጠይም ረጅም ሰው እየመራት ከታች አንስቶ ወደላይ ሲያወጣት አየሁ። ከዚያም እኔን ጠርቶ"ና ደግፈህ ያዛት" አለኝ። እኔም እሺ ብዬ ሴትዮዋን ወገቧን ደግፌ ይዤ ወደ ላይ እየገፋሁ አወጣኋት። መንገዱ በጣም አስቸጋሪ ነበርና በእጃችን እየሟጠጥን እሳርና ደንጋይ እያዝን ወጣነው። ያ ሲመራት የነበረው ሰው ከእኛ አልፎ እርቆ ሄደ። መንገዱንም እየመራን ከዱሩ ውስጥ እንደወጣን በበረሃው አዲስ አስፓልት መንገድ አለ፣ ከተራራው አንስቶ የተሠራ ዝግዛግ የሆነ አዲስ ጥርጊያ መንገድ አገኘን። ያን ይዘን እየሄድን እያለ ፋሲካ ይመስለኛል ካህናቱና መነኮሳቱ ግብረ ሰላም ሲበሉ ውለው ሆዳቸው በጣም ሞልቷል። ከላይ ከተራራው ተነስተው ወደታች ይመጣሉ፤ ከመጠጥ ብዛትና ከጥጋብ የተነሳ ሰክረዋል፤ አንዳንዶቹ ጥምጥማቸውን አውልቀው ሻሻቸውን ይጎቱታል ፣አንዳንዶቹም ቆባቸውን አውልቀው የለበሱትን ብጫ ቀሚስ እየጎተቱ ከተራራው ተነስተው ወደታች መንገድ ይዘው ይሄዳሉ። ሰውዬውም ማለትም ሴትዮዋን ሲሚራት የነበረው እነርሱን ሲያይ መንገድ አሸርፎ ሄደ።እኔም አንዳንዶቹን ስለማውቃቸውና ሁኔታው ስላስጠላኝ ፊቴን ጋርጄ እንዳያዩኝ አድርጌ ሴቷን ይዤ በቀኝ ጎናቸው አለፍኩኝ። በዚህ መካከል አንድ የማውቃቸው መነኩሴ የመስሉኛል ከካህናቱና ከመነኮሳቱ ተነጥለው ተመልሰው ወደእኛ መጡና እርጉዟን ሴትና እኔን በመስቀል ባርከውንና አሳልመውን ከእኛ ተሠወሩ።

ያ ሴቷን ሲመራት የነበረው በሩቅ ሆኖ ይመለከተናል። አቀበቱን ጨርሰን ወጥተን ከተራራ ዘልቀን ሜዳ ላይ ደረስንና እርጉዟ ሴት የምትገባበት ቤት ትልቅ አዳራሽ ነው፣ የተዘጋጀላት። ነገር ግን ቤቱ ተዘግቶ ከዚያ አዳራሽ ውስጥ የብዙ ሰው ድምጽ ይሰማል። እንደደረስነም ሴትዮዋ ሂዳ በጓሮ ብቻዋን ተቀመጠች። እኔና በፊት ሲመራት የነበረው ሰውዬ "ፈቀቅ ብለን እንያት" አለኝ። እርሷ ግን ሽንት ቤት እንደሚጠቀም ሰው መስላ ነው የተቀመጠችው። ምጥ ይዟት ወይም ደክሟት ይሆን አለወቅሁም። ከዚያ መካከል ከተቀመጠችበት ላይ ጥቁር ውሻ ሂዶ ከጎኗ ይቀመጣል። እርስዋም ተነስ ካጠገቤ ጥፋ ከዚህ እንዳላይህ እያለች ስትናገረው። ያ ሲመራት የነበረው ሰው እንደዛ ስትል ሰምቶ አንድ የውሻ ቡችላ ይይዝና በእጁ አንገቱን ይዞ ጭፍልቅ አድርጎ ገደለው። ከዚህ ያለውን ሲገድለው ከዚያ ሴትዮዋ ጋር የነበረው ጥቁር ውሻ የት እንደገባ አልታየም ከፊታችን ተሰወረ። ሴትዮዋም ተነስታ ወደእኛ መጣች። ከዚህ በኋላ ነግቶ እርጉዟ ሴት የምትገባበት ቤት በራፉ እስኪከፈት ድረስ ከከብት በረት ተቀምጠን ሳለን፣ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ ማደሪያና መግቢያ አጥታ ወደእኛ እየተንቀጠቀጠች መጣች። እኔም ለእርጉዟ ሴትና ለእኔ ብርድ ልብስ በታች አንጥፌ በላይም ደርበን አብረን በአንድ ላይ ተኛን። ያችን ወጣት ሴት ልጅም በጎናችን አብረን ከእኛ ጋራ አልብሰን አስተኛናት። ያ ሰውዬም ከሩቅ ሆኖ ነው የሚጠብቀን የነበረ። ሲነጋም ከእኛ ተለይቶ ሄደ ሲሄድም አላየነውም እኛም ከደጅ እንደተኛን አነጋን (ነጋ)። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እንደሚጎበኛት ድሮም ተናገሮአል። ይች ምጥ የከበዳት ሴት ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከተሸፈነ ዱር ወደተራራ የወጣችው፤ ያ ያረገዘችውን መከራዋን ልትገላገለው፣ በውርደት ወድቃ ተሸሽጋ ከነበረችው በረሃ ወደ ተራራ ወጥታ የተቀመጠችው፤ የዓለም

ህዝብ ኃያልነቷንና ተገፍታ እንደተራራ የማትወድቅ መሆንዋን ፤እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ ሊያሳይ ሲል ነው። ተንቃና ተዋርዳ እንደማትቀር እግዚአብሔር በብዙ መንገድ እያሳየ ነው። ኢትዮጵያ የልጆችዋ ደምና እንባ ወደ እግዚአብሔር ዘልቆ ሂዷል። በምሕረቱ እንደሚጎበኛት በቀኝ እጁ እንደሚዳስሳት፤ ከጨለማ አውጥቶ ብርሃን እንደሚያለብሳት(እንደሚያበራላት)ራቡን ጥማቱን እንደሚያሰወግድላት፣ ከበሽታዋ እንደሚፈውሳት ዓለም በሙሉ ኃያልና ትልቅ ሀገር እንደሆነች እንዲያውቃት፣ ፈጣሪዋ ከእርስዋ ጋር እንዳለ ያውቁ ዘንድ ትምህርትም እንዲሆናቸው፣ በእርስዋ እንዲቀኑባትና ለካስ ለእርስዋ ፈጣሪ አለላት ይሉ ዘንድ ነው። ሰዎች እንድታውቁት የሚያስፈልገው ጉዳይ ቢኖር ፤ያረገዘችው ሴት ኢትዮጵያ ናት፣ ወጣቷ ሴትም ኤርትራ ናት። ሁለቱ ለወደፊት አብረው ይሆናሉ ምክንያቱም ሰው ያለው ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና የሚበልጠው።

## <u>ሰኔ፡፲፰፡ቀን፡፲፱፻፺፱</u> (18/1999ዓ/ም)

በዚህ ሌሊት ያየሁት ራዕይ፣ እንደሚከተለው ነው። እኔ የድሮ ካቶሊክ ካህናት የሚለብስቱን የቤተ-ክርስቲያን ቆብ የመሰለውን ለብሼ ይመስለኛል ወደ እሩቅ ሃገር እሄዳለሁ። የአንድ ሰው ድምጽ ይሰማኛል ሰውዬው ግን አይታይም ነበር። እኔ በሰውዬው ድምጽ ፍርሀት ይዞኝ አየገሰገስኩ ስሄድ ቆይቼ ዞር ብዬ ሳይ ፊቱን የተሸፈነ አንድ ጥቁር ሰው አየሁ። ከዚያ በኋላ መንገድ እያቀያየርኩ እሮጣለሁ፣ ሰውየውም ይከተኛል ሊይዘኝ ታቅርቧል። ድንገት ከትልቅ ተራራ ላይ የተሰራ የወታደር ካምፕ የመሰለ ትልቅ ግቢ አያለሁ፤ ወደዚያም እየሮጥኩ ስደረስ መጀመሪያ ያአየሁት ንጉሥ ሰሎሞን ያሰራትን ቤተ መቅደስ ትመስላለች። ከዚያች ስገባ ትንሽ መሻሎኪያ ያላት በር አግንቼ በዚያች አንገቴን ሳስገባ ሁሉም ሰውነቴ ሊገባ አልቻለም። ያም ጥቁር ስው ሊይዘኝ ተቃርቧል። ተነስቼ ሌላ በር ስፈልግ ድንገት ትልቅ በር ተከፍቶ አገኘሁና ዘልየ ገባሁ። ስገባም ብዙ ውሾች በሰው አንደበት ይናገራሉ፥ ሁሉም መጥተው ከበቡኝ። ከነርሱም መካከል አንድ ቀይ ውሻ አለቃቸው መጥቶ ሁሉንም በየስራቸው እንዲሰማሩ አዘዛቸውና እኔን ሰዎች ወዳሉበት አደራሽ እጄን ይዞ ወሰደኝ። ከዚያም ድሮ የማውቃቸው ሰዎች በተራ ተቀምጠው አገኘሁ ። አንዱ ከሁሉ በላይ ያለው መምህር ነው፤ መጽሐፍ ይዞ ያገላብጣል ሌሎቹ ደግሞ ስለ መጽሐፉ ያደንቃሉ። ከዚያ መካከል እኔን ከእንጨት በተሰራ ከትልቅ ቆጥ አልጋ ላይ ወስዶ ያን ትልቅ መጽሐፍ ከያዘው ሰው፣ በስተቀኝ አስቀመጠኝ። ከዚያም በኋላ ወደበረሃ ተወሰድኩ፣ የሄድኩበትም የበረሃ አገር አውሮፓ ውስጥ ኖሮይ ነው።

በበረሃው ውስጥ እየሄድኩ ሳለሁ፣ ድንገት የማላወቃቸው ሁለት ሰዎች በኋላየ ይከተሉኛል፤ደግሞም በአንድ ጊዜ በትልቅ ጎዳና ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን አየሁ። ያለቀና የተቦጫጨቀ አሮጌ ልብስ ለብሰው ምግብ ፍለጋ ይንከራተታሉ የሚሄዱትም በሰልፍ ነው። ከሚከተሉኝ ሰዎች አንዱን የት ሊሄዱ ነው ብዬ ስጠይቀው “ምሳ ለማግኘት ተራ ልይዙ ነው” አለኝ። እኔም ደግሜ እንዴት? ሰዓቱ ገና አልደረሰ ስለው “አይ ካሁኑ ተራ ይዘው ካልተሰለፉ በኋላ አያገኙም” አለኝ። እኔም ሄጄ ልቀላቀል ስል አንድ ሰው ከናህስ የተሠራ የወታደር ቆብ የለበሰና በእጁ ጦር የያዘ ከኋላዬ ሆኖ “እንዳትሄድ” ሲለኝ፣ አብረውኝ ያሉት ሰዎች ወደኋላ እኔን መለሱኝ። እነዚያን ምግብ የሚፈልጉትን ወጣቶች ወታደሮቹ መንገድ አስቀይረው በግራ በኩል ወደሰሜን ወደ መጡበት መለሷቸው።

እኔም የእነዚያን ስቃይና ረሃብ እንዴት እንደጠናባቸው ሳይ እጅግ በጣም አዝኜ አለቀስኩ። ከሕዝቡ ጋር ነው የምቀላቀል ስል፣ ወታደሩ አሁንም መጥቶ መለሰኝ። እኔም በሕዝቡ መራብ እያለቀስኩ ሳለሁ፣ እነዚያ አብረውኝ የነበሩት ሁለት ሰዎች ወደ ምሥራቅ በረሃ ወሰዱኝ። በዚያ በረሃ ውስጥ እየሄድኩ ሳለ፣ ለአትክልቶች መዝሙር ይዘመራል፤ አትክልቶቹም አብረው ይዘምራሉ፤ የሰውም ቅርጽ ተደርጎላቸው ይስቃሉ። እኔም ነገሩ ገርሞኝ ይህ ምን ነገር ነው? እያልኩ ሳስብ አብረውኝ ካሉት አንዱ “ዛሬ የአትክልቶች ቀን ስለሆነ ነው ለነሱ የሚዘመርላቸው” አለኝ። አሁንም በዚያ እየተገረምኩ ስሄድ ሳለ፥ በሸና ዛፍ ዙሪያውን የተከበበ ከትልቅ ወንዝ ደረስኩ፤ የውሃውም ድምጽ የተለየ ቃና አለው፤ በሰው አንደበት ሳይሆንስ በመላእክት አንደበት የሚዘመር መዝሙር ነው የሚመስለው፣ ጭሆቱ ልብን ይመስጣል። ከዚያ እንደደረስኩ ብዙ ትኩስ ነጫጭ ዳቦ (ወይም ህብስት) እንደ ክምር ተከምሮ አገኘሁ። ያን አይቼ አሁንም ገረመኝ ፤ምክንያቱም በፊት ውሾች በሰው አንደበት ሲናገሩ ሁሉም

በአንድ አለቃቸው ትእዛዝ ተቀብለው እጅ ነስተው ሲሄዱ። ሁለተኛው የህዝቡን እንጀራ ፍለጋ በሰልፍ መውጣትና ምግብ እንዳያገኙ በወታደር መከልከላቸውን። መልሶም ወደመጡበት በግድ እንዲመለሱ መደረጉ። ደግሞም ረሃቡ እንዴት እንደጠናባቸው ሳይ፣ ከዚያም እኔን ወደ ሕዝቡ ሂጂ እንዳልቀላቀል መከልከሌና ወደበረሃ ሂጂ ስለአትክልቶች መዝሙር ሲዘመርላቸው በማየቴ። በመጨረሻም ወደትልቅ ወንዝ ወርጂ እንደ ክምር የተከመረ ብዙ ህብስት ነጫጭ ዳቦ በማግኘቴ (በማየቴ)በዚህ ሁሉ እየተደነቅሁ ሳለሁ ከእንቅልፌ ነቃሁ።

ሰማያዊ ህብስት በምድር የታየው
ፍጥረት በልቶ ይደር አሁን ይመግበው
ቃልህ ይድረስና ሰው ሁሉ ይወቀው።
　　ያን ቅዱስ መጽሐፍ ልብ ብሎ ሳያየው
　　ልቡ ተሸፍኗል አላስተዋለም ሰው።
ወንድሙ ወንድሙን በከንቱ ሲገለው
መጨረሻው ጊዜ ደርሶ እያየው ነው
ሁሉም ሂዶ ሰግዷል ተሳስቶ ለአውሬው።
　　ዓመታት አስቆጠርን ጠፍቶብን መላው
　　ሲፈራረቁብን ረሃብ በሽታው
　　ገላችን ልብስ አጥቶ ጸሐይ ሲመታው
　　እየወጣ ሲሄድ ከሞት የተረፈው
　　በሄደበት ሁሉ አንድ ቀን ሳይደላው
　　የሰውም አይደለ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው
　　ችሎታ በሌለው በሥጋ ለባሹ አናመካኝ በሰው።
በውስጥም በውጭም እሳት የተጫረው
አላወቅንም እኛ ምክንያቱ ምንድር ነው
የኢትዮጵያ አምላክ መአቱን አቁረው
አለቀ ፍጥረትህ ምክንያት በሌለው
ቸሩ ፈጣሪያችን እባክህ ታደገው።
　　እጃችን ዘርግተን የምናይ አንተን ነው
　　እረዳት አይመጣም አንተ ካላዘዝከው።
ረሃቡ ጥማቱ በሽታው አይሎ በፍጥረትህ ላይ
ምን አጥፍተን ይሆን በዛብን ስቃይ
እጃችን እንዘርጋ በህብረት ወደ ላይ
እንባችን አፍስሰን እንጩህ ለአዶናይ
ርኅሩህ ነው እርሱ ፊቱን ይመልሳል በደላችን ሲያይ
አንባችን ያብሳል ከጉንጮቻችን ላይ።

## <u>ራዕይ ስለ ሀገር፤</u>

## የቅዱስ፡ሚካኤል፡ዕለት፤ሐምሌ፡<u>፲፪</u>፡ቀን፡<u>፲፱፻፺፱</u> (12/1999፡ዓ/ም)

የቅንጅት መሪዎች ዓለም በቃይ እስር ቤት ፍርድቤቱ የወሰነባቸው (**ሐምሌ ፡፲፪ቀን፡፲ ፱ ፺፱ዓ/ም**) ሲሆን። በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ በውስጥና በውጭ ያለው ቁጣውን የአሰማበትና ወደ ፊት የሚያደርጋቸውን ነገሮች የገለጸበት ወቅት ነበር። እኔም ይህን ስሰማ ኢትዮጵያ አገራችን እንደ ጎረቤታችን ሱማሌና ርዋንዳ ትሆናለች ብለው እነ አቶ መለስ እንደ ተናገሩት እንዲህ አይነት ችግር ያጋጥማትን ይሆን ብዬ ክፉኛ ፍርሃትና ስጋት አደረብኝ። በዚህ የተነሳ ከታሰሩበት ቀን ጀምሬ በአለማቋረጥ ፈጣሪየን በኀዘን በለቅሶና በጸሎት ምህረት እንዲያወርድ ለመንኩት። ***ሐሙስ ቀን የቅዱስ ሚካኤል እለት ከሌሊቱ አራት ሰዓት (4:00)*** **ከምኝታ ላይ እንዳለሁ፣ አንድ ቀይ ሰው ይመጣና *“ለምነው የምታስቸግረኝ”* ብሎ ፤ከምኝታዬ አስነስቶ ወደ ውጭ አውጥቶ ይወስደኛል።** ከተባለው ቦታ

ስንደርስ ሁለት እረጃጅም ሰዎች ብዙ ኬሻ(ወይም ጆንያ)ደርድረው ይጠብቃሉ። እያንዳንዱ ኬሻ ክብደቱ ከመቶ ሃምሳ ኪሎ በላይ ይሆናል፥ በጣም ተጠቅጥቆ የተሰፋ ነው። ውስጡ ምን እንደሆነ አላውቅም። ያን ኬሻ ሁለት ሰዎች እያነሱ ለሕዝቡ ያሸክሙታል ሕዝቡም ተሸክሞ እየተጨነቀ በድልድይ በታች አድርጎ ወደ ሜካ ይጓዛል። አንድ ቀይ ሰው ነጭ ልብስ የለበሰ እኒያ ሁለት ሰዎች እያሸከሙ ሲሰዱ ቁሞ ዝምብሎ ያያል። በመጨረሻ ለኔ "ና ተሸከም" ይሉኛል። እኔም እህ አልኩና ተገርሜ አንገቴን ነቅነቅ አድርጌ ስቁ ፣ለመሆኑ በምን አበሳዬ ነው ይህን የምሸከም ቢሆንም አቅሜ የምችለውን እንጂ ያላቅሜ እንዴት ይሆናል ብዬ፣ ለዚያ ለቆመው ቀይ ሰው ስመልስለት። እኒያ ሁለቱ አሸካሚዎች ለሁለት አንስተው ለእኔ ሊያሸከሙ ቁመው ይጠብቁ ነበር። እኔ ግን አልፈለኋቸው ሄድኩ። ያ የቆመው ሰውዬ ለሌላ ሰው እንዲያሸከሙ አዘዛቸው፣ ሥራቸውን ጨርሰው ሦስቱም በአንድላይ ተሰወሩ። እኔም ምን ሊያሳየኝ ወይም ምን ሊያሰማኝ ይሆን እያልኩ፣ የቀረውን ሌሊት ቁጭ ብዬ አነጋሁት። በጧት ተነስቼ የዘወትር ጸሎት አድርሼ ጌታዬን አመስግኜ ቸር ወሬ አሰማኝ ብዬ ከቤት ወጥቼ እንተርኔት ላይ ወደ ላይብረሪ እየሄድኩ ሳለሁ፣ አንድ ሰው ቴክስት አደረገልኝ፣ ቴክስቱን ሳይ መሪዎቻችን በነጻ ተለቀቁ የሚል ነበር። እኔም በደስታ ተውጬ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ መንገዴን ቀጠልኩ። ላይብረሪ ደርሼ እንተርኔት ገብቼ ሳይ ነገሩ የተገላቢጦች ሆኖ አገኘሁት፣ ታሳሪዎቹ ጥፋተኛ ሁነው በጥፋታቸው ሕዝብንና መንግሥትን ይቅርታ እንደጠየቁ የሚል ጽሑፍ ነበር፣አይቼ የአነበብኩት።

እንግዲህ ሁለት መቶ የሚሆን ሕዝብ የተጨፈጨፈው ህጻናትና አዛውንቶች በጠራራ ጸሐይ የገደሉ እነሱ ሁነው ተገኙ ማለት ነው ፣አይ ይች ድራማ እንደ ተሰራባት መሆኑን ወዲያውኑ ነገሩ ገባኝ። ለማንኛውም ቀኝም ነፈስ ግራ፣ ለጊዜው ለወያኔ ነገሩ እርገብ አለለት። መለስም ከግብረ አበሮቹ ጋር ሆኖ ፪ሺ ዓመትን በጭፈራ አሳለፈ። ሕዝቡና ታሳሪዎቹ ግን ውርደትን እፍረትንና ሽንፈትን ተከናነቡ። ግማሾቹ ታሳሪዎች አንበሳ ገዳይ መስለው እየፎከሩና እየጨፈሩ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ተጓዙ። ሁለት ዓመት እስር ቤት መቆየት ትልቅ ጀብድ የሰሩ መስሎአቸው በነእሱ ስም የሞተውን ሕዝብ ቤተ ሰቦች ሳያተዛዝኑ ወደ ውጭ ፈርጥጠው ሂደው ጉሮ ወሸባዬ እያሉ ቀለዱበት። ውጭ ወጥተውም ወያኔን ትተው እርስ በርሳቸው ተዘራጠጡ ፣አንዱን አምባ ገነን ሌላውን የስልጣን ጥመኛ እየተባባሉ ሕዝቡ በጧት አስታውቄን ቢላቸው፣ ቆዩ አንድነን እያሉ ሕዝብ የታሰረበትን ፣የሞተበትን፣ የተሰደደበትንና ንብረቱን የተዘረፈበትን፣ በመጨረሻ መና አደረጉት። በኋላም ከሦስት ተከፍለው አንድ የነበረውን ሕዝብ ከፋፍለው ወያኔ በሕዝቡ ላይ መልሶ እንዲጨፍርበት አደረጉ። ግማሾቹም ከዚያው ከወያኔ ጉያ መልሰው ተቀረቀሩ ይብላይ፣ ለሕዝቡ እንጂ። እንግዲህ ማስተዋል ያለባችሁ ያነ ሽክም ለህዝቡ ወደ ፊት የሚደርስበትን ስቃይ መከራና ችግር የሚገልጽ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

## <u>ራዕይ ስለ ሀገር፤ጥቅምት</u> ፤፷፥ቀን፡ ፪ሺ (8/2000፡ዓ/ም)

ስለ ብርሃኑ ነጋና ስለ ብርቱካን ሚደቅሳ የአየሁት፣ እነሱና ሌሎች ሰዎች ሁነው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ትልቅ አዳራሽ ውስጥ በራፉ እንደ ተዘጋ በብረት አጥር የታጠረውን ግቢ ዘለው ይገባሉ። እኔም እነሱን ተከታትዬ ግቢውን ዘልዬ ልገባ ስል፣ አንድ ሰው ይመጣና በራፉን ይከፍትልኛል። በዚያ ገብቼ እነሱን ሕዝቡ በተሰበሰበበት መሃል ስፈልግ ብርቱካንን አግኝቼ ይዣት ወደ ውጭ አወጣዋት ፣ብርሃኑ ግን ከዚያ ውስጥ ገብቶ ተሰወረ። በኋላ ከአዳራሹ ወጥቼ መንገዱን ይዤ ስሄድ ወደ ኋላ ዞር ስል ብርሃኑና ሌላ የማላውቀው ሰው ፣ሁለቱ ይከተሉኛል። ለብርሃኑ እንዲህ ያለ ስህተት ትሠራለህ እያልኩ እወቅሰዋለሁ፥ በሉ ተከተሉኝ ብዬ መንገዴን ቀጠልኩ። በሜካ ውስጥ ተደብቀው ሰዎች በነ ብርሃኑ ላይ ድንጋይ ይወረውሩባቸዋል፣ ብርሃኑ ቆም ብሎ ድንጋዩ ወደ መጣበት አቅጣጫ ሲመለከት አንድ ሰው በሜካው ተደብቆ እጁን ብቻ አውጥቶ ለብርሃኑ ይጠቅሰዋል። እኔም ዝም ብለህ ተከተለኝ አልኩና መንገዱን ይዤ ወደፊት ገሰገስኩ። አሁንም ወደ ኋላ ዞር ብዬ ሳይ ሁለት ሰዎች ማከስ የለበሱ በብርሃኑና በጓደኛው ላይ ከመንገዱ ዳር አውጥተው ጥለው ቃላቱን መአስቀመጥ አልፈልግም ብቻ በዚህ በአውሮፓ ያለውን ቆሻሻ ሥራ ይፈጽሙባቸዋል። እኔም ያን ነገር ሳይ በስመ አብ ፣ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ አልኩና ፣ዞር ብዬ መንገዱን ይዤ ትልቅ ወንዝ ወደ አለበት ስፍራ እሮጣለሁ። አሁንም ዞር ብዬ ወደ ኋላ ሳይ እነሱን ትተው እኔን ይከተሉኛል። እኔም በፍጥነት ወንዙን ተሻግሬ ከትልቅ ተራራ ሂጄ ወጣሁ። እነዚያን ፊታቸውን የተሸፈኑትን ያነ ወንዝ

ሞልቶ አላሻግራቸው  ሲል፣ ወደ ነበሩበት ቦታ ተመልሰው ሄዱ። **እንዲሁ በነሐሴ ወር፤ በ፲፱፻ ፺፰(19/98፡ዓ/ም)** የቅንጅት ዓለም አቀፍ ድርጅት ተደራጅቶ በአውሮፓ በአሜሪካ እንዲሁም በአፍሪቃና በእሲያ አገሮች እየተንቀሳቀሰ ድርጅቱን እያጠናከረ በአለበት ወቅት የአየሁት ራእይ ፣እንዲህ የሚል ነበር። ስብሰባ ሲያካህዱ የስብሰባው ፕሮግራም በመስቀል በካንህ ትባርኮ በጸሎት እንዲጀመርና ፕሮግራሙ ሲያልቅም እንዲሁ በካህን የጸሎት ማሳረጊያ ተደርጎ እንዲዘጋ የሚል ነበር። ይህንም ለአንድ ለድርጅቱ ጸሐፊ ነገሩን ገልጨላቸው የሰጡኝ መልስ እንዲህ የሚል ነበር። "እኛ የሃይማኖት ችግር የለብነም" አሉኝ፣ ራእዩ አልተገለጠላቸውም ነበርና። የመለስ አፍዝዝ አደንግዝ እጽ መህተትና አስማት ከበታተናቸውና ከአፈራረሳቸው በኋላ ግን በጣም ሳይሰማቸውና ሳያዝኑ እንዳልቀሩ እገምታለሁ።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>
## ጥቅምት፡<u>፳፮</u>፡ቀን፡ <u>፪ሺ</u> (26/2000፡ዓ/ም)

ስለ ሀገር የአየሁት እኔ ከአንድ ከሞተ ወታደር ጋር ስለ ሀገር እነጋገራለሁ ደግሞም ከፊታችን ስንዴ የሚያጭዱ ሰዎች አሉ። ከዚያ መሃከል ዶክተር ኃይሉ አርአያ ይመጡና "እኛ ምን እናድርግ በአቶ መለስ ታዘን ወደ ፊት ግፋበት ቀጥሉ እንዳትመለሱ ተብለን ትእዛዝ ተሰጥቶናል" ብለው ስንዴ ለሚያጭዱት ሰዎች ይናገራሉ።  ይህ የነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቡድን በአሜሪካና ፤ በካናዳ እየተንቀሳቀሰ በነበረበት ወቅት ነው።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤ታህሳስ፡፬፡ቀን፡ ፪ሺ (4/2000</u>፡ዓ/ም)

አሁንም ስለ ብርሃኑ ነጋና ስለ ብርቱካን ሚደቅሳ የአየሁት እነሱ በአንዲት *አሮጌ ቮልስ ቫገን ነጭ መኪና ተሳፍረው ከሰሜን ወደ ደቡብ ይመጣሉ።* ከእነሱ በኋላ ሦስት ወታደሮች ፊታቸውን ተሸፍነው በሞተር ሳይክል ይከተሏቸዋል። ሰው ከሌለበት ቦታ ሲደርሱ መኪናዋን ያስቆሟታል። አስቁመው ብርሃኑን እጁን ይዘው ከመኪናው አውርደው ተከተለን ይሉታል፣ እምብኝ አልሄድም ሲላቸው ፊቱን በጨርቅ ሸፍነው አፍነው ገደሉት። ብርቱካንን ግን ከመኪናዋ አውጥተው ውጭ ጥለዋት ሄዱ። ብርቱካን ፊቷ ተጋርጦ ጥርሷ ገጦ ሰውነቷ አልቆ ወዲያና ወዲህ እያለች ብቻዋን ታለቅሳለች። አንዳንድ ሰዎች እየመጡ  ያዩአታል።  እሬሳውን የሚያነሳው ሰው የለም። ሰዎች እያዩት ብቻ ይሄዳሉ። እኔን አንድ ነጭ ፈረስ ከልደታ ቤተ-ክርስቲያን ይመጣና ከጫንቃው ሳልቀመጥ ጋማውን ብቻ ይዤ ወደ ዚያ ሥፍራ ወሰደኝ። ከዚያ ሂጄ ከወደቀበት ላይ አይቻው ተመለስኩ። የእሱን አማሟት ለእኔ ለሆኑት ሰዎች ሂጄ እንድናገር ፈረሱ ወደ ከተማ ይዞኝ ሄደ። ከተማ ገብቼ ለሰው ስናገር ፈረሱ ከኔ ተሰወረ።  ሰው ሁሉም ሂዶ እያየው እየተገረመ ዝምብሎ ይመለሳል እሬሳውም ጥርጊያ ላይ ወድቆ ሳይነሳ ቀረ።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤በየካቲት ወር፣፪ሺ</u> (2000፤ዓ/ም)

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሦስት ሰዎች ላይ "እባካችሁ ተስምስምታችሁ ምሩን እኛ ልንሞት እናንተን ምን እንደዚህ አደረጋችሁ" እያለ አንገቱን ደፍቶ ከእግራቸው ላይ ወድቆ ይማጸናል። ሁለቱ ሰዎች ልባቸው በኀዘን ተነክቶ አንገታቸውን ወደ  መሬት ደፉ፣ አንደኛው ግን አሻፈረኝ ብሎ ከጓደኞቹና ከሕዝቡ ተነጥሎ  ሄደ።  ይኸውም የሰዎቹን ስም ዝርዝር መጥቀስ ይቻላል። ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም እንጂነር ኃይሉ ሸዋል ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ናቸው።  የሕዝቡን ምሬትና ሰቆቃ አይተው እንደ ሕዝቡ አንገታቸውን የደፉ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም እና እንጂነር ኃይሉ ሸዋል ሲሆኑ የሕዝቡን ሰቆቃ ምሬትና ችግር እያየ አልስማማም ብሎ ተነጥሎ የሄደው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው።

## <u>አስደንጋጭ ራዕይ፤በኢትዮጵያ፤</u>
## <u>የአቡነ፤አረጋዊ፤ዕለት፤መስከረም ፡፲፬፡ቀን፡፪ሺ፩</u> (14/2001፤ዓ/ም)

በብዙ የሚቆጠሩ ክንፍ ለክንፍ የገጠሙ አይሮፕላኖች ከምሥራቅ ተነስተው ወደ ሰሜን ይበራሉ፤ከነ እርሱ የሚወጣው ጢስ እንደ ጉም ሰርቶ ሰማዩን ሸፍኖታል። ከጉሙ በላይ ብዙ አሳዎች ይርመሰመሳሉ አይሮፕላኖቹ ሌላ ነገር አልጣሉም። ያነ ጉም በአንድ ጊዜ ወደ ዝናብ ይቀየራል የሚወርደው ዝናብም ምድርን ሸፈናት፣ ተራራውም ሜዳውም በውሃ ተጥለቀለቀ፣ ከመሬት በላይ የአሉትን ፍጥረታት በሙሉ ዋጣቸው። እኔ ከትልቅ ተራራ ላይ ወጥቼ ስመለከት ፣ፕሬስደንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ቆራጣ ነጠላ ለብሶ ብቻውን በድልድይ ውስጥ ሲሽሎከለክ አየሁት። እኔም አንተ ብቻህን ከዚህ አለህ ስለው ዞር ብሎ ሳያየይ መልስ ሳይሰጠኝ በድልድዩ ውስጥ ተሰወረ። በእንዲህ እንዳለ አንድ በደም ሰውነቱ የተሸፈነ በጣም ትልቅ ቀይ ሰው፣ ስሙ ገባር የሚባል የትግራይ ተወላጅ የሆነ ከባሕር ብቅ አለ። ሁለት ኤርትራውያንም ተከታትለው ወጡና እሱን ሊይዙ ይሯሯጣሉ፣ እሱም ከነእርሱ ለማምለጥ በባሕሩ ላይ ይሮጣል፣ ሊይዙት ሲቃረቡ እንዳትይዙት ጥፋተኛው ማን መሆኑ ሳይታወቅ ስላቸው ፣እነሱም መልስ ሳይሰጡኝ ፊታቸውን አዙረው ከወጡበት ባሕር ተመልሰው ገቡ። ያነ በደም ሰውነቱ የተሸፈነ ሰውም እኔ ወዳለሁበት ተራራ ዘልቆ መጣና ካላይ መጥቶ ተቀመጠ በዚህ ላይ ነገሩ ተፈጸመ።

## <u>ሁለተኛው ራዕይ፤በኢትዮጵያ፤</u>

## የቅድስት፣ባአታ፣ዕለት፤ጥቅምት፡፫፡ቀን፡ ፪ሺ፩ (3/2001፤ዓ/ም)

ቀኑ ዕለተ ሰንበት ነበር፣ በዚያን ሌሊት ያየሁት ራዕይ። ሁል ጊዜ የሀገራችን ሁኔታ ያስጨንቀኛል ምክንያቱም በሁለት ሺህ ዓመተ ምህረት መግቢያ ዋዜማ እለት መንግስት ቃል የገባውን ለሕዝቡ ሙሉ በሙሉ በተግባር አላሳየም። ሌሎችም ሕዝቡ ተስፋ የጣለባቸው ተስፋ ቢስ ሁነው እየታዩ ነው። ስለዚህ የዚች አገር እጣ ፈንታዋ ለወደስተፊቱ ምን ይሆን እያልኹ እጨነቅ ነበር። የዘወትር ጸሎቴን ደግሜ ከዚያም ስለ ሀገራችን ሁኔታ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን እንደ ምለምነው በዚያን ሰዓትም አጥብቄ ለመንኩት፣ የሀገሪቱ እና የሕዝቡ የመከራ ኑሮ ስለ ሚያሳስበኝ ልመናየን እንደ ጨረስኩ ጌታዬን አመስግኘ ከአልጋየ ወጥቼ ተኛሁ። በምኝታ ላይ እንዳለሁ ሰዓቱ ከሌሊቱ አራት ሰዓት ገደማ ይሆናል ፥ የሚያስጨንቅና የሚያስደነግጥ በሰውነቴ አንዳች ነገር ወረደ። ያየሁት ራእይ እንደሚከተለው ይሆናል። አንድ የፈረንሳይ ንጉሥ ለወገቤ የምታጠቅበት ሽርጥ ለእጄ የምይዘው እረጅም ሽመል ሰጠኝና፣ አንዲት ትልቅ ቀይ ሴት እሷን ፈልጌ እንዳገኝ ወደ እሩቅ አገር እንድ ሄድ ያዘኛል። እኔም ትእዛዙን በጸጋና በደስታ ተቀብዬ ጉዞየን ጀመርኹ፣ ደጋውን ቆላውን ሜዳውን ተራራውን ስወጣ ስወርድ እረጅም ሰዓት ጨረሰብኝ። ድንገት መንደር ከሌለው ትልቅ ጫካ ውስጥ ገባሁ። የምሄድበት መንገድ ጠፍቶብኝ ወደ ፊት ወደ ኋላ ወደ ቀኝ ወደ ግራ እየዞርኩ ስመለከት፣ አንዲት ትንሽ ደሳሳ ጎጆ ቁማ አየሁ። ወደዛች ሄጄ ስገባ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ እግሮቿን ዘርግታ በጫንቃዋ ተንጋላ ተኝታ አገኘኋት። እሷን አይቼ ምንም ሳልጠይቃት እሷም ሳጠይቀኝ ወጥቼ ሄድኩኝ። ምክንያቱም የተላኩት ለትልቋ ሴት ነውና። በመንገድ እየሄድኩ ሳለ ድንገት ሁለት ሰዎች ከፊቴ መጥተው ቆሙ። እኔም ምን ሁናችሁ ነው ከዚህ መጥታችሁ የቆማችሁ ስላቸው አንደኛው ብድግ አድርጎ ሲመልስልኝ "በሐሰት እንደ ተፈረደባቸው ያልሰሩትን ሥራ እንደ ሰሩ አድርገው እንዲናገሩና በወንጀሉም ዳግም እንደሚጠየቁ" ብሎ ነገሩን ገለጸለኝ። እኔም የአንደኛውን ሰው የፍርድ ቤት ወረቀት ተቀብዬ ሳየው በዚህ ሀገር በየ በራፉ ተወርውራ የምትጣለውን ሊፍ ሌት(Leaf let) በራሪ ጽሑፍ ወረቀትን ትመስላለች። ውስጧን ገልጬ ሳያት ዓመተ ምህረትና ወይም ቀን አልተጻፈባትም ዝግዛግ የሆነ ጥቁር ማኅተም ብቻ ነው ያለባት። ያችን ወረቀት ይዤ ወደ ምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሄድኩ፤ሰውየውም ስጠኝ ሲለኝ አልሰጥህም አልኩት። ከግቢው ደርሼ ስገባ እንዳለ በእሳት ተለብልቦ ጠቁሮ አገኘሁት፣ ወደ ውስጥ ስገባ ሁሉም ነገር ተቃጥሎ ግድግዳው እና ጣራው ብቻ ቁሟል ከአካባቢው ሰው የሚባል የለም። ከቤተ-መንግሥቱ ወደውጭ ስወጣ በአንድ ጊዜ ቦታው ወደጫካ ተቀየረ ቤተ-መንግሥቱም ከበረሃ ላይ ብቻውን ተሰርቶ ያለ ይመስላል፥ ከአካባቢው ቤት የሚባል የለም። ከዚያ ማሃከል ጨንቆኝ ወዲያና ወዲህ ስዞር ድንገት ብዙ ቀያይ ከብት በሬና ላም ወይፈንና ጊደር ጎበዝ ጥጃና እንቦሳ ሆኖ በሦስት ተከፍሎ ከቤተ- መንግሥቱ ግቢ ሲወጣ አየሁት። ከዚያ ቀጥሎ ከበረሃው አንስቶ ትልቅ አውራ ጎዳና ይዞ ያ ሁሉ ከብት ወደ ተራራ ይወጣል ቀና ብየ ሳይ ቀይና ነጭ ቀለም ያለው ሰንደቅ አላማ ከተራራው ራስ ላይ ተተክሎ አየሁ። አንድ ሰው ይመጣና "ሂድና ንቀለው" ይለኛል። እኔም ነገሩ ሳይበርድና ሳይስተካከል አልነቅለውም አልኩት፣ ሰውየውም ሌላ ነገር ሳይናገር ከቦታ ተሰወረ። ትልቋ

ቀይ ሴት ኢትዮጵያ ናት ፤ ወጣቷ ሴት ኤርትራ ናት፥ <u>በገጽ 19 የታየው ከዚህ ላይም ታይቶአል።</u> በእንዲህ እንዳለ ከዚያ እልም ካላ ጫካ ውስጥ አልፎ አልፎ ጢስ ሲጤስ ይታያል። እኔም ብቻየን በኀዘን እና በጭንቀት ተውጬ ሳላሁ፣ ያች ፈልጋት የተባልኩት ትልቅ ቀይ ሴት ቀሚሷን እየጎተተች ከቤተ- መንግሥቱ ግቢ ውጭ አየኋት፣ ወደ እሷ እየሮጥኩ ስሄድ እሷም የተዘጋጀ ምግብ ይዛ ቆየችኝ፣ ያን ያቀረበችልኝን እንጀራ በሁለት እግር ጣቶቼና በያዝኩት ሽመል በትር ተመርኩዤ ፤ተሎ ተሎ ጉርስ ጉርስ አድርጌ በልቼ ከሷ ጋር ተለያየሁ። <u>በኋላ የወንዝ ግፈኛ የሰው ቀበኛ የሚል ቃል ተነገረኝ።</u> እንግዲህ ይህ አስደንጋጭና አስፈሪ ራእይ ነው። ወንዙም ግፍ የሚፈጽመው መንግሥት ሲሆን፣ ቀበኛውም የሰውን ምቀኝነት የሚያሳይ ነገር ነው። እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱና እንደ ምህረቱ ብዛት አገራችን ከዳግም ጥፋት፣ ሕዝባችን ከእልቂትና ከቅስፈት እንዲጠብቅልን፤ እኛንም በውጭ አገር የአለነውን በአንድ ላይ አስማምቶ እና አፋቅሮ እንድንኖር ያድርገን። ሁሉም ነገር በእሱ እጅ ያለና የተያዘ ስለሆነ ፣ለአገራችን አንድነት ለወገናችን ደህንነት እንዲሰጥልን፣ ከራብና ከጥማት፣ ከድህነትና ከርዛት፣ ከበሽታና ከሞት አላቆ ፣አገራችን በኃብት የበለጸገችና ሰላም የሰፈነባት እንድትሆን፣ የአንዱ የልዑል እግዚአብሔር ቸርነትና ፍቃድ ይሁንልን አሜን።

## <u>የካቲት:፲፰፡ቀን:፪ሺ፩</u> (18/2001፤ዓ/ም)

በዚህ ዕለት ያየሁት ራዕይ እንደሚከተለው ይሆናል ፥ ከሌሊቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ የዘወትር ጸሎት አድርሼ ሻማ አብርቼ ጌታዬን አመስግኘ ተኛሁ። መጀመሪያ በጣም ከባድ የሆነና እኔን የሚያንቀጠቅጥ ራዕይ ሳይ ተዝለፍልፌ ከመሬት ላይ ወደቅኹ። ከዚያ አንድ ሰው መጥቶ እጄን ይዞ አስነሳኝ። አስነስቶ የፈረሰ ሀገር መልሽ እንድሰራ ያዘኛል፣ ሀገሩም በቦምብ የተመታና የመሬት መንቀጥቀጥ የደረመሰው ይመስላል። ያን የፈራረሰውን እንጨትና ድንጋይ ለማንሳት ብዙ ጊዜ ፈጀብኝ ፣ልብሴ አልቆ ሰውነቴ በጣም ደክሞ ዝናብ እየመታኝ ከጭቃ ላይ ወድቄ ሳለሁ፣ ሥራውን ሳልጨርስ አንድ ሰው አንስቶ ወደ በረሃ ወሰደኝ። ከበረሃው ብቻየን ተቀምጬ በኀዘን ላይ እንዳለሁ፣ ከኢትዮጵያ ተነስተው ሦስት ትላልቅ ሰዎችና አንድ ሕጻን ልጅ ሁነው ብዙ መጽሐፍ ይዘው ወደ እኔ መጡና ትላልቅ ጠፍጣፋ ድንጋይ ደራርበው፣ ከዚያ ላይ ትልቅ ቀይ የበግ አጎዛ አንጥፈው እኔን ነጭ ልብስ አልብሰው አስቀመጡኝ። እነሱ ከኔ በታች ተቀመጡ ፣ሕጻኑ ልጅ ከአንዱ ትልቅ ሰው ጋር ተቀምጦ መጽሐፍ ያገላብጣል። እኛ ያለነበት ቦታ ኮረፍታና አሸዋማ የነበረው መሬት፣ በአንድ ጊዜ ወደ ሜዳ ተቀየረ ደርቆ የነበረው ረጥቦ እሳርና እህል አብቅሎ አየሁት። ከኢትዮጵያ በሰሜን ጎንደር በምሥራቅ በኩል በጣም ጠባብ በሆነች መንገድ አንድ ጠይም ሰው ሽበት የቀላቀለ ነጭ ልብስ የለበሰ በዚያ ቦታ አድርጎ ወደ እኛ መጣ። ሰዎቹ ገና በሩቅ ሲመጣ አይተው መጣ መጣ ብለው ከተቀመጡበት ተነሱ። እኔም ከዚህ አስቀምጡት ብዬ ቦታየን ለቀኩኹ፣እነሱም "አንተ አስቀምጠው እንጂ"እያሉ በዚህ እየተጨቃጨቅን ሳለ ድንገት ሰውዬው ደረሰ። አጎዛውን አንስቼ አራግፌ ና ከዚህ ተቀመጥ ስለው፣አምጣው ብሎ ወደ ትልቅ ደረጃ ሂዶ ቆመ። እኔም ከእግሩ በታች ተበርክኬ ያን አጎዛ አነጠፍኩለት። እሱም እንደቆመ ራዲዮ የምትመስል ነገር ከጀሮው አስጠግቶ ያዳምጣል፥ ድምጽ ግን የላትም። "የኢትዮጵያ የአየር ማረፊያ ባልታወቀ ተመታ" አለና። ወዲያው የገበሬ ጦር ከዓባይ ሸለቆ አንስቶ እስከ ሸዋ ድረስ የንጥጦን አፋፍ ዘልቆ ከተማውን አዲስ አበባን ከቦ ሲያስጨንቀው አሳየን። ይህን ካሳየን በኋላ "ኢትዮጵያ ለአምስት ዓመት የእርስ በርስ ጦርነት ተፈረደባት" ብሎ ተሰወረ።

እኒያም ቀደም ብለው የመጡት አብረው ተሰወሩ። እኔም በድንጋጤ ተዝለፍልፌ ከመሬት ላይ ወደቅኹ። ኢትዮጵያን በአጠቃላይ ውድማ የምታህል አድርጎ፣ ሰሜን ጎንደርን በከፊል የምሥራቁን ክፍል ከሰንበትጌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን አንስቶ ፣እስከ ብራ ታዴዎስ ድረስ ቦታው፣ ደርቆ ለምለም የሚባል ነገር አይታይበትም። ከአርቃ ተራራ ከራሱ ላይ አንድ ትልቅ ዛፍ ብቻ ፣ለምልሞና ቁሞ ይታያል። ያነ አካባቢ በጣም ቀርቦ ታየኝ ወደዚያ ልሄድ ስል እኔ በአለሁበትና በኢትዮጵያ መሃል ጥቁር መሬት ከሁለት በጣም ተሰንጥቆ እንደ ትልቅ ገደል ሆኖ እየተቀጠቀጠ ፣ሊፈርስና ሊናድ ተቃርቦአል። እኔም ልሄድ አልቻልኩም በአለሁበት ቀረሁ። ተነስቼ ወደ በረሃ ብቻየን እያለቀስኩ ስሄድ ሳለ፣ ድንገት ብዙ ነጫጭ ድንኳን ተዘርግቶ አየሁና ወደዚያ ሂጄ ገባሁ። ስገባ አንድ ትልቅ ድንኳን በዙሪያው ሻማ ተቀምጦ ይበራል፣ በላይ የተለያየ መልክ ያለው መብራት እየበራ ከዛ ውስጥ፣ አንድ ትልቅ ቀይ ሰው ተቀምጦ "ያን ድንኳን አንሳና እንዳይዛባ አድርገህ መዝነህ ትከል" ይለኛል። እኔም ኸረ

ጌታዬ ብቻየን አልችልም እረዳት ያስፈልገኛል ሰው ይሰጠኝ ስል፣ አንድ ከሙታን የተነሳ ሰው እንዲረዳኝ ይታዘዛል። ለሁለት አንስተን ዘርግተን መወጠሪያውን ይዘን ስንተክል፣ በአንድ በኩል ይዘማል፣ በዚያ በኩል ሂጄ ሳስተካክል በሰውዬው በኩል ደግሞ ይዘማል፣ በዚህ የተነሳ ለምን አትረዳኝም ብዬ ከሰውየው ጋር ተጣላሁ። ከዚያ ብቻየን አስተካክየ ጨረስኩ ብዬ ለዚያ ትልቅ ሰው ነገርኩት። ሰውየውም "ለምነው የተጣላችሁ" ብሎ ጠየቀኝ። እኔም በሁሉ ነገር ስለ በለጥኩት ነው፣ ብዬ መልስ ሰጠሁት፣ በዚህ የተነሳ ያ አብሮ እንዲረዳኝ የታዘዘው ሰው በጣም ተበሳጨና ከእኔ ተለይቶ ሄደ። በኋላ ረጅም በትር ይዤ ከግቢው ወጣሁ። አሁንም ብቻየን ወደ በረሃ ሄድኩ በያዝኩት በትር እየተመረኮዝኩ ስሄድ ሳለ ፤በዚህ በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያውያን በቡድን በቡድን ሆኖ ጉም በመሰለ ጢስ ታፍኖ እየተንጫጫ አይግባባም አይደማመጥም ተከፋፍሎ ለየብቻ ሆኖ ምግብ ይመገባል(ይበላል)። እኔም ከዚያ ውስጥ ገብቼ ከእኔ ጋር ተስማምቶ አብሮ የሚሄድ ሰው ብፈልግ አጥቼ ተመልሼ ወደ በረሃው ስሄድ ፤ ድንገት ዞር ብዬ ሳይ በቅርቡ ከኢትዮጵያ የመጣች አንዲት ቀይ ወጣት ልጅ አይቼ በይ ከኔ ጋር አብረን እንሂድ ብዬ ስጠይቃት ፤እሷም ፍቃደኛ ሆና እሺ ብላ ስትነሳ፣ አንድ ጥቁር ሰው እጇን ይዞ አትሄጅም ብሎ አስቀራት። እኔም ብቻየን ተመልሼ ወደ በረሃው ሄድኩ። አምስት ሰዓት ላይ ከምኝታየ ነቃሁ።

## የካቲት፡፲፱፡ቀን፡፪ሺ፩ (19/2001፤ዓ/ም)

ለባለ ራዕዩ የተነገረው ወይም የተሰጠው ተስፋ በዕለተ ቅዱስ ገብርኤል ዕለት እንዲህ የሚል ነበር። አንድ ቀይ ሰው መጥቶ ከፊቴ ይቆማል "አይዞህ ለአንተ የአልኩትን ለማንም አልሰጥብህም" ይልና የምግብ አይነት የታሸገ ነገር ከፊቴ አምጥቶ ያሳየዋል፣ ነገር ግን አልሰጠውም። መልሶም "አንድ ነገር ይቀርሃል አለውና እሱን ከፈጸምክ የመጨረሻውን ምርቃቴን እሰጥሀ አለሁ" ብሎ ከፊቴ ተሰወረ። (መጋቢት 12ቀን፡2004 ፡ዓ/ም፤) ከሦስት ዓመት በኋላ ፤በዕለተ ቅዱስ ሚካኤል ዕለት፤ ያየሁት ራዕይ። በአቁማዳ የሞላ ነጭ ስንዴና ጤፍ ተሸክሜ ለም ከሆነ መሬት ላይ ጣልኩት ከጣልኩት በኋላ ቁጭ አልኩ ቀና ብዬ ሳይ አንድ ካህን ከዲንክ አልጋ ተቀምጦ ጤና ይስጥልኝ ብሎ ሰላምታ ሊሰጠኝ መስቀሉን ጨብጦ ሊነሳ ሲል። ብድግ ብዬ ኧረ ቄሴ በእግዚአብሔር እኔ እመጣለሁ እንጂ አንተ እንዴት ወደ እኔ ትመጣለህ፤አትነሳ ብዬ ሂጄ መስቀል ተሳለምኩ። "ካህኑም በመስቀል እያማተበ እንጀራህ ከፍ ይበል ሲሳይህ ይብዛልህ እያለ ምርቃኑን ከጨረሰ በኋላ" ከእኔ ተሰወረ።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>የካቲት፡<u>፳፩</u>፡ቀን፡<u>፪ሺ፩</u> (21/2001፤ዓ/ም)

በዚያን እለት የአየሁት ራዕይ የኤርትራ ጦር ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከቦታው ይንቀሳቀሳል፥ ፕሬዝደንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ጺሙን አሳድጎ እንደ እስኮትሽ ሰዎች ግማሹን ተላጭቶ ከራሱ ላይ ባርኔጣ ደፍቶ በሁለት እጁ ሰይፍና ጎራዴ ይዞ ከፈረስ ላይ ሆኖ ቀጭን ትእዛዝ ለጦሩ ያስተላልፋል። እኔ በዚያን ሰዓት በፈረስ ሁኜ እሱ ወደ አለበት ስፍራ ሄድኩ። ከዚያ ደርሽ እባክህ ተው የሚያልቀው እኮ የሁለቱም ወገን ነው፣ ችግሩ በሰላም ይፈታ እያልኩ ስለምነው፣ እሱ ግን አሻፈረኝ ብሎ የያዘውን ሰይፍ ለጦር አዛዡ ወረወረለትና "ሂዱ ግጠሙ" ብሎ ሲያዝ። እኔ ኧረ ተው አይሆንም ብዬ ከእግሩ ላይ ስደፋ እምብኝ ብሎ ሊሄድ ሲል፣ አንድ ወታደር ይመጣና በያዘው ሰይፍ ከአንገቱ ላይ አሳረፈበት፤ በዚያን ጊዜ ቀጥ ብሎ ቆመ፣ ነገሩም በዚህ አበቃ ጦርነትም አልተካሄደም።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>ሚያዚያ፡<u>፳፫</u>፡ቀን፡<u>፪ሺ፩</u> (23/2001፤ዓ/ም)

በሕይወት ያሉና ብዙ የሞቱ ሰዎች ተነስተው ከአንድ ትልቅ ሜዳ ላይ ተሰብስበዋል። አቶ መለስ የአደፈና የተቀደደ አሮጌ ልብስ ለብሶ ከሕዝቡ ተለይቶ ፈንጠር ብሎ ለብቻው ተቀምጦአል። እኔ ከሕዝቡ መሃል ቁሜ ግራና ቀኝ ተላብሸ ሁለት እጆቼን ወደ ሰማይ ዘርግቼ እስከሙቸ ነው የምትታገስ ተሎ አትፈርድም እያልኩ በመንፈስ መቃተት እያዘንኩና እያለቀስኩ እጸልያለሁ። ከሞቱት መሃል አንድ ሰው "እንዴ ይህ ሰው ዘንዶዉን አይፈራም" እያለ እጁን ወደ መለስ ቀስሮ ቀስ ብሎ አብረውት ላሉት

ጓደኞቹ በሽኩሹክታ ይነግራቸዋል። እኔ ግን እጆቸን ዘርግቼ ሰማይ ሰማዩን ነበር የማይ እስከ ዚያን ድረስ። በኋላ በደመና ተሸፍኖ ሰማዩ ወደታች ዝቅ ብሎ ወረደ፣ በውስጡ እንደ ነጎድጓድ እያገመገመ ይጮሃል፣ደግሞም ከዚያ ውስጥ እንደ ትል የሚብላላ ነገር አለ። እኔ ያን ከአየሁ በኋላ እጆቼን አዉርጀ ፊቴን ወደ ሕዝቡ አዙሬ አሁን ሊፈርድበት ነው፣ ሊፈርድበት ነው፣ እያልኩ እየጮሁ እናገራለሁ፣ በዚህ እንዳለሁ ከእንቅልፌ ነቃሁ። እንግዲህ ዘንዶውስ ማነው ዘንዶው ያለበት ሰውስ ማነው?።

## ራዕይ በኢትዮጵያ፤ግንቦት:፲፮፡ቀን:፪ሺ፩ (16/2001፤ዓ/ም)

በበረሃ ውስጥ ብዙ ሰው ተሰብስቦአል ከዚያ ውስጥ ሁለት ሰዎች ይጣላሉ አንዱ በላይ አንደኛው በታች ሆኖ ይደበድበዋል። አንድ ሰው ተነስቶ ኧረ ሴቶች ተጋደሉ እያለ ይጮሃል ሕዝቡ እየተሯሯጠ ሂዶ በላይ ሆኖ የሚደበድበውን ሰውየ በሃይል ጎትተው አስለቀቁት፣ ሲያስለቅቁት ሁለቱም ወንዶች ናቸው። ከአገላገሏቸው በኋላ በላይ የነበረው ሰውየ እየሮጠ ይሄድና ትልቅ መርግ ድንጋይ አንስቶ ለዚያ በታች ሆኖ ሲደበደብ ለነበረው ሰውየ በዚያ ድንጋይ ወገቡን ጨፈለቀው። ሕዝቡም ድንጋዩን ሲያነሳ ብትንትን አለ። መቼ ትልቅ ቀይ ሰው ነው፣ ተመቹ ደግሞ ጠይም ድቃቃ ነው። ከጨፈለቀው በኋላ የመቹ ሰውየ ወገን ሁሉም ሰው በጣም የሾለና (የሞጠሞጠ) በሁለት በኩል ስለት ያለው መርዛም የሆነ የከሰላ ካራ እያነሳ ለተመቹ ወገን ሊወጋ ያባራቸዋል። የመቹ ወገን ብዙ ናቸው የተመቹ ወገን ግን ጥቂት ናቸው ፣ከተመቹ ወገን የሆነ አንድ ሰው "ኧረ እባካችሁ እርዱን እያለ" ለመሃል አገር ሰው ይጣራል። የመሃል አገር ሰው ግን ከጎናቸው ቁሞ ዝም ብሎ ያይ ነበር፣ እንጂ አረዳቸውም። እኔ ልቤ በኀዘን ተሰብሮ እያለቀስኩ ሳለሁ፣ ከተጠቂው ወገን የሆነች ከአጥቂው ወገን ሁለት ልጆች የወለደች አንዲት ሴት ትመጣና "አንዴ ተነስቶበታል እያለች ለአጥቂው ወገን ድጋፏን" ትሰጣለች። ያ በድንጋይ የጨፈለቀዉ ሰውየ ማለትም አለቃው ፊቱ ደም ለብሶ ዓይኑን እያጉረጠረጠ በሕዝቡ መሃል ቁሞ ያያል። እኔም የሕዝቡን መሸበርና መሰቃየት አይቼ እንባየን እያፈሰስኩ ልቤ በኀዘን ተሰብሮ ይሰፈሰፋል። ይህን ጉድ ቁሜ አላይም ብዬ ከዛ ወጥቼ ስሄድ አንዲት የማላውቃት ትልቅ ሴት ትመጣና ና የሚሆነውን ነገር ዝም ብለህ ተመልከት ብላ ወደ ኮረፍታ የሆነ ስፍራ ወስዳ ታስቀምጠኛለች፣ ከአጠገባችን ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን አለ። ቁጭ ብዬ ስመለከት እኒያን ጥቂት ሰዎች ያ ብዙ ሰው እያባረረ ወደሜካ ውስጥ ሲያስገባቸው አየሁ። በዚህ እንዳለ ከእንቅልፌ ባነንኩ። ነገሩን ግልጽ ላድርግላችሁ እነህ ሁለት ሕዝቦች የኢትዮጵያ ጠላት የሆኑት የሰሜኑ ክፍል ናቸው ድሮ በአንድ ሁነው ኢትዮጵያን ያጠፉ አሁን እርስ በዕርሳቸው ሊፋጁ የቀረቡት። አጥቂው ከሰሜኑ ጫፍ ያለው ሲሆን ተጠቂው ደግሞ ቀጥሎ ያለው ነው። ያ ቁሞ ሲያይ የነበረውና እርዳታ ተጠይቆ አረዳም ያለው የመሃል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

## ራዕይ በኢትዮጵያ፤መስከረም ፳፬፡ቀን:፪ሺ፪ (24/2002፤ዓ/ም)

በዕለተ ሰንበትና በአቡነ ተክለሃይማኖት በአል የአየሁት ራዕይ። ለብዙ ሰዓት የሚያስጨንቅ አንዳች ነገር ከበላየ ላይ ተቀምጦ እንቅልፍ አልወስደኝ ብሎ ቆየሁ፤አምስት ሰዓት ላይ ከባድ እንቅልፍ ወሰደኝ። የአንድ ብሔር ሕዝብ ከሌላው ብሄረሰብ ሕዝብ ጋር ሳይቀላቀል ለብቻው በአንድ ላይ ተሰብስቦ ሳለ እኔ ሂጄ ተቀላቀልኩ። አንድ አፍሮ ገ/መድህን የሚባል ሰው አንተ ከዚህ ማን አመጣህ ብሎ ይጠይቀይና ጉንጮቼን አገላብጦ ይስመኛል። እኔም የአመጣ አመጣኝ ብዬ መለስኩለት። ከዚያ መሃከል አንድ ሰው ከተቀመጠበት ይነሳና "ሁሉም ድርጅቶች መጥተዋል እየመጡም ነው" ብሎ ለተቀመጠው ሕዝብ ይናገራል። እኔ ተነስቼ ቁሜ ሳይ በሰሜን በምሥራቅ በደቡብና በምዕራብ በአራቱ ማእዘን ጦር ተሰልፏል። ነገር ግን በሰሜንና በምሥራቅ አድርጎ በግመል በበቅሎና በአህያ የጦር መሳሪያ ጭኖ ወደ ምዕራብ ብዙ ሰው ወደ መሃል አገር ሲገርፍ አየሁት፣ ሁሉም ሰው ይስቃል፥ እኔ ግን ብቻየን አዝናለሁ አለቅሳለሁ። ከሕዝቡ ተነጥየ ብቻየን ያለ ጫማ በባዶ እግሬ እያዘንኩ ወደ በረሃ ሄድኩ አሁንም የዚያ ብሄረሰብ የሆኑ ሴቶች ሜዳ ላይ ተሰብስበው ዙሪያውን እንደ ውድማ ከትረው ነጭ ፕላስቲክ የመሰለ ነገር አንጥፈው በበላዩ ከሳውዲ ዓረብያ አገር የመጣ ብዙ ነጫጭ ፍንጃል(ወይም ስኒ) ባዶውን አስቀመጡበት። እነሱ ከአፋፍ ላይ ተቀምጠው ይንጫጫሉ ከጎናቸው ጥቂት ነጫጭ ድንኳን ተዘርግተዋል። ከዚያ መሃከል ሁለት ጳጳሳት ሴቶቹ ከአሉበት ይመጣሉ። እኔም ትጸልዩ

ይመስል ከዚህ ምልታደርጉ መጣችሁ ብዬ ስጠይቃቸው። አንደኛው ብድግ አለና "ፈርተን ይገለናል ብለን" ብሎ መለሰልኝ። እኔም በመቀጠል ማንን ነው የምትፈሩ? እግዚአብሔርን ነው? ወይስ ሰይጣንን ስለው፣ አንደኛው "ምናልባት ይህ ሰው ተልኮ ይሆናል" ብሎ ለጓደኛው በሹክሹክታ ይነግረዋል። ከዚያ በኋላ መሄዳቸውን ትተው ከእኔ ጎን ቆሙ። አንድ ሰው ነጭ ልብስ የለበሰ ከሩቅ ሆኖ ወደ ምሥራቅ ፊቱን አዙሮ ከአፋፍ ላይ ቁሞ የእመቤታችን ስም እየጠራ ይዘምራል ይጸልያል። እኔም በድምጹና በጸሎቱ ተመስጬ እሱ የሚለውን ተቀብዬ እጸልያለሁ። ተነስቼ ዞር ብዬ ወደ ኋላ ሳይ ጳጳሳቱ ከሴቶቹ ጋር ሂደው ተቀምጠዋል፣ ትጸልዩ ይመስል አሁንም ከዚህ መጥታችሁ ተቀምጣችዋል እልና በሃይል ቃል ተናግሬ፣ እግዚአብሔርና ሰይጣን ጦርነት ሊገጥሙ ነው፣ ግቡና ጸልዩ ብዬ ሳፋጥባቸው "ኧረ የመጣ እንደሆን ይገለናል" ሲሉ፣ እኔ ቁሜ እያለሁ አይገባትም እኔን ሳይገል እናንተን አይገልም አልኩና ወደ አንድ ትልቅ ነጭ ድንኳን ገብተው እንዲጸልዩ አዝዤ አስገባዋቸው። እኔ ከውጭ ተበርክኬ እየጸለይኩ ሳለሁ፤ አቶ መለስ ከምዕራብ ከጦሩ ተነጥሎ ብቻውን ነጠላ ልብስ ለብሶ ሴቶቹና ጳጳሳቱ ከአሉበት ይመጣል፥ ሴቶቹም ጳጳሳቱም "መጣ  መጣ ብለው" ሲደናገጡ። እኔ ተበርክኬ ከምጸልይበት ስፍራ ደረሰና ምንም ሳይናገር፤ እኔም ቀና ብዬ ሳላየው ጳጳሳቱንም ሳይናገራቸው፤ ከዚያ ቦታ ጠፋ ቀና ብዬ ሳይ ከስፍራው የለም። እኔም ወደ ጸሎት ተመልሼ ስቃያችን በዛ ተሎ አትፈርድም እስከ መቼ ነው የምትታገሰው፤ አልኩና ምርር ብዬ አልቅሼ በቀኝ እጄ መሬቱን በኃይል ስመታው በተአምር ከደረቀ መሬት ላይ ውሃ ይፈልቅና እጄን አጠለመው። ከዚያ ከአምስት ጣቶቼ ጥፍር ላይ እንደ ዛፍ ስር ያሉ ፈትለክ ፈትለክ ብለው ይወጡና ወደ መሬት ሲተከሉ አየሁ። በድንጋጤ እጄን በሃይል ሳብ አድርጌ ሳወጣው፤ እኒያ ከጣቶቼ ላይ የበቀሉት የዛፍ ስር የሚመስሉት ወዲያውን በቅጽበት ጠፉ። ከወደኩበት ስነሳ ማንም ሰው ከበጣገቤ የለም፤ ልብሴን ለባብሼ ተነስቼ ዙሪያው በሸበተ ድንጋይ የታጠረ የጥንት አትክልት ስፍራ ወደ አለበት ግቢ ሂጄ ቁሜ ተደገፍኩ። ከፊት ከነበሩት ሁለት ሴቶች አንዷ ቀሚ አንደኛዋ ተቀሚ ሁነው እየተሯሯጡ ወደ እኔ ይመጣሉ፤ አንደኛዋ ደርሳ "አስጥለኝ ልትገለኝናት" ትላለች። አንደኛዋም ደርሳ "ንብረቴን ወስዳብኚ አለች ትመልስልኝ እያለች ልትማታ" ትገለገላለች። እኔም ልትማታ የመጣችውን ይዤ ቀስ በይ እያልኩ ሳለሁ ንብረት ወሰደች የተባለችው ሴት ከመሬት ተንጋላ ወድቃ እርቃኗን ሁና እፍረተ ሥጋዋን ገልጣ ታሳያለች። ገንዘብ ተወሰደብኝ የምትለው ለኔ "እያት እያት" ትላለች ዞር ብዬ ሳይ የእሳት እረመጥ የመሰለ ነገር ከሴትዮዋ ገላ ላይ ሳይ፥ በስመ አብ ወወልድ ፤ወመንፈስ ቅዱስ ፤አሐዱ አምላክ፤ አሳቻም ልታስቱኝ ነው የመጣችሁ፤ አልኩና ሁለቱንም ከፊቴ ጥፉ ብዬ አባረርኳቸው። ከዚያ በኋላ እየተሳሳቁ ሁለቱም በአንድ ላይ ሄዱ። እኔም ብቻዬን ከአትክልቱ ስፍራ ድንጋይ ተደግፌ ቀረሁ። ያ ለጦርነት የሄደው ሕዝብም በዚያው እንደ ሄደ ቀረ አልተመለሰም የጦርነት ድምጽም አልተሰማም።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤ጥቅምት፡፳፡ቀን፡፪ሺ፪</u> (20/2002፤ዓ/ም)

ስለ ሀገር የታየ ጊዜና ወራቱ መቅረቡን የሚያሳይ ራዕይ። ከአምባ ጊዮርጊስ ከተማ ተነስቼ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ እልም በአለው የባህር ዛፍ ደን በአለበት አድርጌ ወደ ገጠር እሄዳለሁ፣ እየሄድኩ ሳለ አፍንጫቸው በቂጥኝ የተቆረጠ ፊታቸው በእሳት የተቃጠለ በጣም አስቀያሚ የሆኑ ሁለት ሴቶች ይመጡና ጉንጮቼን አገላብጠው ስመውኝ ሄዱ። እኔም በኋላ በጠና ታመምኩ፣ ታምሜ በሕይወትና በሞት መሃከል ላይ ሳለሁ፣ አንዲት ትልቅ ሴት ትመጣና በሰውነቴ ላይ እንደ ኩፍኝ ቁብ ቁብ ብሎ የነበረውን በሽታ በጣብቂያየ ያለውን ሳይቀር ሙልጭ አድርጋ በንጹህ ውሃ አጠበችኝ። ከዚያ በኋላ የኔን ቆሻሻ ልብስ ወርውራ ጥላ ሌላ አዲስ መጎናጸፊያ አምጥታ አለበሰችኝ። ያን አልብሳ ወደ ትልቅ አዳራሽ ይዛኝ ገባች። ከዚያ አዳራሽ እንደገባነ እሷ ትልቅ ምጣድ ጥዳ እንጀራ ትጋግራለች፤ከአዳራሹ አንድ ትልቅ ቀይ ሰው ከትልቅ ወንበር ከፍ ብሎ ተቀምጦአል፥ በዙሪያው ሰዎች ተሰብስበው ተቀምጠው ትልቁን ሰውየ ያያሉ። በትልቁ ሰውየ ትንሽ ፈቀቅ ብሎ በቀኙ በኩል ዝቅ ያለ ቀይ ወንበር ተዘጋጅቶአል። እኔ ከትልቁ ሰውየ ፊት ለፊት ቀኝና ግራ ተላብሼ ቆምኩ፣ በአዳራሹ ጸጥታ ሰፍኗል የሚናገር የለም። ያን ቀይ ወንበር ለኔ ነው የተዘጋጀ ብዬ ሂጄ ልቀመጥ ስል፣ ድንገት እንደ ጸሐይ የምታበራ ቀይ ሴት መጥታ ቁጭ አለች። እኔም እግሮቼን ወደ ኋላ ሳብ አድርጌ እንደ ተላበስኩ ቆምኩ። ሴትዮዋ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ እንደ ነፋስ ተውለብልባ ባለ አራት እግር አረንጓዴ ትንሽ ወንበር መጥታ ከፊቴ አረፈች። እኔም ከትልቁ ሰውየ በታች ከሰትዮዋ ፊት ለፊት ሁኜ ከዛች

ወንበር ሂጄ ተቀመጥኩ።  በኋላ ያች መጀመሪያ ሰውነቴን ያጠበችኝ ሴት ትልቅ ደመራ ወደ አለበት ሥፍራ ወሰደችኝ። በደመራው ዙሪያ ጳጳሳት ቁመዋል፣ አንድ ቀይ ወጣት ይመጣና መሬቱን ሲመታው ወተት የመሰለ ነጭ እሳት ከጳጳሳቱ ላይ እየዘለለ ወጣባቸው። አሁንም ደግሞ መሬቱን ሲመታው ያነ እሳት ዘሎ አንዱን ቤት ተያያዘው ። እኔ ሂጄ በቅጠል መትቼ በግድ አጠፋሁት። ወጣቱን ልጅ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ ብዬ ስጠይቀው "ታዲያ ምን ላድርጋቸው አለና የአንዱን ጳጳስ መቋሚያ ተቀብሎ መሬቱን ሲመታው" እሳቱ ጠፋና መቋሚያው ለምልሞ እርጥብ ቅጠሎች ይዞ ተነሳ። ከዚያ በኋላ ጳጳሳቱ የተወሰኑ በአንድ ላይ እንሂድ ሲሉ ግማሾቹ በአንድ ላይ አንሄድም በማለት ሳይስማሙ ቀሩና ከሁለት ተከፈሉ።  ግማሾቹ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ግማሾቹ ደግሞ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሄዱ።
የእሳቱ ነገር ካአበቃ በኋላ ያች ቀይ ሴት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይዛኝ ሄደች። *በሰንበትጌ ቅዱስ ሚካኤልና በብራ ታዴዎስ ቅ/ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መሃከል በአለው በአርቃ ተራራ አንድ ትልቅ ቀይ ሰው ዙርያው በወርቅ መስቀል በተለበጠ መንኮራኩር ወይም ፈረንጆች ሆት ኤይር ባሉን (Hot air Balloon) በሚሉት አይነት ሆኖ ከሰማይ ተነስቶ ወደ ምድር ከሩቅ ሲመጣሲ አየነው።  በሰሜን ጎንደር በወገራ አውራጃ በአምባ ጊዮርጊስ ወረዳ በምሥራቅ በኩል ከጎረንኮ ማርያም ገዳም  ለ15 ደቂቃ ያህል እራቅ ብላ የምትገኝ መንገድ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ከአምባ ጊዮርጊስና ከእንቃሽ ማርያም አንስቶ የሁለቱን አውራ ጎዳና አገናኝታ በሰንበትጌ ሚካኤል አድርጋ ወደ ምሥራቅ የምትወስድ ቀጭን መንገድ አለች። ማጭድ እርሙ ባዓሕታ ግራር ከምትባል ሥፍራ ከዚያች ቀጭን መንገድ ላይ አንዲት ጠይም ትልቅ ሴት ሰፊ ቀሚስ ለብሳ በህብረ ቀለም በአሸበረቀ ትልቅ መቀነት ወገቧን ታጥቃ (አስራ)ሁለት እጆቿን ከፍ አድርጋ በሰፊው ወደ ላይ ዘርግታ ፊቷን ወደ ምሥራቅ አዙራ በእኛና በመንኮራኩሩ መሃከል ቁማ አለች። መንኮራኩሩ የአራት ኪሎ ሜትር እርቀት ያህል ወደ እሷ ሊደርስ ሲቀረው "መጣ መጣ እግዚኦ በሉ ሊያቃጥል ነው ሊፈርድ ነው እያለች" ትናገራለች። ጠይሟ ሴት ከፊታችን ሁና ስትናገር አብራኝ የነበረችው ሴት ከኔ ተሰወረች፤ እኔም ብቻየን ቀረሁ።*

ጌታን ልትቀበል ሲመጣ ከሰማይ፤
እጇን ዘርግታለች ኢትዮጵያ ወደ ላይ።
ደስ ይበልሽ በጣም ኢትዮጵያ እማማ፤
በክርስቶስ መንበር ጭሆትሽ ተሰማ።
እጆቿን ዘርግታ ቁማ ስታለቅስ፤
ወደ ታች ወረደ እንባዋን ሊያብስ፤
የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ።
እራሱ ሊጎበኝ የኢትዮጵያን ምድር፤
ወደ መሬት መጣ በወርቅ መንኰራኵር።
በወርቅ መንኰራኵር ወረደ ክርስቶስ፤
በቃሉ መሰረት አንችን ለመፈውስ።
የኃያላን ኃያል የንጉሦች ንጉሥ
ለአንች ተገለጠ እንባሽን ለማበስ፤
የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ።
ከሰማይ ወረደ የፈጠረሽ ጌታ፤
ወጥተሽ ተቀበይው በእልልታ በሆታ፤
እንባሽን አቁመሽ በሳቅ በፈገግታ፤
ኀዘንሽን አቁመሽ ተሞልተሽ በደስታ፤
አንችን ሊያድን ወርዶአል ከረሃብ ከበሽታ፤
የዓለም  መድኃኒት  የሰማዩ  ጌታ!!!
ይህ አካባቢ ብዙ ባህታዊ አሉበት የሚባል ቦታ ነው። እኔ እኳ ከማውቀው ከወንድም ከሴትም ከዛፍ እግር ሆነው ለሀገርም ለሃይማኖትም አነጋግረውን ተሰወሩ የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። እንዲሁም ራዕይ (ህልም) የሚያዩም ብዙ ናቸው። ይህን የአርቃን ተራራ የሚያዋስኑት በሰሜን ምሥራቅ የሰንበትጌ ቅዱስ ሚካኤል፤ በምሥራቅ ከግርጌው የቧክሽ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤ በደቡብ ከእግሩ የብራ ታዴዎስ ቅ/ሥላሴ ገዳም፤ በምዕራብ በኩል ደግሞ የጎረንኮ ማርያም ገዳምና የብራ ኢየሱስ ገዳም፤ እንዲሁም

የጎረንኮ ማርያምንና የብራ ኢየሱስን ገዳም ከእግሩ አድርጎ አቅፎ የያዛቸው የጎረንኮ ተራራ ፊት ለፊት ቁሞ ይታየዋል። ስለዚህ አካባቢ ከሰማሁትና ከአየሁት በመነሳት ትንሽ ልበል። ለምሳሌ ስለ ብራ ታዴዎስ፤ "ብራ ማለት የሀገሩ ስም ሲሆን ታዴዎስ ማለት ቅዱስ፤ጻድቅ የሆኑበትንም በዚህ ቅዱስ ቦታ ቅዳሴ ገብተው ሣለ ጠላት መጥቶ ቤተክርስቲያኑን ያቃጥለዋል አብረዋቸው የሚቀድሱት አባቶች የነደደው እሳት ሲበዛ ጥለዋቸው ወጥተዋል። ጻድቁ ታዴዎስ ግን ጻድቅና ቅዱስ ያሰኛቸው ከጌታዬ ሥጋና ደም ጋር አብሬ እቃጠላለሁ እንጂ አልወጣም በማለት ከእሳቱ ቃጠሎ ውስጥ ቢቀሩም እንኳንስ ሰውነታቸውን ልብሳቸውን እንኳ ነዲዱ እሳት አልነካውም። በዚህም ገድላቸው ቅዱስና ጻድቅ መሆናቸው ከፈጣሪያቸው የአማላጅነት ቃል ኪዳን ተቀብለውበታል። በዚህ ተራራ ቅዱስ ታዴዎስ ገዳም፤ በሚገኝበት በምሥራቅ በኩል ልዩ ልዩ የቅዱሳን ዋሻ ሲሆን በደቡብ በኩል ቅዱስ ያሬድ የጸለየበት ዋሻ ተብሎ ይጠራል።" ሁለተኛም በዚህ "ተራራ ላይም ታኅሣሥ 3 ቀን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዋዜማዋ እለት፤ ታቦተ ሕጉ ከቦታው ወጥቶ እራስ አርቃ ወደ ተባለው ዛፉማ ስፍራ ድንኳን ወደተተከለበት ታቦተ ሕጉ ሲገባ በቦታው ላይ ጠበል ፈልቆ ያድራል። ካህናቱም ሲያገለግሉ ካደሩ በኋላ የሀገሩ ሕዝብ ከጠበሉ ይረጫል ጠበሉም ይጠጣል። ከዚያ በኋላ ታቦተ ሕጉ ካደረበት ተነስቶ ወደ ቀደመ ገዳሙ ሲመለስ ጠበሉ ይደርቃል የጠበሉም መፍለቅ የሚታየው በየዓመቱ ነው ይህ ድርጊት የእመቤታችን የቅድስተ ቅዱሳንን የድንግል ማርያምን ከልጇ ከፈጣሪዋ የተቀበለችውን ቃል ኪዳንና ተአምር የሚያረጋግጥልን ነው። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ በቤተሳይዳ ፈውስ ያደረገበት የነበረውን ጠበል ያስታውሳል ዮሐ ፡ም፤5 ከቁ ፡ 1-9። እና በዚያን እለተ ታኅሣሥ፤ 3ቀንም ፤ ጠበል የሚጠጡና የሚጠመቁ በየዓመቱ እየተሳሉ ስእለቱ ስለሚደርስላቸው በርካታ ገንዘብና እህል ለገዳሙ ይገባል።" አንድ ቄስ ሁለት ዓይኑን ገርሞት አንድ ዓመት ሙሉ በሰው እየተመራ ከቆየ በኋላ ታሣሥ 3 ቀን በዓመት አንድ ጊዜ በምትፈልቀው በባአታ ጸበል ተረጭቶ ድኗል፤ ከዚያን እለት ጀምሮ ያነ ቄስ እያከበረ በዓመት በዓመት ይዘክራት ነበር።

" በዚህ ተራራ በጣገብ ያሉት ዋሻዎች በተለይ ተጋምዶ የሚባለው ዋሻ ሰማይ ጠቅስ ከሆነው ገደል አጠገብ ሲገኝ ዋሻው ከእግሩ በኩል ወደ ላይ ብዙ ጊዜ የማይወጣበት ቢሆንም በዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት ተነስቶ በነበረው መከራ ሕዝቡ ወደ ተራራው ጫፍ ሲሰደድ በዚሁ በኩል እንደ ወጣ አበው ይተርካሉ። በዚህ በኩል የሚገኙት የገደል ዋሻዎች ከታላላቅ አዳራሾች የሚበልጡ፤ ሲሆኑ የሚገኙትም ዙሪያውን ነው። በነዚህ ዋሻዎች ውስጥ ቅዱሳኑ በየጊዜው ድንቅ ተአምራትና ፈውስ የሚፈወሰው። በጸሎት ለበረታና አጽንኦ በዓት ላደረገ መቋሚያውና መቁጠሪያ እንደያዙ ቅዱሳኑ በጸሎት ላይ ሆነው ይገለጹለታል። ፈቃዳቸው ሲሆንም ያነጋግሩታል። እንዲሁም ዋሻዎቹ ከታላቁ ገዳም ብራ ታዴዎስ ስለሚገኙ ቅዱሳኑ ከዋሻዎቹ ወደ ገዳሙ ውስጥ ለውስጥ የሚመላለሱበት መንገድ መኖሩ ታውቋል። ከቅዱሳኑም የሚወጡትና የሚገቡት ቤተክርስቲያኑ ከላይ እያለ በሥር በኩል በምሥራቅ ገብተው በምዕራብ በኩል ነው። ከዚህም ሌላ በየጊዜው ያለ ሰዓት ሌሊት ካህናቱ ለአገልግሎት ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ በአካባቢውም ሆነ በገዳሙ ውስጥ ማንም ሰው ሳይኖር በደመቀ ሁኔታ በድምጸ መላእክት ሰዓታት ተቁሞ ስብሐተ ፍቁር እየደረሰ፤ ጠቅላላ አገልግሎት እየተፈጸመ ይሰማቸዋል። ካህናቱም በድንጋጤ ያዩትንና የሰሙትን ጧት ለሕዝብ ይናገራሉ። ይህ አቢይና ድንቅ ታሪክ ከሚታይባቸው ዋሻዎች አንዱ ኢትዮጵያዊው ጻድቅና ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ የጸለየበት ነው።" እስካሁንም ወንዶችም ሴቶችም ትንቢት ሲናገሩና በራዕይ ሲገለጽላቸው ይታያል።

***<u>እራሴ ከሰማሁትና ካየሁት እንዲሁም ፤ ንቡረ ዕድ ወልደ ማርቆስ ሰለ ገዳሙ አጭር ታሪክ ከጻፉት መጽሐፍ ቀንጨብ አድርጌ የተጠቀምኩት ነው።</u>***

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>ጥቅምት:<u>፳፱</u>፡ቀን፤<u>፪ሺ፪</u> 29/2002፤ዓ/ም)

በእለተ ሰንበትና በበዓለ እግዚአብሔር ቀን ስለ ሀገር የታየ። በትሬን ይዤ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ እላካለሁ፣ ከተባለው ቦታ ስደርስ ከትልቅ ተራራ ግርጌ አንድ ትልቅ ዛፍ አለ፣ ከዚያ ዛፍ ስር አንዲት ባለ ዛር ሴት በትልቅ ገንዳ ላይ ብዙ ስኒ ዘርግታ በተለያየ ማጨሻ ገል ደክራ እጣን እያጤሰች ተቀምጣለች፣ በዙሪያዋ ብዙ ነጫጭ በጎች እሷን አጅበው ተቀምጠዋል። ከዚያ ደርሼ ያን የተዘረጋ ስኒና የእጣን ማጨሻዋን ደፍቼ ሰባበርኩባት። ስሰብርባት "እኔኮ ባአለ ዛር ነኝ" ትለኛለች። አዎ አውቃለሁ ባአለዛር ነሽ ብዬ መለስኩላት። ከእሷ ጋር እየተነጋገርኩ ሳለ እንስትና ተባት የሆኑ ጦበት

ጦበት በጎች ተነስተው ሊይዙኝ ሲሉ በስመ አብ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ ብዬ እሩጬ አመለጥኩ። አሁንም ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መንገዴን ስቀጥል ከተራራው ትንሽ ዝቅ ብሎ ዳርና ዳሩ በዛፍ የተሸፈነ በጋ ተክረምት የሚፈስ ትልቅ ወንዝ አለ። ከዚያ ከመድረሴ በፊት ሁሉም መሬት ደርቆና ተቃጥሎ ውድማ የምታህል ድንግል መሬት ሲጦ ተሰጥጦ እሳርና ሱፍ በቅሎባት አገኘሁ። ከእሷ ዳር በትሬን ይዤ ቁጭ ብዬ ሳለሁ ፤በትሬ ድንገት ከኔ ተሰወረች ጠፋችብኝ ብዬ፣ ወዲያና ወዲህ እየዞርኩ ስፈልግ ሳለ፣ ***<u>ዘንግ የነበረችው ከዘራ ፤አንድ መልክ የነበረችው ዝንጉርጉር ሁና፣ በትረ ያእቆብ መሰላ አገኘዋት።</u>*** እሷን ይዤ ስንሳ አሁንም ድንገት ከደረቀውና ከተቃጠለው መሬት ላይ ዙሪያዋ እንደ ውድማ ተከትራ ለምለም እሳር በቅሎባት ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ከውስጧ ተቀምጠዋል፣ ብዙ ከብቶች ከደረቀው መሬት ላይ ቁመው ያችን ለምለም ቦታ ዙሪያዋን ከበዋታል። ሁኔታው አስገርሞኝ ያን ላይ ተነስቼ ወደዚያ ስሄድ ያ በአንድ ላይ ታጉሮ ቁሞ የነበረ ከብት እረኛውን ጠቅጥቆ አሻፈረኝ ብሎ እሳርና ውሃ ፍለጋ ወደ ወንዙ ይሄዳል፣ ጊደርና ወይፋፍኑ አጥቅቶ ሲሄድ ክበዶቹና የሚያጠቡት ሰውነታቸው ደክሞ ቆዳቸው ከአጥንታቸው ጋር ተጣብቆ መሄድ ተስኖአቸው ይቀራሉ። እረኛው ተነስቶ እኒያን የደከሙትን ከልክሎ አቁሞ ሊያስቀር ሲል እኔ ደርሼ ተዋቸው የአንድ አገር ስም ጠርቼ የሌላው አገር ከብት የተሰጠው ቦታ አልበቃው ብሎት ሌላ ሊጨምር ይባክናል፣ እናንተ ግን ከዚህ ከአንድ ላይ አጉራችሁ በረሃብ ልትገሏቸው ነው፣ ተዋቸው ይሂዱ ስል። አንድ ጠይም ጎበዝ ብድግ አድርጎ “አይ እድሜ ለመላው አማራ ከብት እንጂ እኛማ ከዚህ አፍነን ልንገላቸው ነበር” ይላል። ምስጢሩ ሌላ ነው የሰውየውን ስም አልገልጠውም።

ያ እረኛውን አምልጦ የሄደው ከብት ከወንዙ ሲደርስ ውሃው ደርቆ የሚጠጣው አጥቶ ከታች ወደላይ ውሃና እሳር ፍለጋ እየባከነ ይሄዳል። ከዚያች ለምለም እሳር ቦታ ላይ ከቆሙት ሰዎች አንድ ሽማግሌ ሰው ይገኛል፣ ያን ሽማግሌ ሰው በሉ ደግፋችሁ አንሱትና ምርኩዝ ፈልጉለት እላቸዋለሁ፣ አብረው ላሉት ሰዎች። ይህን ብዬ ስናገር ያች ለምለም ቦታ በምሥራቅ በኩል ሰባትና ስምት የሚሆኑ ዋሻዎች አፋቸውን ከፍተው ይታያሉ ፤በሉ ሁሉም ሰው እጁን እያስገባ ለሽማግሌው ምርኩዝ የሚሆን በትር ይፈልግ ብዬ እኔም አብሬ ልፈልግ ተዘጋጀሁ። ለየአንዳንዳችን አንዳንድ ዋሻ ደረሰን ሁሉም ሰው ወደ ዋሻው እጁን አስገባ ፤ፈልጎ አጣ። እኔ እጄን ሳስገባ ቅርንጫፎቿ ለምለም ቅጠል የአሷት ወይራ በትር አገኘሁ፣ ያችን አውጥቼ በሉ እንኩ ቀፍቅፋችሁ ምርኩዝ አድርጉለት ብዬ አብረው ለአሉት ሰዎች ሰጠዋቸው። ከዚያ በኋላ ወደ ዚያ ጠይም ጎበዝ እድሜ ለመላው አማራ ከብት ወደ አለው ሰው ሄድኩ። ከዚያ ደርሼ በአንድ እረኛ ሲጠበቅ የነበረ የወንድማማቾች ከብት ለእየራሱ ተበታትኖ እረኛ ይፈልጋል። ለዚያ ጠይም ጎበዝ ለመሆኑ እናንተ ሥራ ነው የምትሰሩት ወይንስ ከብት ነው የምትጠብቁት ብዬ ስጠይቀው “እኛ ምን እናድርግ ዋና ዋና ዎቹም ጥለውን ተነስተው ሄዱ” ብሎ ይመልስልኛል። እኔም በነገሩ አዝኜ ተነስቼ ከአንድ ተራራ ጫፍ ሂጄ ተቀመጥኩ። ቁጭ ብዬ በአራቱ ማእዘን ስመለከት ያ ጥንት የማውቀው ለምለም አገር ደርቆና ተቃጥሎ የዛፎቹ ቅርንጫፎቻቸው ደርቀው ስሮቻቸው አፈር ክዶአቸው የሚለብሱት አጥተው እርስ በርስ እንደ አረግ ተጠላልፈው አጥንት መስለው ገጠው ይታያሉ። መሬቱም አፈሩ ተሟጦ አልቆ አለት መስሎ ገጦ ይታያል ይቅርና እህልና እሳር ሊያበቅል ቀርቶ ችፍርግ የሚያበቅል አይመስልም። እንግዲህ የዚህን ትርጉም እኔ በራሴ ተንትኜና ገልጬ ከምጽፈው ይልቅ አንባቢው ክፍል ተመራምሮ ይድረስበት ብዬ ትቸዋለሁ። ሁሉም ሰው ክፉ ወንጀለኛ ኃጢአተኛ ነው። እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱ ምህረት ያውርድልን ሁሉም በእርሱ እጅ የተያዘ ነውና የሚሳነው ነገር የለም። እንግዲህ ከብት ምን መሆኑን እረኛ ምን መሆኑን ትርጉሙን የምታውቁትም ታውቁታላችሁ የማታውቁትም ተመራምራችሁ ድረሱበት።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>መጋቢት፡፫፡ቀን፡፪ሺ፪ (3/2002፤ዓ/ም)
## <u>ዙሪያ ገቡ የተመሸገ የታጠረና የሚያስፈራ ግቢ ሲፈርስ የሚያሳይ ራዕይ።</u>

አንድ አሥቂኝ የሞቱትንና በሕይወት ያሉትን የዘፋኞቹንና የአሥቀኞችን ስም እየጠራ በአጠቃላይ የሞያ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ላይ የደረሰውን ግፍና በደል እየዘረዘረ ይናገራል። በሰው እጅ የሞቱትንና የተደበደቡትን እንዲሁም እስረኛ ሁነው የማይንቀሳቀሱትን ሰርተው እንዳይበሉ ከስራ የታገዱትን

መሹለኪያ ቀዳዳ አጥተው የሚሰቃዩትን የሞያ ባልደረቦቹን ስም እየጠራ ተንበርክኮ ጩሆቱንና ጸሎቱን ለእግዚአብሔር ያሰማል። እራሱ ከዚህ ሁሉ መከራ እንዴት ሾልኮ እንዳመለጠ ሲናገር በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት ከአገሩ ወደ ሌላ አገር እንደወጣ ያስረዳል። ይህን ብሎ ሲናገር ቅዱስ ጊዮርጊስ በስዕል መልክ ተመስሎ ከጎኑ ቁሞ ይታያል። አሁንም በመቀጠል ተንበርክኮ በጸሎት እግዚአብሔርን ሲማጸን ሳለ። እኔ በትሬን ይገፔ ከእሩቅ አገር ተነስቼ ወደ አቶ መለስ ዜናዊ እንድሄድ ታዘዝኩ። ከዚያ ስደርስ ቦታው ጭር ብሏል የአቶ መለስም ግቢያቸው ትልቅ የነበረው አንሶ ከትልቅ አዳራሽ ውስጥ የነበሩት ለቀው ከአንድ ግለሰብ በጣም ትንሽ ከሆነች ቤት መልሶም እጅግ በጣም ውድ በሆነ ክራይ ተከራይተው ተቀምጠዋል። የግለሰቡ ግቢ ቁመቱ በጣም እረጅም የነበረው ያንሳል፣ በብረትና በስሚንቶ የተገነባው ግቢ ወደ ጥሬ ካብ ይቀየራል። መጀመሪያ ካቡን ዘልዬ ስገባ እንደ አንበሳ የሚያስፈሩ ጥቋቁር ውሾች የቤቱን ዙሪያ ከበው ቁመው ይጠብቃሉ። እኔን ሲያዩ መናከስ ቀርቶ ድምጻቸውን አላሰሙም፣ አንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ጸጥ አሉ። እኔም በትሬን ይገፔ ከበራፉ ቆምኩ፣ያች ትንሽ ቤት የአቶ መለስ ዜናዊን ባለቤትና ልጆች ብቻ ይዛ ጥርቅም ብላ ተዘግታለች። ከዚያው ቁሜ ሳዳምጥ በፍርሃትና በጭንቀት ተውጠው ያለቅሳሉ፣ አቶ መለስን ለማግኘት እረጅም ሰዓት በትሬን ተደግፌ ከግቢው ውስጥ ቁሜ ቆየሁ። እሳቸው ግን ማለትም አቶ መለስ ከቦታው የሉም ፣ቤቱም አልተከፈተም ፣ተመልሼ ልወጣ ስል እንዳለ ግቢው ፈረሰ። እኔም በፊት ዘልዬ የገባሁት በኋላ ግን ስመለስ በፈረሰው በራፍ አድርጌ ወጣሁ። በአካባቢው ውር የሚል ሰው የለም አቶ መለስም እንደ ተደበቁ ቀሩ በዚህው አበቃ አቆመ።

## <u>የተስፋ ራዕይ፤</u>መጋቢት፡ ፳ቀን፡፪ሺ፪ (20/2002፤ዓ.ም)

እኔ ካልሄድኩ አንድነት አይገኝም አልኩና ከሩቅ አገር ተነስቼ ወደ ኢትዮጵያ ሄድኩኝ። መጀመሪያ መጠጥና ምግብ እየሸጠች ከምትተዳደር ከአንዲት ድኀ ሴት ቤት ሂጄ ገባሁ፣ ስገባ ብዙ የናይጀሪያ ጥቋቁር ሰዎች ተሰብስበው አገኘሁ። በኋላ አንድ ሽጉጥ የታጠቀ ጥቁር ሰው ዘሎ ገባ፣ ወዲያው ሽጉጥ አውጥቶ በዓይን ጥቅሻ ሁሉም ሰው ከመሬት እንዲተኛ አዘዘ። ሴቷ ቁማ ታለቅሳለች የሰዎችንና የሴቲቱን ገንዘብ ወሰደባቸው። የነዚያን ገንዘብ ከዘረፈ በኋላ ወጥቶ ሄደ፣ እነዚያም ወጥተው እየተሳሳቁ ተከትለውት አብረው ሄዱ። እኔም እነሱን እያየሁ አሁን ተመሳጥረው ነው ይችን ድኀ የዘረፏት፣ አይ መንግሥት የሌለበት አገር እያልኩ ወጥቼ ሄድኩኝ። ከዚያ መሃል አንዲት ትልቅ ሴት በችግር የተሰቃየች ፣በኀዘን የተጎዳች ፤ በረሃብ የማቀቀች፤ ህጻን ልጅ እንደ ጠፋት ሁሉ በሰው መሃል ዓይኗን ወዲያና ወዲህ ይንከራተታል። እኔን አይታ በሰው መሃል አድርጋ ወደ እኔ መጣች፤ ዞር ብዬ አይቼ አንች ሴት ምንሁነሽ ነው የምታለቅሽው ስላት። “ምግቤ ተዘግታብኝ የሚከፍትልኝ አጥቼ ፤ ቀለቤ ተዘግታብኝ የሚያወጣልኝ አጥቼ” ትላለች። ታዲያ እኔ ሚዛን መዛኝ ነኘ እንጂ ቁልፍ አሊያስኩ አልኳትና፤በይ ቁልፍ ተቀብዬ አወጣልሻለሁ ብዬ ወደ መሃል ከተማ ሄድኩኝ። ሴትዮዋም ትከተለኛለች ሁለት እስላሞች ከከተማው ወጣ ብለው በራፍ ዘግተው በመስኮት ብርሃን እያዩ ጌጣጌጥ ይሰራሉ፣ የሚሰሩት ከግድግዳ ላይ የሚቀመጥ የፎቶ ማስቀመጫ የመስታውት ፍሬም ነው። በዚህ አድርጌ እንድወጣ ትፈቅዱልኛላችሁ ስላቸው “እህ ደሞ ለአንተ እብኝ ይባላል” ሲሉ። ታዲያ ይህን ጌጣጌጣችሁን ካላነሳችሁ እንዴት አድርጌ እሄድ አለሁ ይሰበራል ስላቸው። በአንተ አይሰበርም ቁምበትና ሂድ ይላሉ። እንዳሉት ከዚያ መስታውት ፍሬም ላይ ስቆምበት ምንም ሳይሰበር ቀረ። እኔም በመስኮቱ ወጥቼ ሄድኩኝ። ከከተማው ስገባ ክርስቲያኑም፤ እስላሙም በየ ቤቱ፤ በየ ምግብ ቤቱ፤ በየ ሱቁ ፤ አዛውንቱም ፤ ወጣቱም እየወጣ ይገናኘኛል። “ለረጅም ጊዜ ጠፍተህ አሁን መጣህልን” እያሉ ይደሰታሉ። ከዚያ መንገዴን ስቀጥል በፊት ኃብታም የነበረ በአሁኑ ሰዓት የደህየ ወፍጮ ቤት የነበረው በወፍጮና በንግድ የሚተዳደር አንድ ነጋዴ ትልቅ ሰው ጓዝ ተሸክሞ ሲመጣ አግኝቼ ቁልፉን ስጠኝ ስለው። በማተብ የታሰረች አንዲት ቁልፍ አውጥቶ ይሰጠኝና “ይመስልልኝ ይመስልልኝ በአንተ ይመስልልኝ በአንተ ለአግኝ” ብሎ እጆቹን ዘርግቶ ወደ ላይ ወደ ታች ጎንበስ ቀና እያለ እኔን ይማጸናል። እኔም ለሰውየው መልሼ ወፍጮ ቤቱን ከፍቼ ለሰትዮዋ ቀለቧን ለአወጣላት ነው የምሄደው አልኩና፣ አይዞህ አንተንም አረሳህም ብዬ ከእሱ ተነጥዬ ስሄድ፣ወዲያውን ብርቱካን ሚደቅሳ ጥቁር ልብስ ለብሳ በጣም ተጎድታ ፊቷን ተሸፍና ወድቃ አየኋት።

ጎኔን በጦር እንደ ተወጋ ሰቅዞ ያዘኝ ፤ከራሴ አንስቶ እስከ እግር ጣቴ መላ አካላቴን ወረረኝ ፤በኀዘን ተዋጥኩኝ። ሁሉም ሰው ብርቱካን መሪያችን እያለ በነቂስ ሲወጣ አየሁት፤ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ሳይቀሩ መሪያችን፤ መሪያችን ይላሉ። ኧረ መቼ ይሆን ከአንች ትልቅ ሰው የሚወጣብሽ ለአንች የሚያስቡትን እንደ ደሮ ጫጩት እያነቅሽ ትገይአለሽ እያልኩ ፤እንደ ሰው ኢትዮጵያን እወቅሳታለሁ። እጆቼን ወደ ላይ ዘርግቼ ሰማዩን እያየሁ እስከ መቼ ነው የምንሰቃየው ተሎ አትፈርድም ብዬ ከመሬት ወድቄ እየጸለይኩ አለቅሳለሁ። እንዲሁ በጥር ወር ፤ ፳፻፪ (2002፤ዓ.ም ) በጣም ከፍቷት ተጎሳቁላ ከመሬት ላይ ወድቃ "ኧረ እባክህ ጸልይልኝ ተሰቃየሁ" እያለች ስትለምን በራዕይ አይቻት ነበር። እኔ ግን በዚያን ጊዜ ምንም ምልስ አልሰጠኋትም (አላዘንኩላትም) አልጸለይኩላትም ነበር፤ አሁን ግን በጣም ነው የተሰማኝ። ወዲያውኑ አቶ መለስ ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን አፍጥጦ ሁለት ቀንድ አብቅሎ ከፊቴ መጥቶ ቆመ። ብድግ ብዬ አንተ ሰይጣን በአንተ ተሰቃየን አልኩና ጉሮሮውን አንቄ ያዝኩት፤እንደ ኳስ ቀለለኝ ፊቱን ሸፍኜ አንገቱን ፈጥርቄ ይዤ ከግድግዳ ጋር አጋጨሁት፤ ደም ግን አይወጣውም ፤ ከመሬት ጥዬ ስደበድበው ከትልቅ አዳራሽ ወጥታ አንዲት ትልቅ ሴት ከደረጃው ቁማ ስታየኝ ፣በኔ እጅ ደም እንዳይፈስ ብላነው ብዬ መደብደቤን አቆምኩ። እሱም ተነስቶ በማሽላ አገዳ ውስጥ አድርጎ ሄደ። በአገዳው ውስጥ ገብቶ ተደብቆ የሆነ ነገር ሲወስድ አየሁት። ወዲያውኑ አበደ ራሱን ስቶ ቆየና ተቀይሮ እባብ ሁኖ እኔን ጠልፎ ሊጥለኝ ውስጥ ለውስጥ መጣ፣ ቁሜ ጠበቅሁት። መጥቶ ሊይዘኝ ሲል፣ አንገቱን አንቄ ይዤ ራሱን ፈጥፍጬ ጣልኩት፤ አሁንም ሳይሞት ተነስቶ ሄደ።

አንድ ቀይ ሰው ከፊቴ መጥቶ ይቆማል፣ በል አባቴ አንተ መጽሐፉን አሳትመው እኔ ሂጄ መግባት አለብኝ ስለው ፣"የታል መጽሐፉ" ሲለኝ። ከተስፋዬ ቤት አለልህ ብዬ የተቀበልኳትን ቁልፍ እንደያዝኩ ይህን ሰው ከአልገደልኩት አይተወኝም እያልኩ ሳስብ፣ እሱም እየተደበቀ ይከታተለኝ ጀመር። እኔም ራሴ ከአልገባሁ ሰላም አይገኝም ተአምር አይፈጠርም ብዬ፣ ጥንት የተመሰረተች አሁን የፈረሰች ህንጻ ከአለባት አገር ሄድኩኝ። ከዚያ ደርሼ ሳያት ሰዎች ሊሰሩ ተሰማርተዋል፣ አንድ ቀለም የሚቀባ ኢራቃዊ ሰው እኔን ሲያይ ለብሶ ቀለም የሚቀባበትን ነጭ ኮብሌት ቱታ አውልቆ ሊሄድ ሲል፣ እኔን ስታይ ነው የምትሄደው? ቆይ አልኩና አስቀረሁት። ወዲያው አቶ መለስ ጭፍሮቹን አስከትሎ እኔን ሊይዝ ሲመጣ በሩቅ አየሁት። ለሰዎቹ ግን አይታያቸውም ነበር። አሁን ተአምር ታያላችሁ እያልኩ አብረውኝ ላሉት ሰዎች ስናገር፣ የመለስ አባት ይመጡና ከፊታችን ቁመው ህንጻውን ተደግፈው "መጣባችሁ ተደበቁ ተደበቁ እያሉ" ለኔና ቀለም ለሚቀባው ኢራቃዊ ይናገራሉ። እኔም አንሄድም ተአምር ይፈጠራል ስላቸው አብረዋቸው ከአሉት ሰዎች ጋር ሁነው በኃይል ገፋፍተው ሁለታችን ከህንጻው ውስጥ ያስገቡናል። ኢራቃዊው ወዲያው በህንጻው ዘሎ ወጥቶ ሄደ። እኔ ህንጻውን ይዤ ተንጠላጥዬ እወጣለሁ ስል ማንም ሰው ሳይመታኝ ከጭኔ ላይ በሰይፍ ተመታሁ፤ ስመታ ተመልሼ ከህንጻው ውስጥ ከአንዲት ትንሽ ክፍል ሂጄ ገባሁ። እኔም እንደ እስረኛ አንገቴን ከጉልበቴ ላይ አስደግፌ ቁጭ አልኩ። መለስም እስከ ጭፍሮቹ ከህንጻው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሳይገባ በውጭ ከሩቅ እንደ ቆመ ቀረ። እኔንም አላገኘኝም ያልተመታው እግሬ ሳይቀር በእውነት ደንዝዞ ሲያመኝ ዋለ። የብርቱካን ሁኔታም ልቤን በኀዘን ነክቶት ቀረ። ያች ህንጻም አሸዋማ ከሆነ ቦታና ለም ከሆነ መሬት የተመሰረተች ከከተማ ወጣ ብላ የታነጸችው አሁን ፈርሳ ባዶ ሁና የምትታየው ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም ነች። ራዕዩ በገሃድ ወዲያው የታየ ነው። ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ እራዩ እንደታየ ብዙም ከእስር ቤት ሳትቆይ ተፈትታለች። ኢራቃዊውም በፊት እስላም የነበረ ወደ ክርስቲያን የተቀየረ፣ ለቤተ ክርስቲያ ብዙ የሠራና አስተዋጽዎ ያደረገ ነበር። ሰይጣን በነመለስ ተመስሎ ልክ ከቅድስቲቱ ቦታ ከኢየሩሳሌም ህንጻ ግቢ አዘልሎ አውጥቶ እንዳጠፋው ሁሉ ሕልሙን ባየሁ ከስድስት ወር በኋላ ከክርስትና እምነቱ ወጥቶ ጠፋ፣ ተፈልጎም አልተገኘ። እኔንም ሰይጣን በብዙ ነገር ሲፈታተነኝ ከእምነቴ ተሰነካክየ እንዳልወድቅ ፣እግዚአብሔር ከጎኔ ሆኖ ሲጠብቀኝ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጽር ግቢ ዘልየ እንዳልወጣ ብሎ በራሱ ሰይፍ መትቶ አስቀመጠኝ። ይህ ሰው በግብጽ ቤተ-ክርስቲያን ሲያገለግል የነበረና ለቤተ-ክርስቲያኒቱ ብዙ አስተዋጽዎ ያደረገ ነበር። ክርስትና አባቱም የቤተ-ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ የሆኑት መነኩሴ ነበሩ።

<u>(ይህ ምስጢራዊ ራዕይ ነው፤ ማንም ሰው በቀላሉ ትርጉሙን ሊያውቀው አይችልም፤ እግዚአብሔር የገለጸላቸው ካልሆነ በስተቀር)።</u>

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>ግንቦት፡፳፩፡ቀን፡፪ሺ፪ 21/2002፤ዓ/ም)

አንድ አባ ገ/ጻዲቅ የሚባል ባህታዊ  አባ ገ/ሚካኤል ፤ ለሚባል በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ በአምባ ጊዮርጊስ ወረዳ በስተ ምሥራቅ በኩል ለምትገኝ ለጎረንኮ ማርያም ደብር አስተዳዳሪ ለሆነ መነኩሴ የነገረው ራዕይ እንዲህ የሚል ነበር።  ያ ባህታዊ ለዚያ መነኩሴ ይጠራና "ጾም ጹም ይህ መንግሥት እስኪ ወድቅ ድረስ" ይለዋል። ያ መነኩሴም ነጭ ልብስ ለብሶ ከመሬት ላይ ወድቆ እግሮቹን ዘርግቶ ተኛ። እኔ ለዚያ ባህታዊ መልሽ ይህማ ሁልጊዜ እንደ ጾመ አይደል የሚኖር ብዬ መለስኩለት ይህን ስለው፤ ባህታዊው ከፊቴ ተሰወረ። የዚህን መነኩሴ ታሪክ ከማውቀው ጥቂቱን ልንገራችሁ ይህ መነኩሴ  እናቱ ግብር አድቅቃ ያሳደገችውና የአስተማረችው ከፊደል ቆጠራ ጀምሮ እስከ ቅስና ማእረግ ያገኘው አሁን በአላፊነት ተረክቦ በሚያስተዳድራት ገዳም ነው። አባቱ ቄስ ተሰማ ይባላሉ ፣እሱ እንደተወለደ ይሞታሉ። እናቱ የእሱን ትልቅ ወንድም ከአጎቶቹ ጋር ትተው የአባቱን ኃብት አውርሰው መንኩሰው ቆብ ጭነው ህጻን ልጃቸውን ይዘው ገዳም ገቡ። ልጁም በአደገባት ገዳም ተምሮ የዲቁና ማእረግ ተቀብሎ ሲያገለግል፣ ከእለታት አንድ ቀን አባ ወንድማገኝ የሚባሉ ባህታዊ በገዳሟ ውስጥ የሚኖሩ ያገኙትና "ልጄ ሲሆን ድንግል ሁነህ ቤተ-ክርስቲያንን አገልግል ሚስት አታግባ አገባለሁ ካልክም በዚህ ዓመተ ምህረት እንጂ በዚህ አመተ ምህረት አታግባ" ይሉታል።  ቀኑን ወሩንና አመተ ምህረቱን ገልጬ ያልጻፍኩት፣ እኔ በዚያን ጊዜ ልጅ ስለነበርኩ ለአውቀው አልቻልኩም።
እሱ ግን የተነገረውን እረሳውና ዲያቆን የሆኑት ጓደኞቹ ሚስት አጭተው ሲዳሩ እሱም እንደነሱ ሴት አግብቶ በትዳር ዓለም ላይ ለመኖር ፈለገና እናቱን ሚስት ፈልገሽ አጋቢኝ አላቸው። እናቱም በሮ ይጠፋብኛል በማለት ፈርተው አጭተው አጋቡት። ተድሮ በጫጉላ ላይ እንዳሉ ሙሽራይቱ ሳትታመም በድንገት ከዳሱ ውስጥ እንዳለች ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች።  በኋላ ዲያቆኑ እኒያ ባህታዊ  የነገሩትን ነገር በቀብር ስነ ስርአት ላይ ሕዝቡ እንዳለ ተናገረ ይህ ብቻም አይደል ብዙ ነገር ነግረውታል። ስለ ሃይማኖት መርከስና ፤ ስለ ሀገር መጥፋት በሰው ልጅ እልቂት እንደሚደርስ ሌላም ስለረሃብና ጦርነት እንደሚሆን ነግረውት ነበር። ከዚያ በኋላ ለምንኩስና መአረግ በቅቶ ዛሬ የገዳሟ አላፊና አገልጋይ ሆኖ ተቀምጧል።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>ሰኔ፡፲፫፡ቀን፡፪ሺ፪ (13/2002፤ዓ/ም)

መርቆሬዎስ የሚባል ባህታዊ የነገረኝ ራዕይ እንዲህ የሚል ነበር። መጀመሪያ እኔ በአንድ እጄ ጭራሮ እንጨት በአንድ እጄ ግሬራ ይዤ ወተት ለአመጣ ከሰዎች ጋር ሁኜ ወደ በረሃ እሄዳለሁ። በኋላየ አንድ ወጣት ልጅ ይመጣና አልፎኝ ከሄደ በኋላ ተመልሶ ወደ ኋላ ይመለስና ይቀራል፣ ትንሽ ቆይቶ ይጠራኛል። እኔም ዞር ብዬ ሳየው የድሮ የሃይማኖት አስተማሪየ መስሎ ታየኝና የንታ አረጋዊ ብዬ ተመልሼ ሂጄ ጉንብስ አልኩና ጉልበቱን ልስመው ስል "እንዳትቀርበኝ" አለና ወደ ኋላ ሸሸ። "ተከተለኝ" ብሎ ከመንገዱ አውጥቶ ወደ  ሌላ ስፍራ ወሰደኝ።  ቆም አለና እንደመቃተት ብሎ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘረጋ። ወጣት የነበረው በአንድ ጊዜ ትልቅ ሰው ሆነ ልብሱም አሮጌና የአደፈ የነበረው ነጭ ሆኖ ወደ አዲስ ተቀየረና ባዘቶ መሰለ። የኢትዮጵያን ስም እየጠራ በግእዝና በአረበኛ ይጸልያል። ትንሽ ቆየና "ኢትዮጵያ በራላት፣ ኢትዮጵያ በራላት፣ ለኢትዮጵያ አበራችላት" እያለ ደጋግሞ ይናገራል። ይህን ሲል እመቤታችን ለኢትዮጵያ መብራት አበራችላት ማለቱ ነው። ቦታው  ከጎረንኮ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን በእስተ ምዕራብ በኩል ከገዳሙ ትንሽ የአምስት ደቂቃ መንገድ ያህል እራቅ  ብሎ ይገኛል። የእርሻ ቦታ ነው የድንጋይ ካብ የበዛበት ባድማ ነው። እሱ እንዲህ እያለ ሲጸልይ፥ እኔ ከእግሩ ላይ ተደፍቼ በሁለት እጄ እግሮቹን ጠምጥሜ ይዤ በመንፈስ ተመስጬ  እሱ የሚለውን፣ እኔም ኢትዮጵያ በራላት ኢትዮጵያ በራላት እያልኩ እጮሃለሁ፤ ሰው የሚባል በስፍራውና በአካባቢው የለም እኔና ባህታዊው ብቻ ነን። ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ ከእኔ ተለይቶ በድንጋይና በድንጋይ መሃል ከአለች ጎጆ ዋሻ ከምትመስል ሂዶ ገባ። እኔም ተከትየው ልገባ ስል፣ በራፉ በእንጨት መዝጊያ ተዘጋ ልከፍት ብል አልከፈት አለኝ። ውስጡ ጨለማ ነው የሌላ ሰው ድምጽ አብሮ ይሰማል። እኔ በድንጋጤ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራሁ በትሬን ይዤ ወደ በረሃ እሮጥኩ። ከዚያች ዋሻ ውስጥ ሁለት ወጣቶች ይወጡና "አባ ተመለስ ይሉሃል" እያሉ ይጠሩኛል። አንደኛው የያዝኩትን በትርና ድንጋይ ሳይፈራ ደርሶ እጀን ሊይዘኝ ሲል፣ እንደ እብድ  አድርጎኝ የነበረው አይምሮየ ተመለሰና ጤነኛ ሰው ሆንኩኝ።

ሁለቱ ወጣቶች መልሰው ወደ ባህታዊው ሲወስዱኝ በአንድ ጊዜ ቦታው ተቀየረና ሰው ያልነበረበት በሕዝብ ሞላ ከመሃሉም አንድ ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን አለ። ያ ሁሉ ሕዝብ ከቤተ-ክርስቲያኑ በጣገብ ሆኖ በእንቢልታ፤በመሰንቆ ፤ በክራር ፤ በበገና ፤ በዋሽንትና በተለያየ፣ የሙዚቃ መሳሪያ ይጫወታል። ከዚያ ውስጥ ህጻናቶችን አቅፈው የሚያጫዉቱም አሉ። እኔ ሂጄ ከሕዝቡ እንደ ተቀላቀልኩ እኒያ ሁለት ወጣቶች ወደ ባህታዊው ሊወስዱኝ የነበሩት ተሰወሩና፤ እኔን ሌላ አንድ ቀይ ወጣት ስሙ ቅዱስ የሚባልና አንዲት ወጣት ሴት ሁነው ተቀበሉኝ። ወጣቱ ወንድ “መጽሐፉን እንዴት አደረከው” ብሎ ይጠይቀኛል። እኔም ግራ በመጋባት መጽሐፍ መጻፌን የት ያውቃል ማንስ ነገረው እያልኩ በመገረም ጸጥ ብዬ ቆየሁ። ቆይቼ ስመልስለት መጽሐፉ ተቃርቦአል ትንሽ ነው የቀረው፤ እሱም ሊዘገይብኝ የቻለው በሁለት ነገር ስለተ ጻፈ አልገናኝ ብሎ ለዚያ ማስተካከያ መሳሪያ እየተፈለገ ነው፣ ብዬ መለስኩለት። እሱም “ቢያልቅ ጥሩ ነበር” እያለ ከሕዝቡ ነጥለው ወደ ተራራ ይዘውኝ ሄዱ። ከዚያ በመቀጠል አሁንም ስለ መጽሐፉ ይጠይቀኛል “እንዴት አድርገህ ነው የጻፍከው” ይለኛል። እኔም በሁለት ጉዳይ ነው የጻፍኩት ግማሹን በሀገር ግማሹን በሃይማኖት እለዋለሁ። እሱም “መልሶ ሃይማኖት ከፖለቲካ ጋር ምን አገናኘው” ይለኛል። እኔም በስሜት ተሞልቼ እንዴት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ምን ጊዜ ከፖለቲካ ነጻ ሁና ታውቃለች። ከአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን እንዲያውም ከዚያ በፊት ጀምሮ ይችን ሃይማኖት ለማጥፋት ያልመጣባትና ያልሞከረ ጠላት አለ ወይ? እያልኩ እጠይቀዋለሁ። በዚህ መሃከል የት ቦታ እንዳለሁ ሳላውቀው ዙሪያው ላጥ ያለ ገደል ሆኖ ከመሃል ላይ ሜዳ ከሆነ ተራራ አስቀምጠውኝ ተሰወሩ። እኔም በዚህ እንዳለሁ ባነንኩ።

## <u>ራዕይ በኢትዮጵያ፤</u>ሐምሌ፡፳፩፡ቀን፡፪ሺ፪ (21/2002፤ዓ/ም)

በመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በአል ዕለት በዚያን ሌሊት ስለ ሀገር የታየ ራዕይ። ከሙታን የተነሱ ሁለት ሰዎች አንድ ወንድና አንዲት ሴት መነኩሴ ሁነው ወደ እኔ ይመጣሉ። ወንድየው *ታህሳስ* ፲፬፡ቀን፡፲ ፱ ፻፺፯ (14/1997፤ዓ/ም ) እንዲሁ በዚያን ጊዜ የተገለጸልኝ ዘለቀ የሚባለው ሰውየ ነው። የሴቷ መነኩሴ ስም ልክነሽ ትባላለች፣ ከኔ ትንሽ ፈንጠር ብለው ቁመዋል። ሴቷ መነኩሴ መልኳ የወይን ጠጅ የመሰልች እንደ ወርቅ የምታብረቀርቅ የእጅ መቁጠሪያ ይዛለች። ወንድየው ይመጣና “ሂድና የእጅ መቁጠሪያዋን ተቀበል” አለኝ። እኔም እሽ ብዬ ሄድኩ፣ ደርሼ መቁጠሪያሽን ስጭኝ ብላት አልሰጥህም አለችኝ። ተመልሼ ሂጄ አልሰጥህም አልችኝ አልኩት። ከዚያ እሱ ሄደና ተቀብሎ አምጥቶ “እንካ ብላት” አለኝ። እኔም ተቀብየ መቁጠሪያዋን በላኋት፣ ስበላት ምንም አልታወቀኝም ሳላምጣት ሳትሰበር ሂዳ ከሆዴ ተቀመጠች። በኋላ የሰውነቱ ቆዳ ከአጥንቱ ጋር የተጣበቀ የለበሰው ልብስና ጢሙ እንደ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ፤ የእንባው ብዛት እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ያለ፤ አንድ ሰው ከእርሻ መሃል ቁሞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ ዞሮ ይጸልያል፤ ያለቅሳል፤ ይወድቃል ይነሳል፤ ይለምናል። እያለቀሰ የሚለምነውም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የቆመበትን የእግሩን ኮቴና ቃሉን “በእኔ ላይ ይሁንልኝ” እያለ ይጸልያል። ሲለምንም “እግርህ የቆመበት አፈር ተነስቶ ከደረቴ ላይ ይለጠፍ፣ ቃልህ ከራሴና ከልቤ ውስጥ ይቀመጥ ይደር” እያለ ፣በጣም እያለቀሰ ይለምናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቁሞባት የነበረው አፈር እንደ ብራና ተጠቅልላ ተነስታ ከደረቱ ላይ ተለጠፈች፣ ሲታይ ልክ የእግሩ ጫማ የአረፈበት ነው፤ የሚመስለው። አሁንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በሰውየው እራስ አድርጎ ከልቡ ላይ ሲቀመጥ ይታያል። ቃሉ ከራሱና ከልቡ ከተቀመጠ በኋላ ሰውየው ከወደቀበት ተነሳ። ከዚያ በኋላ እሱን የመሰለ ሰው ፈልጎ ለማግኘት በአራቱ መአዘን በምሥራቅ፣ በምዕራብ፤ በሰሜንና በደቡብ፤ ኢትዮጵያን በሙሉ ዞራት ፈልጎ ግን ሊያገኝ አልቻለም። እንደ እሱ የታረዘና የተራበ የሰውነቱ ቆዳ ከአጥንቱ ጋር የተጣበቀ በጾም በጸሎት የተጠመደ ሰው አጣ። ከዚያ ምርር ብሎ አለቀሰ ፣እንባውን እንደ ውሃ አፈሰሰው፤ እሱ እንደዛ ሆኖ ሳየው፤ እኔም ካለሁበት ሁኜ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። ከቆመባት የእርሻ መሬት ላይ እንዳለ እንደ ነፋስ ሽው ብሎ ተሰወረ። እሱ ሲሰወር በጎኔ ቁመው የነበሩት ወንድየውና ሴቷ መነኩሴ አብረው ተሰወሩ። እኔም ብቻየን እያለቀስኩ ከሜዳው ላይ ቀረሁ።

## ራዕይ በኢትዮጵያ፤የሆሳዕና፡ዕለት፤ያየሁት፤
## ሚያዝያ፡፱፡ቀን፡፪ሺ፫ (9/2003፤ዓ/ም)

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ መሐንዲሶች ትግራይን ሊገነቡ እቃቸውን ወይም መሳሪያቸውን ይዘው በሙሉ ይሄዳሉ። እኔም እንደነሱ ስሚንቶ ላቦካ ድንጋይ ልሸከም አካፋና ዶማ ይዤ አብሬ ሄድኩ። ሁሉም ሰው ወደ እየ ሥራው ሲሰማራ እኔ የያስኩትን አካፋና ዶማ አስቀምጬ ኢትዮጵያውያንና የውጩ ዜጋ ወደ ተሰበሰበበት ትልቅ ሜዳ ወርጄ ሄድኩ። ከዚያ ስደርስ ልክ እንደ በርኒል (ጀርመን) ያለ ትልቅ ግምብ ተገንብቶ አገኘሁ። ከዚያ ላይ ወጥቼ ወደታች ስመለከት ኢትዮጵያውያን የውጭ ዜጋውም ከዚያ ሜዳ ላይ ተኝቶ አየሁ። አንድ የውጭ ዜጋ ነጭ ሰው የራስ ጠጉሩ ጢሙን አሳድጎና አጎፍሮ ቀና ብሎ እኔን ሲያይ “ሃድጊ አማራይ ሃድጊ አማራይ” እያለ እየለፈለፈለፈ ወደ እኔ ይመጣል። ማነው ይህን ብሎ የነገረህ እያልኩ በጥያቄ ሳጣድፈው እሱ ግን መልስ ሳይሰጠኝ ደርሶ እግሬን ይዞ ጎትቶ ወደታች ሊጥለኝ ሲል፣ እንዳትይዘኝ እንዳትይዘኝ ብየ በኃይል ቃል ስናገረው ከግንቡ እግር ቀጥ ብሎ ቆመ።ለመሆኑ ሃድጊ አማራይ ማለት ትርጉሙን ታውቀዋለህ ወይ? ስለው፤ መልስም አልመለሰልኝም። እኔም ሃድጊ ማለት ትርጉሙ እንደዚህ ነው፤ የሰው ልጅ አህያ ይባላል ወይ? በል ማታ እመጣለሁ ጠብቀኝ አሳይሃለሁ ስል። ከዚያ ሜዳ ላይ ተቀምጦ የነበረ ሕዝብ በሙሉ ግልብጥ ብሎ በድንጋጤ ወደ እኔ ሲመጣ ተነስቼ ወደ ቀድሞ ቦታየ ወደተራራ ወጣሁ። ከተራራው ወገብ ስደርስ ጨለማ ሆኖ መንገዱ ይጠፋኛል። ከዚያ ሁኜ ስጨነቅ አንዲት ቀይ ወጣት ሴት ልጅ ትመጣና ከቤቷ ውስጥ አስገብታ መብራት አብርታ በጣም ጠባብ በሆነች መስኮት አውጥታ “በል እኔ እከተልሃለሁ” ብላ ሰደደችኝ። ሰራተኛው ሁሉ ከነበረበት ሥፍራ ስደርስ አንድም ሰው አላገኘሁም። መሳሪያውን እየያዘ ወደ እየመጣበት ሀገር ተመለሰ። ቀና ብየ ሳይ በትግራይ ክፍለ ሀገር አዳዲስ ህንጻዎች በሙሉ የቆመ ድንጋይና የተለበለበ ግንድ መስለው ጠቁረው እንደተጀመሩ ቁመው ሲቀሩ አየሁ።

## ራዕይ በኢትዮጵያ፤ የትንሳኤ ዕለት፤
## ሚያዝያ፡፲፮፡ቀን፡፪ሺ፫ (16/2003፤ዓ/ም)

ከቤተ ክርስቲያን ቆይቼ ከቤቴ ደርሼ ትንሽ ምግብ ቀምሼ ወደ ምኝታ ክፍል ገብቼ ተኛሁ። ሆዴን ቁርጠት አመመኝ። ትንሽ እንዳሳቃየኝ ወዲያው ከባድ እንቅልፍ ወሰደኝ። ሦስት የማላውቃቸው ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች በደን የተሸፈነ ከትልቅ ተራራ ላይ በጣም ቀጭን የሆነችና ጠመዝማዛ መንገድ ቅርጹ ሰርጓጅ መርከብ የመሰለ ነጭ አውቶቢስ አቁመው፤ ብዙ ነጫጭ ልብስ የለበሰ ሰው ቁመው ያሳፍራሉ። ከዚያ እኔንም ወስደው “በል ትኬት ቁረጥና ወደ ዓለም መጨረሻ ልንወስድህ ነው” ይሉኛል። እኔም አልቆርጥም መልሶም እናንተ አይደላችሁም የምትወስዱኝ፣ እኔ በራሴ ነው ትኬት ቆርጬ የምሄድ ብየ ቁሜ ስከራከር። አንዲት ትልቅ ቀይ ሴት አንድ ወንድ ልጅ ያላት ሁለት ሴቶች በቀኝና በግራ አጅበዋት እየተከራከርን ካለነበት ቦታ መጥታ ከፊታችን ቆመች። ቀና ብየ እሷን አየሁና ይህ ሁልሽ አደይ (እናቴ) ትኬት ቁረጥና እንውሰድህ እያሉ ያስቸግሩኛል ብየ ስነግራት። እሷም ሳትናገራቸው እነሱም ሳይናገሩ የያዙትን ሰው አሳፍረው በዚያች ጠመዝማዛ መንገድ አድርገው ተሰወሩ። እኔን ያች ትልቅ ሴትዮ ወደ ተራራ ይዛኝ ወጣችና፤ ከኔ ተሰወረች። ከተራራው ላይ ሁኜ ዘቅዝቄ ወደታች ስመለከት የኢትዮጵያን ከብት የሱዳን ሕዝብ ከትልቅ በረት ዘግቶ በረሃብ ይቆላዋል። ከብቱ ተዘግቶ ያለው ከተራራው ግርጌ ደልዳላ ከሆነ ሜዳ ከመሰለ ሥፍራ ነው። ያ ጥቋቁር ሕዝብ ደግሞ ነጭ ጀለቢያውን ለብሶ ሂማውን ከራሱ ላይ ጠምጥሞ ከከብቱ በታች ጨለማ የሆነ ትልቅ ዋሻ አለ ፤ከዚያ ገሚሱ ከውስጥ ገሚሱ ከውጭ ሆኖ ቁሞ ይጠብቃል። በኋላ ከተራራው ተንደርድሬ ወርጄ ያን እንደ ግንብ ተገንብቶ ከብቱ የተዘጋበትን በረት በእጄ ስጫነው፤ በአንድ ጊዜ ተናደ። ከብቱም በዬ አለበት እየወጣ ሄደ። ሱዳኖቹም ሳይናገሩ እያዩ ቁመው ቀሩ።

## ራዕይ በኢትዮጵያ፤የግንቦት፤ልደታ፡ዕለት፤ያየሁት፤
## ግንቦት፡፩ቀን፡፪ሺ፫ (1/2003፤ዓ/ም)

አንድ በጣም ያረጀ ቀይ ሰው ቁጭ ብሎ ይሰፋል የሚሰፋው ነገር ግን አይታወቅም፣ አይታይም እንዲሁ እጁና መርፌው ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው የሚታየው። እኔም ለረጅም ሰዓት ከእሱ ጋር ከቆየሁ በኋላ ጥያቄ አቀረብኩለት ፤ጥያቄየም እንስሳቶች ተሰብስበው እባክህ ይህን ወንዝ አሻግረን እያሉ ይለምኑኛል ወንዙ ግን ደርቋል አልኩት። ሰውየውም "የምታየው ወይም የምሰማው ነገር አለ" ብሎ መለሰልኝ። ወንዙ በጎረንኮ ማርያምና በብራ ታዴዎስ መሃከል ያለ ድሮ በጋ ተክረምት የሚፈስ አሁን ግን የደረቀ ትልቅ ወንዝ ነው። ከላይ ከራሱ ሽማ ማጠቢት ሲባል ከታች ደግሞ ወደ ሰንበትጌ ቅዱስ ሚካኤል መሻገሪያ ላይ፣ ባአታ ግራር ይባላል። ድሮ ዙሪያው በግራር ዛፍና በሸንሸና ዛፍ የተሸፈነ ነበር፣ ከብቱ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ካልሆነ በስተቀር ወርዶ ውሃ አይጠጣም። ምክንያቱም በዛፍና በቁጠማ የተሸፈነ ስለሆነ እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ነው። በኋላ ሂጄ ባአህታ ግራር ላይ ከደረቀው ወንዝ ዳር ከመንገዱ ተኛሁ። አንድ በጣም ቁመቱ እረጅም የለበሰው ቀሚስና በላይ የደረበው መጎናጸፊያ እስከ ተረከዙ የደረሰ ፊቱ የማይታይ በታች በምሥራቅ በኩል በደረቀው ወንዝ አድርጎ እረጅም ቀይ ዘንግ ይዞ ወደ እኔ መጣ። እኔም እሱን ቀና ብየ ለማየት ስለፈራሁ ተኝቼ ጸጥ አልኩ፣ እሱም አልፎ የሚሄድ መስሎ ዞር ብሎ በያዘው ዘንግ ቀኝ ጎኔን ጉስም አድርጎ ወደ ጎረንኮ ማርያም ሄደ። ከዚያ ወንዝ ዳር እንደሆንኩ በሌሊት ተነስቼ የዘወትር ጸሎት ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃንና ይዌድስዋ መላእክትን፣ እደግማለሁ። ገና የዘወትር ጸሎት ስጀምር አንድ ከሙታን የተነሳ ሰው የምደግመውን ጸሎት ሊያሳስተኝ ይታገለኛል። እኔም እንዳይዘኝ ሁኜ ለእሱ ሳልናገር በዚህና በዚህ ሊይዘኝ ሲያሯሩጠኝ በየ ፈፋው እየተደበቅኹ ሳልሳሳት በቃሌ እደግማለሁ። _**ስብሐት ለአብ ፤ስብሐት ለወልድ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ፣ ስል ከእኔ ተለይቶ ተሰወረ።**_ ከላይ የዘረዘርኳቸውን ጸሎት ደግሜ ስጨርስ ብርሃን በራ። ወዲያው ከብቱ ፣በጉ ፍየሉ ፣አህያው ፣ፈረሱ፣ በአንድ ላይ ተሰብስበው መጡ። ከዚያ ወንዝ ዳር ቁመው ወደ ምሥራቅ ዞረው እንደ ሰው ጉንብስ ቀና እያሉ ይሰግዳሉ። አንድ ትልቅ አጋዘን መጥቶ ከእነሱ ጋር ተቀላቅሎ አብሮ ሲሰግድ አየሁ።

## _ግንቦት ፳ቀን፣ ፪ሺ፫_ (20/2003፤ዓ/ም) የአየሁትራዕይ፤

ጠ/ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ለአማቱ ለባለቤቱ እናት በእሳርና በገለባ ቤት ሊሰራ ሕዝቡን ሰብስቦ ይጣደፋል ። ያ ገለባና እሳር የእንጨት ጣራ የለው ለግድግዳ የሚሆን ባላና ማረግ አቁሞ የሚይዝ ምሰሶ የለው ቢቆልሉት ዙሮ ይፈርሳል፣ ዝምብሎ ይድክማል ሰውም አብሮ ተሰለፈ እንጂ እንዲሁ ቆሞ የጎሪጥ ያ የዋል። ከውጭ ተነስቼ ከዚያ ከሚሰራበት ቦታ ደረስኩና ከላይ የዘረዘርኳቸውን ቆጥሬ መሰረት የሌለው ምን አይነት ቤት ነው የምሰሩ ብየ መሰረቱን እኔ እጥላለሁ። ሕዝቡ የሰውየውን መጥፎ ሥራ ዘርዝሮ ከነገረኝ በኋላ "እንዴት ከዚህ ጋር አብረህ ትሰራለህ" አለኝ። እኔም ይህ እናንተን አይመለከታችሁም የሚመለከተው ሌላ ክፍል አለ ብየ ነገሩን ስዘጋ። አቶ መለስ "በእኔ ባንዴራ ለምነው የማታምኑ ብሎ ሲጠይቅ" ሕዝቡ እንዳለ ግልብጥ ብሎ ወደ እኔ መጣ። ቤቱን በህብረት ሰርተን ከጨረስን በኋላ ሕዝቡን ወደ ቆጥ አልጋ ይዤው ወጣሁ። አቶ መለስ የኳስ ቅርጽ ያላት እንደ ወርቅ የምታብረቀርቅ ሲይዞአት የምታሙለጨልጭ መልኳ ኩል የመሰለ አንዲት ትንሽ ድንጋይ ሲቀርባት ዓይኑን ትወጋዋለች ሊይዛት ሲል ከእጁ ታመልጣለች ለሕዝቡ ግን እንደ ኩል ጠቁራ ታብረቀርቃለች እንጂ ዓይን አትወጋም። ሕዝቡንም ቢጣራ ሂዶ የሚረዳው አላገኘም፣ ብቻውን ማንሳት አቅቶት፤ ከወገቡ በታች ጨርቅ አገልድሞ በላበት ተነክሮ (ተውጦ) የሚረዳው አጥቶ፤ ከሰው ጋር ከተራራው ሳይወጣ ብቻውን እያለህለህ ከታች ወድቆ ቀረ። ከዚያ በኋላ ከሕዝቡ ነጥሎ መንፈስ ቅዱስ በደመና አድርጎ ወደ ደቡብ ክፍለ ሀገር ወስዶ ከበረሃ ጣለኝ። ብቻየን ከበረሃው ወጥቼ ከትልቅ ሜዳ ላይ ደረስኩ ያ ሜዳ ዙሪያው በባሕር ተከበበ ከትንሽ ደሴት ላይ ቁሜ ባሕሩን ልሻገር ፈራሁ፤ ዞር ስል በአለት ድንጋይ የተገነባ ግምብ ቆሞ አየሁ፣ ያን በእጄ ስመታው እጄን ወደ ውስጥ አስገባው። ሌላው ሰውነቴ ወደ ኋላ ቀርቶ እጄ ብቻ ተቀርቅሮ ስሰቃይ ሁለት የከብት እረኞች እያለቀሱ መጥተው ጎትተው አወጡኝ። ተሸክመው ባሕሩን አሻግረው ከአንድ ገበሬ ቤት ወስደው አግብተው እንጀራ ስጡት ብለው ተነስተው ሄዱ። ሴቲቱ ማጀት ገብታ እንጀራ በወጥ አድርጋ አቀረበችልኝ። ባልየውም ሚስቱም እኔ የምጠይቃቸውን አልመለሱልኝም ዝም ብለው "አዳነነ አዳነነ" ይላሉ። ቋንቋቸው ኦሮሞኛ ነው፣ አማርኛ አችሉም ወይ ስላቸው አሁንም "አዳነነ አዳነነ" ይላሉ። በሉ እኔም አዳነ ነው ስሜ፣ አይዞአችሁ ሌት ተቀን ጸልዩ እንደ ጥንት አባቶቻችን በፍቅር ተሳስረን አንድ የምንሆንበት ጊዜ

ተቃርቦአል ብየ፣ የአቀረቡልኝን እንጀራ ሳልበላ ከእነሱ ተለየሁ። ሰዎቹ በመልካም አስተያየት እንግዳ መቀበላቸውና ጸባያቸው ፍቅራቸው በራዕይ ያ የሁት እስካሁን በገሃድ ያ የሁት መስሎ ነው የሚታየኝ። ቀጥሎም ከግንቦት ማለቂያ ላይ (፪ሺ፫ ዓ/ም) አቶ መለስ የሰሜኑ ጦርነት "አስፈርቶኛል" ብሎ ሊወጣ ጓዙን ሲጠቀልል አየሁት። በአጠቃላይ የታየው ራዕይ ይዋል ይደር ይዘገይ እንደሆነ እንጂ መድረሱ የማይቀር ነው። በሊቢያው መሪ በሞአመር ጋዳፊ የታየው ራዕይ፣ ከአስር ዓመት በኋላ ተፈጸመ። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጥቅምት ወር ፡በ2003፤ ሞአመር ጋዳፊን ሁለት ንጉሦች ከፈረስ ሲያወርዱት አየሁ። ስበቡ በራሱ ሰዎች ይሁን እንጂ በእንግሊዝ መንግሥትና በፈረንሳይ መንግሥት መውረዱ የታወቀ ነው።

## <u>ነሐሴ፤ ፲፪ቀን፡ ፪ሺ፫</u> (12/2003፤ዓ/ም)

ስለ ሀገር የታየ ራዕይ አንድ ቀይ ሰው ነጭ ልብስ የለበሰ ክንፍ ያለው፤ አቶ መለስን ሊገድል በክንፎቹ በሮ ከግቢው ይገባል። ከግቢው ገብቶ ሲያይ ፣አቶ መለስን ዙሪያውን ከበው የሚጠብቁ ጥቋቁር አንበሳዎች አንገታቸውን ወደ ምድር ደፍተው በልባቸው ተኝተው ያያል። እነሱን ጠቅጥቆ አልፎ አቶ መለስ ወደ ተኛበት ሲያመራ፤ ከትኩስ መቃብር ገብቶ አፈሩን በበላዩ ሳይለብስ በነጭ ልብስ ተጠቅልሎ እግሮቹን ዘርግቶ ተኝቶ አገኘው። ከዚያ ቁሞ አየና ይህስ ሙቶአል ብሎ፤በክንፎቹ በሮ ከግቢው ወጣ። ከግቢው እንደወጣ በክንፎቹ መብረሩን ትቶ በእግሩ እየተራመደ ሄደ።

## <u>በጥቅምት ወር፡፪ሺ፬</u> (2004፤ዓ/ም)

አባ ጳውሎስ ሙተው ሕዝቡ ለቀብር እንዲወጣ መንግሥት ያስገድዳል። ሕዝቡም በነቂስ ወጥቶ ሬሳውን በቃሬዛ (በአልጋ) ተሸክሞ በመንገድ ይጓዛል። ሁለት ቁመታቸው እረጃጅም ቀያይ ሰዎች በእበት በተለቀለቀ አውድማ ትልቅ የስንዴ ምርት አምርተው ቁመው ይጠብቃሉ። በአውሮፓ አገር የተነሳ ትልቅ አውሎ ነፋስ ምርቱን ወደ ምሥራቅ በተነው። የስንዴውን ምርት በትኖ ከአጠፋ በኋላ አባ ጳውሎስን ሊቀብር የወጣውን ሕዝብ ከአውሮፓ ተነስቶ የሄደው ነፋስ ካህናቱንም ጨዋውንም ከመሃል ገብቶ እያስጨነቀ በታተነው። ሕዝቡም በየ ዛፉ፤ በየ ስርቻው፤ በየ ዋሻው፤በድጋይ እግር እየገባ ተደበቀ። አባ ጳውሎስ ከቃሬዛ ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ሳይቀብራቸው ጥሏቸው ሸሸ። ከሜዳ ላይ ብቻቸውን ያለ ቀባሪ ወድቀው ቀሩ።

## <u>መጋቢት ፲፪፡ቀን ፤፪ሺ፬ (12/2004፤ዓ/ም) በሀገር የታየ ራዕይ፤</u>

ይህውም በሰሜን ጎንደር ቦታውን ገልጾ መናገር አያስፈልግም በፈተና ላይ ያለው ነው። ከዚህ በውጭ ሀገር እንዴት እንደ ሄድኩ ሳላውቅ ከደጋ ተነስቶ ጥቅጥቅ ካለ ደን ጫካ ውስጥ ክብረ በአልና ጥምቀትን ሊያከብር ከሚጓዝ ብዙ ሕዝብ ጋር ሂጄ ተቀላቀልኩ። ስቀላቀል ግን እኔ የለበስኩት ልብስ ሕዝቡ ከለበሰው ልብስ የተለየ ነበር፤ በተለይ ከራሴ ላይ የደፋሁት ባርኔጣ መስቀለኛ ሆኖ በጎንና በጎን ያለው ታጥፎ ታስሮአል ፤በፊትና በኋላ ያለው ደግሞ ተዘርግቶአል። የተሰራውም ከሐር ሆኖ መልኩ ሰማያዊ እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቅ ነበር። ሕዝቡ መንገዱን አቁሞ እኔን ይመለከታል፤ በዚያ መሃከል እንዳለሁ ከሕዝቡ ተለይቼ ወደ ትልቅ ተራራ ተወሰድኩኝ። እንዴት እንደሄድኩና ማን እንደወሰደኝ ግን አላውቅም ነበር። ከተራራው ላይ ሜዳ ሆኖ ወደታች ግን ከሰማይ ያራቀ ላጥ ያለ ገደል ነው። በላይ በኩል ቀጥ ያለች መንገድ ሆና በአንዲት ማገር በተያዘች በቀጭን እንጨት ሰው ዘሎ እንዳይወጣ ታጥራለች መንገዷ የአንድ ሰው እግር ጫማ እኳ ሞልታ አታስረግጥም። በዚያች ቀጭን መንገድ እግርና እግሬን እያተላለፍኩ ያችን ቀጭን እንጨት በግራ እጄ ጨብጬ ይዤ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስሄድ የያዝኳት እንጨት ዘመም ትልና ከገደሉ ጫፍ ታደርሰኛለች። ወደ ታች ሳይ ትላልቅ ዓይን ያላቸው ሰው የመሰሉና እባብ ሌላም ሌላም እንሥሳት የመሰሉ እኔን ወደ እነሱ እየጠቀሱ ከገደሉ ተለጥፈው አየሁ። በዚያን ሰዓት በድንጋጤ እየተንቀጠቀጥኩ ፈጣሪየን ስማጸን ድንገት ያ ገደል ወደ ጫካ ደን ተቀየረ። ከዚያ ጥቅጥቅ ካለ ዱር ውስጥ ዓይን ያለው ነጭ ስንዴ በቀለ ወዲያው እሸቶ ደርቆ ታጨደ። የታጨደውን ብዙ ሰው እየተሸከመ ሁለት ሰዎች በጣም ትልቅ የሆነ ክምር እንደ ቤት ክዳን

አለባሶውን አድርገው ይከምራሉ። በዚህ እየተገረምኩና እየተደነቅሁ ፍርሃቴ ለቆ ክምሩም ተከምሮ ማለቁን ሳላይ ድንገት ፏፏቴ ካለበት ወንዝ ደረስኩ። ወንዙን ተሻግሬ ሰው ወደ አለበት መንደር ስሄድ የስንዴውን ክምር ሲከምሩ የነበሩ ሁለት ቀያይ ሰዎች ከወንዙ ዳር ቁጭ ብለው፤ አንድ ጠይም ሰው የኔን ባርኔጣ ቀምቶ እንዲወስድላቸው ላኩት። ሰውየው ገስግሶ ከእኔ ደርሶ ባርኔጣህን አምጣ አለኝ። እኔም አልሰጥም በዬ ስከራከር ትልቅ ሰይፍ መዘዘብኝ። ባርኔጣየን በብብቴ ውስጥ ደብቄ የመንደሩን ሰው ድረሱልኝ ብዬ እየሮጥኩ ስጣራ ፤ጥቂት ትላልቅ ሰዎችና ብዙ ሕጻናት ልብሳቸው አልቆ ግማሽ ገላቸው በጸሐይ ተቃጥሎ ሰውነታቸው በረሃብ ተጎሳቁሎ በአማጋው ብቅ ብቅ አሉ። ሰውየው እነሱን ሲያይ እኔን ትቶ እነሱን ሊገድል አልፎ ገስግሶ ሄደ። የረሃባቸውና የርዛታቸው አልበቃ ብሎ ልትገላቸው ነው ይህማ አይሆንም፤ በኔ ምክንያት አትገላቸውም ብዬ የደበቅኩትን ባርኔጣ ሰው እንዳያይ አድርጌ በልብሱ ውስጥ አስገባሁለት። ሰው እየተሯሯጠ ሲመጣ ከትላልቆቹ ቀድመው ሕጻኖቹ ደረሱ። ሰውየውን ዙሪያውን ሲከቡት ያችን መስቀለኛ ባርኔጣ ወደ ሽንብራ እሸት ቀይሮ በጣት ቀለበት የምትሞላ አድርጎ ለኔና ቀድመው ለደረሱት ሕጻናት ሰጥቶ ወንዙን ተሻግሮ ሂዶ ከሁለቱ ሰዎች ጋር ተቀላቀለ። ወዲያው አብረው ሶሥቱም ተሰወሩ። እኔ የተቀበልኳትን የሽብራ እሸት ለቀረው ሰው ለሁሉም አድየ(ሰጥቼ) አዳረስኩት። ሰውም በዚያች ትንሽ ሽንብራ እሸት ሆዱን ሞላ። እኔም ከዚያ በኋላ ከሕዝቡ ጋር ተለያየሁ። እንግዲህ ይህ ራዕይ በጣም ከባድ ነው፤ እግዚአብሔር የገለጻላቸው የበቁ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ማንም አይፈታውም።

## <u>ሐምሌ፡፲፪ቀን፡፪ሺ፬ (12/2004፤ዓ/ም)</u>

ጥቁር መሬትና ቀይ መሬት በአለባት ሀገር ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ብዙ ጥቋቁር ከብት ሀገሪቱን አጥለቅልቋት አየሁ። ከዚያች ሀገር ሂጄ ትልቅ ሰው ብፈልግ አጣሁ። ይቅር በከተማው በገጠሩም ሆነ በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ በአራቱ መአዘን ብፈልግ ሳላገኝ ቀረሁ። በዚህ የተነሳ እያዘንኩና እያለቀስኩ ሳለ፤ አንድ ትልቅ ቀንድ ያለው በሬ ድንገት ከተራራ ላይ ወርዶ ወደ እኔ መጣ። ወዲያውም በምሥራቅ በኩል በጎረንኮ ማርያም ገዳም አድርጋ የምታስፈራ ትልቅ ቀንድ ያላት ላም ወደ በሬው መጣች። ላሚቱ ከበሬው ልትደርስ ትንሽ ሲቀራት ከግባሯ ላይ የወጣው ብርሃን ተወርውሮ ከመሬት ላይ ሲተከል አየሁ፥ ወዲያውም ሳታምጥ ወንድ ጥጃ ወለደች። ጥጃውም ፊቱ እንደ አንበሳ የሚያስፈራ ሆኖ በአንድ ጊዜ አድጎ ትላልቅ የሚያስፈራ ቀንድ አውጥቶ፤ ያን ጥቋቁር ከብት፤ ወግቶ ወግቶ ፤ሲጥለውና ገድሎ ሲጨርሰው አየሁ። የበሬው የላሚቱና የጥጃው መልካቸው አንድ አይነት ነው። የሁሉም ዓይናቸው ፊታቸውና ቀንዳቸው በጣም ስለሚያስፈራ እኔም ቀና ብዬ ላያቸው አልቻልኩም፤ አንገቴን ወደ መሬት እንደደፋሁ ሁሉም በአንድ ጊዜ አብረው ተሰወሩ። ያ ጥቋቁር ከብትም በሙሉ አልቆ ቦታው ባዶውን ሲቀር አየሁ። ስለዚህ አካባቢ ትንሽ ልበል ይህ ቦታ የሚገኘው በሰሜን ጎንደር በወገራ አውራጃ የሚገኝ ሲሆን የበቁ አባቶች ልክ እንደ ጎንደር አርባ አራት ቤተ ክርስቲያን ይተከልበታል ብለዋል ተብሎ ሲነገር ሰምቻለሁ። ነገር ግን ብዙ ደስታንና ጅግር እንደታየበት፤ ብዙ ፈተናዎችን እንዳስተናገደ የሚታወቅ መሆኑን እኔም ደርሼ በዓይኔ የአየሁት ስለሆነ የሚታወቅ ነው። በጣሊያን ጊዜ የሆነውን ልለፈውና እኔ ከደረስኩ ያየሁትን ለመግለጽ ልሞክር። በአብዮቱ ፍንዳታ ወቅት በደርግና በኢድዩ የተካሄደውን ጦርነት፤ እንዲሁም በደርግና በወያኔ የተደጋገመ ጦርነት የተካሄደበት ቦታ ነው። የደስታውና የጥጋቡ ዘመን የታየበት አካባቢው በተፈጥሮው ለምለም ስለሆነ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚመረትበት በመሆኑ በደርግ ዘመን በምርት አንደኛ ሆኖ የተመዘገበበት ወቅት ነበረ፤ ሕዝቡም ጥጋብ እንጂ ረሃብ አይቶ አያውቅም ነበር። እንግዲህ በደርግና በወያኔ በፊትም ያየሁት በኋላም የሰማሁት የተካሄደውን ጦርነት ደርግ ከጉንኮ ተራራ ላይ ሆኖ ሲመሽግ ወያኔ ደግሞ ከአመድጌ ተራራ ላይ መሽጎ ለረጅም ወራት በከባድ መሳሪያ ሲጠዛጠዙበት የነበረ ነው። አሁን እኒያ ተራራዎች ከጦርንርት ቀጠና ነጻ ሁነው አመድጌ ተራራ ለበቁ ሰዎች በራዕይ ተገልጦ የዮሐንስ ነጎድጓድ ቤተ ክርስቲያን ተገድሞበታል። እንዲሁም የጉንኮ ተራራ የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተተክሎበታል። መጀመሪያ ከዚያ ተራራ ላይ ሕዝቡ የእሳር ጎጆ ሰርቶ የቅዱስ ያሬድን ታቦት አስገብቶ ሳለ ደርግ በእርሻ ማህበር ያደራጃቸው ሰዎች ሌሊት ያን የሳር ጎጆ አፍርሰው ጣሉት፤ ካህናቱም ታቦቱን ተሸክመው በተራራው ላይ ለሳምንታት ያህል ከቆዩ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል የተገለጠላቸው ሰው የሥላሴን

ታቦት እንጂ ከዚያ ቦታ መትከል ያለባችሁ ተብሎ ለሕዝቡ ተነገረው፤ እንዲሁም የቅዱስ ያሬድን ታቦት በተደራቢነት እንጂ በእሱ ስም አታስገቡ ታባሉ።
ከዚያ ሕዝቡ ተሰብስቦ ከተወያየ በኋላ ሰፊ ቤተ ክርስቲያን ተሰራ ታቦቱም በደማቅ ሁኔታ ከቦታው ገባ ጠላትም ሁለተኛ ያን ቤተ ክርስቲያን አልነካውም። እንደገና አሁን የአማረ ህንጻ ተሰርቶለት ግልጋሎቱን እየሰጠ ይገኛል። እነዚህ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ሲተከሉ ሌሎችም በክርስቲያኑና በሞስሊሙ ወንድሞቻችን ብዙ ቤተክርስቲያናት ተሰርተዋል። ይችን ትንሽ ከተማ በአሁኑ ሰዓት አስራ ስድስት ቤተ ክርስቲያን ዙሪያዋን እንደ ሙሽራ ከበዋት ይገኛሉ፤ከአስራ ስድስቱ አምስቱ ወያኔ ከገባ በኋላ የተሰሩ ናቸው። ለነዚህም ከፍተኛ ተአምር ሲሰሩ የታዩ ገዳም የተባለችው የዮሐንስ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያንና የባህታ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ከነዚህ ከሁለቱ ደብሮች የአንዳቸውን የአሳዩትን ተአምር ልናገር በዮሐንስ ነጎድጓድ ተራራ ላይ የነበረውን ደን ወያኔ ቢጨፈጭፈውም ሕዝቡ እንደገና ባህርዛፍ ተክሎ መልሶ ጫካ አደረገው። ቤተ ክርስቲያኗ ሥትሰራ ሕዙቡ ለደብሯ አበረከተ በኋላ ግን ሰው ጭቅጭቅ ፈጥሮ የእየ አካባቢውን ቆርጦ ወስዶ ሊጠቀም ሲያስብ መጀመሪያ ጭቅጭቅ የተነሳበትን ቦታ በአንድ ሌሊት አድርቆት አደረ። ከዚያ በኋላም ሕዝቡ ፈራና መቁረጡን አቆመ።

*አንዱ፡- ኢታልቅስ፤ እንሆ፥ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነስቶአል አለኝ። በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሊቃውንቱም፤ መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፥ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት፤እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው። (የዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ።፭፡ከቁጥር፡፭-፯።) እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦኢታልና፥ ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶኢታልና፤እንዲህ ብሎ፡-ይህች ለዘላለም ማረፊያዬናት፤መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ። አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፥ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ። ካህናቶችዋንም ደኅንነት አለብሳቸዋለሁ፥ ቅድሳኖችዋንም እጅግ ደስ ይላቸዋል። በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፥ ቀብቼ ላነገሥሁትም መብራትን አዘጋጃለሁ። ጠላቶችንም አፍረትን አለብሳቸዋለሁ፤ በእርሱ ግን ቅድስናዬ፤ ያብባል። (መዝ፤131። ቁ፤13-18።)*

እንዲሁም ኢትዮጵያን ከድንግል ማሪያም ተወልዶ በሄሮድስ ዘመን ከእናቱ ጋር ተሰዶ ለሦስት ዓመት ያህል የቆየባት፤ በመስቀ ላይ ሆኖ ክቡር ደሙን በብርሃን ጽዋ በቅዱስ ዑራኤ አማካይነት ማርና ወተት ይዝነብብሽ ብሎ የባረካት፤በዋልድባ ገዳም እራሱ ተገልጦ ተአምር ያሳየባትና ስራእቱን የአስቀመጠባት፤በመጽሐፍ ቅዱስ ከአርባና ከአምሳ በላይ ቃሉ የተነገረባት፤በመጨረሻም በዘንግ የሚገዛ ንጉሥ ይመጣል ብሎ ቃል የገባላት፤ሀገር ስለሆነች፤ ልክ እንደ ኢየሩሳሌም እሱ እንደማይለያትና ኃያልነቷን ያረጋገጠባት ሀገር ነች። ለእነ አብርሃም ፤ለእነ ያእቆብ፤ ለእነ ዳዊት ቃል በገባው መሰረት ኢየሩሳሌምን እንደ ባረካትና እንደ አዳናት ሁሉ ። ኢትዮጵያንም ለአለፉት ቅዱሳን አባቶቻችን ቃል በገባው መሰረት ፈጽሞ ይባርካታል። ከአለባት የእርስ በርስ ጦርነት፤ ከረሃብና ከችግር አላቀ ከመመጽዋትና ከልመና ያድናታል፤ከወደቀችበትም ያነሳታል፤ክብሯን መልሶ ያጎናጽፏታል።

## ግንቦት ፡፴ቀን፡ ፪ሺ፬ (30/2004፤ዓ/ም)

አንድ ደሳለኝ ይሚባል ቀይ ሰው ባህታ አወጣችህ ማርያም ቆመችልህ ብሎ ሲያበቃ ጥንት ወደ ተመሰረተች ቤተ ክርስቲያን የማሳይህ አለ ብሎ ሲወሰደኝ ይህንማ አይቸዋለሁ ስለው። አይ አንተ ያየህ ይህነው እኔ ግን የማሳይህ አዲስ ነገር ነው አለኝ። በጸሐይ መግቢያ በኩል ሜዳ ሆኖ ለቤተ ክርስቲያኗ የሚጠቀሙባት ዙሪያዋ በካብ የተካበች ምንጭ አለች ከእሷ ጠጥቼ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ቅጥር ግቢ ደረስኩ። ከዚያ ደርሼ ዙሪያዋን ስጎበኝ በጸሐይ መውጫ በኩል ብዙ ነጫጭ በጎችና ብዙ ነጫጭ እርግቦች ተሰብስበው አገኘሁ። በጎቹ እሳር አይለቅሙም እርግቦቹም እንዲሁ መሬት ጭረው ጥሬም ይሁን ሌላ ነገር አይጠቀሙም እንዲሁም ተሰብስበው ቁመዋል። የአሉበትም ቦታ ቤተ ክርስቲያኗ የተሰራችው ኮረፍታ ተራራ ላይ ስለ ሆነ በጎቹና እርግቦቹ ከቤተ ክርስቲያኗ ግርጌ ከወገቡ ላይ ነው። ከእንስሳቶቹ በታች ላጥ ያል ገደል አለ፤ ከእንስሳቶቹ መሃል ቁሜ እየተገረምኩ ሳለ ድንገት ትልቅ ጥቁር ዘንዶ ከአንገቱ በታች እንደ ትቦ ተጠቅልሎ ከአንገቱ በላይ ደግሞ ቀጥ ብሎ ወደ ሰማይ እያየ ተንከባሎ

ገደል ሲገባ አየሁ። ሁለቱም እንስሳቶች ተከፋፍለው የነበሩት ዘንዶው ከእነሱ ተለይቶ ተንከባሎ ገደል ከገባ በኋላ በአንድ ሜዳ ላይ ተቀላቅለው ሲኖሩ አየሁ። ***ይህን ራዕይ ፤ግንቦት ፳፱ ቀን፡ ፪ሺ፬ (29/2004፤ዓ/ም)*** ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሂጂ የእግዚአብሔር ኃይል በመምህር ግርማ ላይ አድሮ ድንቅ ተአምር ሲሰራና ሰይጣንን እያስለፈለፈ ሲያስወጣ ሳይ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ በእኔ ላይ አድሮ በራዕይ የገለጸልኝን እንደሚፈጸም ሳልጠራጠር አምኜ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ከዚህ በላይ ያለውን ራዕይ የገለጸልኝ በዚህው ሌሊት ነበር። ወዲያውኑም ወር ባልሞላ ውስጥ ቀደም ሲል በራዕይ የገለጸልኝን የአቶ መለስንና የአባ ጳውሎስን አማሟት አሳየኝ።

እንግዲህ ከላይ የተጻፈውን ዘርዘር አድርጌ ላቅርብ፤ በግንቦት ወር ወደ ሀገር ቤት በኀዘን ምክንያት ለአንድ ወር ያህል ተጉዤ ነበር። እና አንዳንድ ነገሮች ማለትም በህብረተሰቡ የሚደርሰውን አፈና፤ጭቆና፤ እና እንግልቲት እንዲሁም በአንድ ብሄር ተወላጆች አድሎ ሲደረግበት ሳይ ነጻነት በአለበት ሀገር ስለምኖር ስሜቴን መቆጣጠር አልቻልኩም። ስለዚህ የተሰማኝን ስሜት ለመግለጽ ተገደድኩ። በተለይ በአክሱም ኤርፖርትና በጎንደር ኤርፖርት በደረሰብኝ እንግሊትት ፓስፖርት እየታየ አነተ ወደፊት አንተኛው ደግሞ ወደ ኋላ በል እየተባለ ሲንገላታ አየሁ። እኔም ተራየ ደርሶ ፓስፖርቴን ሳሳይ ፈረንጅን ለማሳለፍ ብሎ ትግራይ ላይ አስተናጋጁ ወደ ኋላ ቆይ የሚል መልስ ሲሰጠኝ የተሰማኝን ስሜት ስገልጽ ደፋር የሚል ስም ተሰጠኝ። እንዲሁም ጎንደር ላይ በተሳፋሪውና በራሴ ላይ የደረሰውን በደል መቆጣጠር ስላልቻልኩ በተናገርኩት ቃላት ተገረመና አንተ ከሰማይ ነው ወይ የመጣሃው አለና ግዴታ እኮ የለብነም ያለመጫን መብታችነው ብሎ ሽቅብ ቁልቁል አየኝ።እኔም በህግሪቱ መንግሥት እንደሌለና የወሮበላዎች ሀገር መሆኗ አረጋገጥኩ። ከዚያ በኋላ ምንም ማድረግ ስለማልችልና አክስቴም ደግሞ ያሉህን ክፈል እባክህ ስትለኝ ተጽፎ የተሰጠኝን ትኬት ይዤ ገንዘብ ወደ ሚከፈልበት ቢሮ በምልክት ተነግሮኝ ሄድኩ። ከዚያ ስደርስ ከሁሉም የሚገርም ነገር ያየሁት ከጎንደር ሰው የጠፋ ይመስል ከትግራይ የመጣ ሰው ሲቀመጥ ለዚያውም ኩታራ ለትልቅ ሰውና ለእግዳ ክብር የማይሰጥ እኔም ከታች ያደረሱብኝን በደል አቤቱታ አሰማለሁ ብየ ያሰብኩትን አንደኛ በቋንቋ አንግባባም ይህስ የባሰ ነው እንጂ የተሻለ አላገኝም ብየ ተውኩት። እውነትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዓመታት አፍነው ይዘው ሲያስጨንቁት ያልተናገረውን እኔ ከውጭ ሂጄ እንደዚያ ስል ያስገርማል። ከዚያም ሂጄ በደረስኩበት ሥፍራ ሁሉ ህብረተሰቡን በአለው ስርአት ላይ የሚያነሳሳ ቃላት ስናገር ዘመዶቼም በሰላም ወደ ቦታህ ብትመለስ ይሻላል ምክንያቱም ከዚህ ሰላዩ ብዙ ነው ማን እንደሆነ አይታወቅም ደግሞም ለእኛ ችግር እንዳታመጣብን እና ስለዚህ በሰላም ድምጥህን አጥፍተህ ወደ አገርህ ተመለስ አሉኝ። አንዳንድ ጓደኞቼም ባክህን ከዚህ እንደፈለክ የምትናገረውን ከዚያም ሂደህ እንዳትናገር ብለው ማስጠቀቂያና ምክራቸውን ለግሰውልኝ ነበር። እኔ ግን ምክራቸውን አልተቀበልኩትም መክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጻፈ እንደማይቀር ስለማውቅ ጌታዬን ተማምኜ ሄድኩ። እንዳሉትም አደጋው ተጋርጦብኝ ኑሯል፤ እምነቴ ጽኑእ ስለነበር፤ የፈጠረኝ ጌታ እግዚአብሔር አላጋለጠኝም፣ እመቤቴም ታደገችኝ፤ ጠበቀችኝ እንጂ፥ በአውሬዎች እጅ ተይዤ እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሰለባ ሁኜ ነበር።

## ሚያዚያ ፳ ቀን ፡፪ሺ፫ ፡ ዓ/ም፤

የሆሳእና እለት ያየሁት ራእይ ፤እንደሚከተለው ይሆናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጭን መንገድ በተራ በሰልፍ ቁሞ አንዱን አንዱ ሳያልፈው ሁሉም ጸጥታ በሰፈነበት መልኩ እጆጁን ዘርግቶ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ፊቱን ዞሮ ሲመለከት አንድ ሰው የተዘጋጀ ምግብ አምጥቶ ሲመግበው አየሁ። የምግቡ አይነት ከአትክልት ፤ከአዝእርት ፤ ከፍራፍሬ እንዲሁም አይቸው የማላውቀው የምግብ አይነት አምጥቶ ሕዝቡን ከመገበ በኋላ ያነ ትልቅ ሰው ከሕዝቡ ተነጥሎ ተሰወረ። ሕዝቡም አንገቱን ዝቅ አድርጎ ሰግዶ ምግቡን ተቀብሎ ተመገቦ፤ከአበቃ በኋላ፤ በፍቅር፤በሰላም በአንድ ሆኖ ተጓዘ። እንግዲህ ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን መምጫ መቃረቡን የሚያሳይ ምልክት ነው። መጻፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን፤አንተም፡የዘንዶውን፡ራሶች፡ቀጠቀጥህ፤ለኢትዮጵያ፡ሰዎችም ፡ምግባቸውን ሰጣሃቸው። **መዝሙር ፤፸፬ (74) ቁጥር፡ ፲፬ (14)። በፊቱም ፡ኢትዮጵያ ፡ይሰግዳሉ ፥ ጠላቶቹም አፈር፡ ይልሳሉ። መዝሙር ፡፸፪(72) ቁጥር፤፱(9)።**

## **<u>ሐምሌ ፡፲፱ ቀን፡ ፪ሺ፭ ፤ዓ/ም፤</u>**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትልቅ አዳራሽ ተሰብስቦ መጠጥ ጠጥቶ ተሳክሮ እርስ በርሱ በሽመል ሲከታከት ሽመሉ ከሰው ሰውነት ሲያርፍ እንደ ጥይት ይጮሃል። የሟች ወንድም የገዳይን ወንድም ብድር መልሶ ይገድለዋል፤ አዳራሹ እንዲሁም ሜዳው እሬሳ በሬሳ ሆነ። ሟችም ገዳይም ማን እንደሆነ አይታወቅም እንዲሁ እሬሳ ወድቆ ሲታይ ምጣፍ የሌለው የጠፍር ዲንክ አልጋ እያመጣ እሬሳውን እየያዘ ይሄዳል። ወንድ ወንዱ እራቅ ብሎ ቆሞ ሴቶችን ሂዳችው ቅበሩ ይሏቸዋል፤ ሴቶችም ሊቀብሩ ይሄዳሉ። ከዚያ አንድ ትልቅ ሰው ወንዶች ተሰብስበው ከቆሙበት መሃል ሁነው አይ ይህ መከራ ጀመረ መጣበት እንግዲህ ይላሉ። እኔ ብድግ አድርጌ ከጀመረ ቆይቶአል ግን አልፈነዳም እላለሁ። **<u>ይህን ስል አንድ ድሮ የማውቀውን መምህር ተመስሎ ቀይ ሰው በራሴ በላይ ሆኖ አንተ ጸልይ፤ አንተ ጸልይ እያለ ደጋግሞ ይናገራል፤ እኔም ቀና ብዬ ሳይ ሰማይ እንጂ ሰው የለም የሚታይ።</u>** ከዚያ በኋላ እረጅም በትር ይዤ፤ እረጅም ቀሚስ ለብሼ ከሕዝቡ ተነጥዬ ወደ በረሃ እየሄድኩ ሳለ አንዲት ወጣትና አንዲት ትልቅ ሴት ለሁለት በጆንያ(በኬሻ) ሞልቶ የተሰፋ ነጭ ስንዴ ለሁለት ይዘው ሲሄዱ አገኘኋቸው። አልፌ ልሄድ ስል ፊቷን የሸፈነችው ትልቋ ሴት እረ እባክህ እርዳን እያለች ትለምነኛለች እኔም የኔ ሃይማኖት ሌላ የእናተ ሃይማኖት ሌላ እንዴት ይሆናል ይህ የሚያይ ሰውስ ምን ይል ስላት። እርዳኝ የምልህ እኮ እኔ ነኝ እኒህን አስመሳይ ተዋቸው ትላለች። እኔም በይ በልጅቱ በኩል ልያዝ ብዬ ስመለስ እኔም እኮ ልጅ ነኝ ትልና፤ ያን የተሸፈነችበትን ብጫ ጨርቅ አውልቃ ወርውራ ስጥለው ትልቅ ሴት የነበረችው በአንዴ ወደ ወጣት ተቀየረች። እኔም ነገሩ ገርሞኝ ቁሜ ሳለሁ፤ ሁለቱ ሴቶች ስንዴ የሞላውን ጆንያ ለእኔ ጥለውኝ ከፊቴ ተሰወሩ።

*ያች የፈተና ዓለም መድረሷን እያየሁ
ስጨነቅ ስቸገር ቀኑን እውላለሁ።
ፍርኃት አደረበኝ ያን የመከራ ቀን በህሊና ሳየው
ከሰዎች ጋር ሁኜ እርሜን እየበላሁ።
የት አባቴ ላምልጥ የትአባቴን ልድረስ
ያች መጥፎ ቀን ሳያስቧት ስትደርስ
ብወድቅ ብነሳ እንባዬን ባፈስ
ዓይኖቼን ጨፍኜ ወደ እርሱ ባለቅስ
የጌታዬን ቃሉን እያወቅሁ ሳፈርስ
ብጠራው አይሰማኝ ጸሎቴም አይደርስ።
እንዲያ ስጨነቅ ስቸገር እያየች
ሞትንም ብጠራት አልሰማህም አለች
የጌታዋን ትእዛዝ እርስዋም ታከብራለች።
ብወድቅ ብነሳ እንባዬን ባፈስስ
ዓይኖቼን ጨፍኜ ወደ እርሱ ባለቅስ
ባለቀ ሰዓት ላይ አይሰጠኝም መልስ
ፍረዴን መቀበል ነው ሰዓቷ ስትደርስ።
አወዩ አበሳዬ በደሌ መብዛቱ
የሰጠኝን እድሜ
ሳልጠቀምበት አለፈ ጊዜያቱ
ንስሐ ሳልገባ ቀረሁኝ በከንቱ።
ችግሬን ተመልከት በጭንቀት ነው ያለሁ
ለሥጋዬም አልሆንኩ ነፍሴን ጭምር ጎዳሁ
ተማለደኝ አምላክ ስምህን እጠራለሁ
ይቅር በለኝ ጌታ እኔስ በድያለሁ።*

***<u>“መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች። (ም፤13፡ቁ 1-13)</u>***

ፍቅርን፡ ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ፡ ስጦታንም፡ ይልቁንም፡ ትንቢት፡ መናገር፡ በብርቱ፡ ፈልጉ። በሰዎችና፡በመላእክት፡ልሳን፡ብናገር፡ፍቅር፡ግን፡ከሌለኝ፡እንደሚጮህ፡ናስ፡ወይም፡እንደሚንሽዋሸዋ፡ ጸናጽል፡ሁኛለሁ። ትንቢትም፡ቢኖረኝ፥ ምስጢርንም፡ ሁሉና፡ እውቀትን፡ ሁሉ፡ ባውቅ ፥ ተራሮችንም፡ እስካፈልስ፡ ድረስ፡ እምነት፡ ሁሉ፡ ቢኖረኝ፡ ፍቅር፡ ግን፡ ከሌለኝ፡ ከንቱ፡ ነኝ። ድሆችንም፡ ልመግብ፡ ያለኝን፡ ሁሉ፡ ባካፍል፥ሥጋዬንም፡ ለእሳት፡ መቃጠል፡ አሳልፌ፡ ብሰጥ፡ ፍቅር፡ ግን፡ ከሌለኝ፡ ምንም፡ አይጠቅመኝም።

ፍቅር፡ያስታግሣል፡ፍቅር፡ ያስተዛዝናል፡ፍቅር፡ አያቀናናም፡ ፍቅር፡ አያስመካም፡ፍቅር፡ አያስታብይም፡ ብቻዬን፡ይድላኝ፡አያሰኝም፡አያበሳጭም፡ለክፉ፡ነገርን፡አያሳስብም፡ከእውነት፡ጋር፡ደስ፡ይለዋል፡እንጂ፡ ስለ፡ዓመፃ፡ደስ፡አይለውም፡ሁሉን፡ይታገሣል፥ሁሉን፡ያምናል፥ሁሉን፡ተስፋ ያደርጋል ፥ በሁሉ፡ ይጸናል። ፍቅር፡ ለዘወትር፡ አይወድቅም፤ ትንቢት፡ ቢሆን፡ ግን፡ ይሻራል፡ልሳኖች፡ ቢሆኑ፡ ይቀራሉ፡እውቀትም፡ ቢሆን፡ይሻራል። ከእውቀት፡ከፍለን፡እናውቃልንና፥ ከትንቢትም፡ ከፍለን፡ እንናገራለንና፤ ፍጹም፡የሆነ፡ ሲመጣ፡ ግን፡ ተከፍሎ፡ የነበረው፡ ይሻራል። ልጅ፡ ሳለሁ፡ እንደ፡ ልጅ፡ እናገር፡ ነበር፥እንደ፡ ልጅም፡ አስብ፡ ነበር፥ እንደ፡ ልጅም፡ እቆጥር፡ ነበር፤ ጎልማሳ፡ ሆኜ፡ ግን፡ የልጅነትን፡ ጠባይ፡ ሽሬአለሁ። ዛሬስ፡በመስታዋት፡በድንግዝግዝ፡እንደምናይ፡ነን፡በዚያን፡ጊዜ፡ግን፡ፊት፡ለፊት፡እናያለን፤ዛሬስ፡ከእውቀት፡ ከፍዬ፡አውቃለሁ፡በዚያን፡ጊዜ፡ግን፡እኔ፡ደግሞ፡እንደ፡ታወቅሁ፡አውቃለሁ።እንዲህም፡ከሆነ፥እምነት፡ተስ ፋ፡ፍቅር፡እነዚህ፡ሦስቱ፡ጸንተው፡ይኖራሉ፤ከእነዚህም፡የሚበልጠው፡ፍቅር፡ነው”።እንግዲህ፤ቅዱስ፤ሐዋ ርያው በዚህም በሌላም ስለ ፍቅር በአጽንኦት ተናግሮአል።

**<u>ሰላም እንባባል እንመስርት ፍቅርን፤</u>**

ሰላም እንባባል እንመስርት ፍቅርን፤
ሰይጣን እንዲታሰር ተይዞ እጅና እግሩን፤
እንግዲህ ይበቃል መተረማመሱ፤
ልባችን አንድ ይሁን እንቅረብ ወደ እርሱ፤
ወደ ኃያሉ ጌታ ከፈጠረን እግዜር፤
ያሳለፍነው ችግር በደስታ እንዲቀየር።

    ተለያይቶ መኖር ከእንግዲህ ይቅርብን
    ደስታም ሆነ ችግር ደርሶአል ለሁላችን
    እንደ ጥንት አባቶች እንኑር ተስማምተን።

ከእግዲህ ይቅርብን መሄዱ በቡድን
በአንድ እንሁንና በእግዚአብሔር እንመን
የተከፋፈለው መንገዱ አንድ እንዲሆን።

    የምድሩ ሥራችን ከላይ ሲጠብቀን
    በቀኝ ሆነ ግራ ከግዜር ፊት ሲያቆመን
    መዋሸት አንችል እንደ ምድሩ መስሎን
    መዝገቡ ተከፍቶ ሲጠራ ስማችን
    ከቶ በዚያን ጊዜ ምን ይሆን መልሳችን
    መካድ አይቻልም እንደ ሰው ፈጣሪን።

አልተጠቀምንበት የተሰጥን ጊዜ
ለንስሐ ቀርበን አላረግን ኑዛዜ።

    መሄዳችን ላይቀር ፊትና ኋላ ሁነን
    ከአሁኑ እናዘጋጅ ዋስ ጠበቃ የሚሆን
    በላይኛው ቤት ስንጠየቅ ቁመን
    ለሰራነው ሥራ መስክሮ የሚያወጣን
    አሁን እናዘጋጅ ጊዜው እንዳያልፈን።

ቤታችን እንስራ ከዐለት ቆፍረን
ወጀብ የማይጥለው የማያረጀውን
የምድሩን ሳይሆንስ የላይ የሰማዩን
እንዳናጣ መግቢያ ስንሄድ ጠቅልለን።

እሱን እንለምን ሁነን በኀዘን በትካዜ፤
ከሙሽራው ቀርበን እንድንሆን ሚዜ፤
ልብሳችን እንጠብ ባዘቶ አስመስለን፤
መሄድ እንድንችል ከሰርጉ ታድመን።
አሁን እንዘጋጅ በጥሪው መሰረት፤
እንዳንዘገይ እንድረስ በሰዓት፤
ቀርበን እንድንበላ ከሙሽራው ፍትፍት፤
ለእኛ የተባለው እንዳይሆን ለሌላ፤
ቀድመን እንገኝ እንዳናፍር በኋላ።
አብረን እድንገባ ከሙሽራው ጋራ፤
ነቅተን እንጠብቅ ሙብራታችን ይብራ፤
በውጭ ተጥለን እንዳናይ መከራ፤
ማቀላፋት ይቅር እንቁም በተራ፤
አቤት እንድንል ስማችን ሲጠራ፤
ቁመን እንቆይ ተላብሰን ቀኝ ግራ።
ጣፋጭ ይሁን እንጂ እንዳይሆን መራራ፤
የምናቀርብለት ለላይኛው ሙሽራ፤
ስጦታችን አምሮ ሲያገኝ ተቀባይ፤
ፍስሃ ደስታ ይሆናል በላይ በሰማይ
እኛም ደስ ብሎን ስንል ሃሌ ሉያ፤
እሱም ይሰጠናል የወርቅ መዳሊያ!!!

ሰላም እንባባል እንመስርት ፍቅርን
ዲያብሎስ ተይዞ እንዲታሰርልን
ሁልጊዜ እያደባ ከእግዜር የሚያጣላን።
ከሰውነት ገብቶ የሚያጣላ ሰውን
ከገነት ያስወጣ ሄዋን እና አዳምን
በቃየል ላይ አድሮ የገደለ አቤልን።
በሚካኤል ሰይፍ ተቆራርጦ ይውደቅ
ገብርኤልም መትቶ ይጣለው በሙብረቅ
የዲያብሎስን ቦታ ማመንጫውን ያድርቅ።
ሚካኤል በሰይፉ ቆራርጦ እንዲጥለው
ገብርኤልም በጦር ወግቶ እንዲዘርረው
ሰላም ተባብለን ፍቅርን እንልበሰው።
የጨለማው ንጉሥ ዲያብሎስ ሳጥናኤል፤
እኛን አስደንግጦ እንዳይከተን ገደል፤
ሁልጊዜ እንለምን የሰማዩን ኃያል፤
እሱ እንዲያስጠብቀን በእርሱ ባለ መዋል፤
በዙሪያችን ተክሎ የብርሃን መስቀል።
ፍቅርን መስርተን ሰላም ከተባባልን
የእግዚአብሔር መላእክ ከኛ ጋር ይሆናል
ዲያብሎስን አስሮ ጉድጓድ ያስገባዋል
ለአንድ ሺህ ዓመታት ሰው ሰላም ያገኛል።
የሰላምን እንቅልፍ ተኝተን እድናድር
ከምኚታ በፊት ጌታን እናመስግን
በሰላም አውሎ በሰላም እንዲያሳድር።
<u>ከላይ እንደገለጽኩት ፍቅር ከሌለን እምነታችን ሁሉ የከንቱ ከንቱ ሆኖ ነው የሚቀር።</u>
**<u>ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!</u>**

**<u>ከአዳነ መኮነን</u>**